አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሃ ግብር
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል
የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር

[illegible] ግለሰቦች የመዋቅርና [illegible]

በ
ማርቆስ የሻነው

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሃ ግብር
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል
የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር

# የኮሪያ ዘማቾች ግለተረኮች የመዋቅርና የጭብጥ ትንተና

በ
ማርቆስ የሻነው

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ሰኔ፣2000 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሃ ግብር
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል
የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር

# የኮሪያ ዘማቾች ግለተረኮች የመዋቅርና የጭብጥ ትንተና

በሥነጽሑፍና ፎክሎር ለኤም.ኤ ዲግሪ
ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

በ
ማርቆስ የሻነው

አማካሪ
ዶ/ር ፊቃደ አዘዘ

ሰኔ፣ 2000 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የኮሪያ ዘማቾች ግለተረኮች የመዋቅርና የጭብጥ ትንተና

በ

ማርቆስ የሻነው


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሃ ግብር

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር


የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

........................ ........................

አማካሪ ፊርማ

........................ ........................

የውስጥ ፈታኝ ፊርማ

........................ ........................

የውጭ ፈታኝ ፊርማ

## ማረጋገጫ

ይህ ቴሲስ የእኔ መሆኑንና በውስጡም የተገለገልኩባቸውን ማቴሪያሎች ሙሉ በሙሉ መጥቀሴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም ማርቆስ የቻነው

ፊርማ ..........

የማስረከቢያ ጊዜ ሰኔ ፣ 2000 ዓ.ም

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# ምስጋና

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሰጠኝ የድህረ ምረቃ እስኮላርሺፕ ባለውለታዬ ነው። በመቀጠል አማካሪዬ ዶ/ር ፈቃደ አዘዘን ላመስግናቸው እወዳለሁ። ዶክተርን የማመሰግናቸው ገና እንደተገናኘን የጥናታዊ ጽሁፉን አቅጣጫ በመጠቆም፣ መጻህፍት በማዋስ፤ ስጠፋባቸው በማስታወቂያ ጭምር በመፈለግና በማስፈለግ፣ ሲያገኙኝ በቃልና በሰጠኋቸው ወረቀቶች ላይ ምክርና አስተያየት በመስጠታቸው ነው። ለጥናቴ መረጃ በማቀበል ለተባበሩኝ ለአስር አለቃ አሰፋ አስፋው፤ ለመቶ አለቃ ታደሰ ገ/ክርስቶስ፣ ለኮሎኔል ገ/ኢየሱስ ሚካኤል፤ ለብርጋዲየር ጄኔራል ደስታ ገመዳ፣ ለኮሎኔል አለማየሁ ካሳ እንዲሁም ለአምሳ አለቃ ተስፋዬ ሳህሉ ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁኝ። እነዚህን ግለሰቦች እንዳገኛቸው ለረዱኝ «የኢትዮጵያ ኮሪያ ዘማቾች ማህበር»፣ ለማህበሩ ፕሬዚደንት ኢንጂነር ኮሎኔል ዕምላአለ ወረደ፤ ለማህበሩ ፀሀፊ ሻምበል አክሊሉ ደስታ፣ ለማህበሩ ሰራተኞች ለሻለቃ ለማ አድርጋቸው፤ ለኢፍሬምና ለእቴነሽ ተ/ስላሴ እንዲሁም ለአርቲስት መራዊ ስጦት ምስጋና አቀርባለሁኝ።

በሁለተኛ ደረጃ ይህንን ትምህርት በምከታተልበት ወቅት ወንድሞቼ ትልቁ የሻንውና አቢይ ትእዛዙ ለሰጡኝ ድጋፍ በእጅጉ አመስግናቸዋለሁኝ። የጥናታዊ ጽሁፉን አርምጃ በማገዝ ረገድ የጓደኝነት ውዴታና አንዳንዴም ግዴታቸውን የተወጡት ምርጥነህ ወንድሙ፤ ሰይፈዲን ዑመር፤ ዳዊት ፀሐይና ዳዊት ሃይሉ ምስጋና ይገባቸዋል። ትምህርቴን እንድጨርስ ይመኙ የነበሩት አባቴ፤ እናቴ፤ እህቶቼና ወንድሞቼ ምስጋናዬ ይድረሳቸው። በመጨረሻም ፕሮፌሰር ደረጀ ከበደ፤ ሲቭ የር ጀኔሬሽን ኢትዮጵያ፣ ዶ/ር ኮርኒ ስኪዊር ለጥናቴ መሳካት ለአበረከቱት አስተዋጽኦ ሳላመሰግናቸው አላልፍም።

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በኮሪያ ጦርነት ከተሳተፉ ኢትዮጵያውያን ወታደሮች በተሰበሰቡ ግለተረኮች ላይ ያተኮረ ነው። የጥናቱ ዓላማ የዘማቾቹን ግለተረኮች ከመዋቅርና ጭብጥ አንጻር መተንተን ነው። የትንታኔው ቀዳሚ ክፍል አጠቃሎ፣ እውቅያ፣ ሰራ፣ ልቀት፣ ምዘናና ኮዳ የሚባሉት የግለተረክ መዋቅሮች በዘማቾቹ ግለተረኮች ውስጥ ያላቸውን ገጽታ ናሙና ግለተረኮችን በመውሰድ አሳይቷል። በዚህም መሰረት የዘማቾቹ ግለተረኮች የተጠቀሱትን መዋቅሮች በአጥጋቢ ሁኔታ የአካተቱ ሆነው ተገኝተዋል።

የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ሁለተኛው የትንታኔ ክፍል ከዘማቾቹ የተሰበሰቡት ግለተረኮች ባሏቸው ዓቢይ ጭብጦች ላይ የቀረበ ነው። የኮሪያ ጦርነት ተሳትፏቸውን አስመልክተው የተተረኩት ግለተረኮቻቸው የዘመቻውን ሂደት ጋሬጣማና ስኬታማነት የሚገልጹ ሁለት ዓቢይ ጭብጦች አላቸው። ከሀገር ቤት ሽኝታቸው ጀምሮ ኮሪያ ጦር ግንባር እስከገቡበት ድረስ ያለፉባቸውን ሂደቶች አስመልክተው በዘማቾቹ የተተረኩት ግለተረኮች የኮሪያ ዘመቻቸው ቀዳሚ ሂደቶች ለተራኪዎቹ ጋሬጣማ እንደነበሩ አሳይተዋል። በኮሪያ ጦር ግንባር ግዳጅ ከመቀበል ጀምሮ ሃገር ቤት እስከተመለሱበት ድረስ ያሉትን የዘመቻው ሂደቶች የተመለከቱት ግለተረኮች ደግሞ የኢትዮጵያውያኑ ወታደሮች የኮሪያ ጦርነት ተሳትፎ በስተመጨረሻ መሳካቱን የሚያሳይ ጭብጥ ይዘዋል።

ይህ ጥናት በደሁንታ ክፍሉ በርካታ ሃሳቦችን ያቀረበ ሲሆን ዋነኛው ከዘማቾቹ እድሜ አንጻር የኢትዮጵያ ወታደሮች በኮሪያ ጦርነት የነበራቸውን ተሞክሮ የሚያስረዱ ግለተረኮች ከአረጋውያኑ ዘማቾች የመሰብሰብ ጅምር ተጠናክሮ እንዲቀጥል የሚጠይቅ ነው።




HS LIBRARY
ADDIS ABABA UN

## ሙዳየ ቃላት

| | |
|---|---|
| ስክርብ | transcription |
| ትውራዊ ዳራ | theoretical background |
| ድፍየና | definition |
| አጠቃሎ | abstract |
| አውቅያ | orientation |
| ሴራ | complicating action |
| ልቀት | resolution |
| ምዘና | evaluation |
| ኮዳ | coda |
| ተተራኪነት | tellability |
| ጋሬጣ | predicament |

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

አጠቃሎ I

1. መግቢያ

1.1. የጥናቱ መነሻ.....1

1.2. የጥናቱ ዓላማ.....1

1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት.....1

1.4 የመረጃ አሰባሰብ.....1

1.4.1 የተሰበሰቡ መረጃዎች.....2

1.4.2 የመረጃ ምንጮችና የአሰባሰብ ሂደቶች.....2

1.4.3 የመረጃው አሰባሰብ.....3

1.4.4 ስክረባ.....4

1.5 የጥናቱ ገደብ.....4

1.6 የጥናቱ ተጠቃሚዎች.....5

2. ክለሳ ድርሳን

2.1 የኮሪያ ጦርነት አጭር ታሪክ.....6

2.2 በኮሪያ ጦርነት የኢትዮጵያ ተሳትፎ.....9

2.3 የኮሪያ ዘመቻ አሻራዎች.....11

2.3.1 ዲፕሎማሲያዊ አሻራ.....11

2.3.2 ባህላዊ አሻራ.....12

2.4 የግለተረክ ተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት.....13

3. የግለተረክ ትውራዊ ዳራ (Theoretical background)

3.1 የግለተረክ ድፍኖና (Definition).....19

3.2 የግለተረክ መዋቅር.....19

3.2.1 የአጠቃሎ መዋቅር (Abstract).....20

3.2.2 የአውቅያ መዋቅር (Orientation).....20

3.2.3 የሴራ መዋቅር (Complication).....21

3.2.4 የልቀት መዋቅር (Resolution).....21

3.2.5 የምዘና መዋቅር (Evaluation).....22

3.2.6 የኮዳ መዋቅር (Coda).....23

3.3 የግለተረክ ጭብጥ.....23

3.4 ተተራኪነት (Tellability).....24

3.5 የግስተረክ ክልሰፋ (Classification)........................................................26
4. የኮሪያ ዘማቾች ግለተረኮች የመዋቅርና የጭብጥ ትንተና
4.1 የኮሪያ ዘማቾች ግለተረኮች የመዋቅር ትንተና........................................28
4.1.1. የናሙና ግለተረክ አንድ የመዋቅር ትንተና........................................28
4.1.1.1 የእውትያ መዋቅር........................................................29
4.1.1.2 የሴራ መዋቅር........................................................30
4.1.1.3 የልቀት መዋቅር........................................................33
4.1.1.4 የምዘና መዋቅር........................................................34
4.1.2 የናሙና ግለተረክ ሁለት የመዋቅር ትንተና........................................34
4.1.2.1 የእውትያ መዋቅር........................................................35
4.1.2.2 የሴራ መዋቅር........................................................35
4.1.2.3 የልቀት መዋቅር........................................................37
4.1.2.4 የምዘና መዋቅር........................................................37
4.1.2.5 የኮዳ መዋቅር........................................................38
4.2 የኮሪያ ዘማቾች ግለተረኮች የጭብጥ ትንተና........................................38
4.2.1 የኢትዮጵያ ዘማቾችን የኮሪያ ጦርነት ተሳትፎ ጋሬጣማ
ሂደቶች የሚያሳዩ ግለተረኮች የጭብጥ ትንተና........................39
4.2.1.1 አሽባሪው ሽኝት........................................................39
4.2.1.2. ፈታኝ የመርከብ ጉዞ........................................................40
4.2.1.2.1 የመርከብ አግራሞት........................................40
4.2.1.2.2 ጤና-ነሺው የመርከብ ላይ ቆይታ............40
4.2.1.2.3 የባልደረባን ሬሳ ባህር ስመጣል መቃጣት.42
4.2.1.3 አስደንጋጩ የፑዛን አቀባበል........................................43
4.2.1.4 ትራጀዲያዊው የልምምድ ላይ ሁነት........................................43
4.2.2 የኮሪያ ዘማቾች ግለተረኮች የስኬት ጭብጥ........................................45
4.2.2.1 ግዳጅን መወጣት........................................................46
4.2.2.1.1 ምርኮ የማምጣት ግዳጅን መወጣት.........47
4.2.2.1.2 የስለላ ተልዕኮን መወጣት ........................49
4.2.2.2 የአለመማረክ ስኬት........................................................49
4.2.2.3 የበላዔሰብ ፕሮፓጋንዳ........................................................52
4.2.2.4 ሙያዊ ትሩፋት........................................................54
5. ማጠቃለያ........................................................................................56
6. ደሁንታ........................................................................................60

አባሪ አንድ፡ የተረክ አቀባዮች ዝርዝር....................................................................62
አባሪ ሁለት፡ ለኩሪያ ዘማች ኢትዮጵያውያን ቃለ መጠየቅ የተዘጋጁ ጥያቄዎች...............63
አባሪ ሶስት፡ የግለተረኮች ስብስብ....................................................................66
ዋቢ መጻህፍት..........................................................................................84

# 1. መግቢያ

በዚህ ክፍል የጥናቱን መነሻ፣ ዓላማ፣ አስፈላጊነት፣ የመረጃ አሰባሰብ ሂደት፣ ገደብና ተጠቃሚዎች አስመልክቶ ሃሳብ ይቀርባል፡፡

## 1.1 የጥናቱ መነሻ

የመመረቂያ ጥናት ርዕሶችን በተለያዩ ምክንያቶች ስቀይር ቆይቼ በስተመጨረሻ ከዶ/ር ፈቃደ አዘዘ ጋር በተመካከርነት ተገናኘሁ፡፡ አዲስ ርዕስ መፈለግ ስለነበረብኝ ፍንጭ እንዲሰጡኝ ጠየቅኋቸው፡፡ ከሰፊ ውይይት በኋላ በመጦሪያ ማዕከላት ከሚገኙ አረጋውያን «ፐርሰናል ኤክስፒሪየንስ ናሬቲቭ» ሰብስቤ ጥናት ልሰራ እንደምችል ጠቆሙኝ፡፡ በአረጋውያን ላይ ጥናት የመስራቱ ሃሳብ እንደተጠበቀ ሆኖ ለትኩረት በሚያመች መልኩ ርዕሱን በኮሪያ ዘማቾች ላይ አጠበቡልኝ፡፡ ይህን ተከትሎም ጥናቱ የተለያዩ ሂደቶችን በማለፍ በዚህ መልክ ሊቀርብ በቃ፡፡

## 1.2 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓላማ በኮሪያ ጦርነት ከተሳተፉ የአንደኛው ቃኘው ሻለቃ ዘማቾች ግለተረኮችን ሰብስቦ ያላቸውን መዋቅራዊ ገጽታና ጭብጥ መፈተሽ ነው፡፡ የመጀመሪያውን ዓላማ በተመለከተ በተረክ ጥናት እንደ ግለተረክ ይኖሩታል ተብለው የሚታሰቡት ስድስት ያክል መዋቅሮች ከዘማቾቹ በተሰበሰቡ ግለተረኮች ውስጥ ያላቸውን ገጽታ መፈተሽ ነው፡፡ ሁለተኛው የጥናቱ ዓላማ በዘማቾቹ ግለተረኮች ውስጥ የተስተዋሉትን ዓቢይ ጭብጦች መተንተን ነው፡፡ በመጨረሻም ከተራኪዎቹ በእድሜ መግፋትና ተረኮቻቸው ሊኖሯቸው ከሚችሉ ዘርፈ ብዙ ፋይዳዎች አንጻር ቀርጾ ማቆየት ጥናቱ ከሚያሳካቸው አላማዎች ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት

ኢትዮጵያ ዓለም አቀፋዊ ገጽታ በነበረው የኮሪያ ጦርነት ላይ በአምስት ተከታታይ ዙር ካሳተፈቻቸው ከስድስት ሺህ በላይ ወታደሮች ውስጥ በአሁኑ ሰዓት በህይወት የሚገኙት በመቶዎች የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት ዘማቾቹ በኮሪያ ጦርነት ወቅት የነበራቸውን ግለሰባዊ አሻራ ለአሁኑና ለመጪው ትውልድ በወጉ ቀርጾ ማቆየት ከዘማቾቹ ዕድሜ መግፋት አንጻር ወቅታዊ ተገቢነት አለው፡፡ የአንደኛው ቃኘው አባላት የኮሪያ አውደ ውጊያ የግል ገጠመኝ ትኩረት ተሰጥቶት አለመቀረጹንም ከመረጃ አቀባዮቹ እንደሰማሁና በቤተመጻህፍቶች ከአካሄድኩት ፍተሻ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ይህንን ክፍተት የመሙላት አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ይታመናል፡፡

## 1.4 የመረጃ አሰባሰብ

በዚህ ክፍል በጥናቱ ሂደት ስለሚሰበሰቡ መረጃዎች፣ የመረጃ ምንጮችና የመረጃ አሰባሰብ አጠቃላይ ሃሳቦች ይቀርባሉ፡፡

### 1.4.1 የተሰበሰቡ መረጃዎች

የዚህ ጥናት መረጃዎች በኮሪያ ጦርነት ከተሳተፉ ስድስት ያህል ኢትዮጵያውያን የተሰበሰቡ ግለተረኮች ናቸው።

### 1.4.2 የመረጃ ምንጮችና የአሰባሰብ ሂደቶች

የዚህ ጥናት ዓቢይ የመረጃ ምንጮች በኮሪያ ጦርነት ወቅት በአምስት ዙር ከተሳተፉ ኢትዮጵያውያን ውስጥ የአንደኛው ዙር ዘማቾች ናቸው። ከእነሱም በተጨማሪ የኮሪያ ጦርነትንና የኢትዮጵያን ተሳትፎ አስመልክተው የተጻፉ መጻህፍት፣ ጋዜጦችና መጽሄቶች በመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል። መጻህፍቱ፣ ጋዜጦቹና መጽሄቶቹ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኬኔዲ ቤተመጻህፍት፣ ከኢትዮጵያ ጥናት ተቋም ቤተ መጻህፍትና ከ«ኢትዮጵያ ኮሪያ ዘማቾች ማህበር» የተገኙ ናቸው። ቀጥዬ የጥናቱ ዓቢይ የመረጃ ምንጭ የሆኑትን ዘማቾች ለማግኘት ያለፍኩባቸውን ሂደቶችና መልካም ትብብሮች በተመለከተ ጥቂት ነጥቦችን አቀርባለሁ።

ለዚህ ጥናት መረጃ የሚያቀብሉኝን የአንደኛው ቃኘው ሻለቃ ኮሪያ ዘማቾችን በማግኘት ረገድ «የኢትዮጵያ ኮሪያ ዘማቾች ማህበር» ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። ጥር 23፣ 1999 ዓ.ም ቅድስት ስላሴ ካቴድራል ጀርባ ወደ የሚገኘው የማህበሩ ጽ/ቤት በመሄድ ጸሐፊውን ሻምበል አክሊሉ ደስታን አገኘኋቸው። ስለጥናቱ አስረድቻቸው መረጃ የሚሰጡኝን ዘማቾች በማገናኘት ረገድ እንዲተባበሩኝ ጠየቅኋቸው። ቀጠሮ ሰጡኝና ከወር በኋላ ተመልሼ ወደ ማህበሩ ጽ/ቤት በመሄድ ጸሐፊውን አገኘኋቸው። ሃሳቤን ተቀብለው ማህበሩ ያሳተማቸውን አራት መጽሔቶች ሰጡኝና እነርሱን ካነበብኩ በኋላ ተመልሼ እንድመጣ ነገሩኝ። ከዚዜ በኋላ ወደ ማህበሩ በመሄድ ጸሐፊውን አገኘኋቸው። በማህበሩ በኩል የሚካሄዱ ትብብሮች በሙሉ አድራሻቸው ከማህበሩ ጽ/ቤት ውጪ የሆነውን የማህበሩን ፕሬዚደንት ፈቃድ ማግኘት ስላለባቸው ወደ እርሳቸው መሩኝ። የማህበሩን ፕሬዚደንት ኢንጂነር ኮሎኔል አምላእሉ ወረደን ሚያዚያ 12፣ 1999 ዓ.ም አግኝቼ የጥናቴን አላማ ከገለፅኩላቸው በኋላ የማህበሩ አባላት የጥናቱ ተባባሪ እንዲሆኑ የሚጋብዝ ደብዳቤ እንዲፅፉልኝ ጠየቅኋቸው። ለማህበሩ ጸሐፊ እንደሚያሳውቋቸው ቃል ገቡልኝ።

ሰኔ 2፣ 1999 ዓ.ም የማህበሩን ጸሐፊ አገኘኋቸው። የአንደኛው ቃኘው አባል በመሆናቸው ለቃለ መጠይቅ እንዲተባበሩኝ ስጠይቃቸው ፈቃደኛ ሆኑልኝ። ለሌላ ቀን ቀጠሮ ሰጡኝ። የስራ ጫና ስለነበረባቸው ለቃለ መጠይቅ ሊመቻቸው አልቻለም። እኔም ለጥናቱ የሚያስፈልጉኝን የአንደኛው ቃኘው አባላት ለማግኘት የበኩሉን ብጥርም ሊሳካልኝ አልቻለም። ሐምሌ 17፣ 1999 ዓ.ም ወደ የኢትዮጵያ ኮሪያ ዘማቾች ማህበር ስሄድ ጸሐፊውን ባላገኛቸውም የማህበሩን ፋይናንስ ሰራተኛ የመቶ አለቃ ታደሰ ገብረ ክርስቶስን አገኘኋቸው። የመቶ አለቃው የአንደኛው ቃኘው አባል በመሆናቸው ወደ ማህበራቸው ስመላለስ ስለጥናቱ አውቀው ስለነበር ለቃለመጠይቅ ተባባሪ እንዲሆኑ ጠየቅኋቸው። ፈቃደኝነታቸውን ገልጸው ቀጠሮ ሰጡኝ።

ሐምሌ 30፣ 1999 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ኮሪያ ዘማቾች ማህበር ስሄድ የመቶ አለቃ ታደሰን አገኘኋቸው፡፡ በስራ ጫና ምክንያት ለሌላ ቀን ቀጠሮ እየሰጡኝ እያለ አንድ አረጋዊ ወደ ነበርንበት ቢሮ ገብተው ከመቶ አለቃ ጋር ሲወያዩ ቆዩ፡፡ ከቢሮው ሊወጡ ሲሉ የመቶ አለቃ ስለእኔ ጥናት ለእኚህ አረጋዊ ገለጻ አድርገውላቸው ለቃለ መጠይቅ እንዲተባበሩ ጠየቋቸው፡፡ አረጋዊውም ፈቃደኝነታቸውን በመግለፅ የቀጠሮ ቀን ሲያማርጡ ቆዩና በስተመጨረሻ እዛው በማህበሩ ግቢ ውስጥ ቃለ መጠይቁን ለመስጠት ፈቃደኛ ሆኑ፡፡ እኚህ ዘማች አስር አለቃ አሰፋ አስፋው የሚባሉ ሲሆኑ ኮሪያ እያሉ በውጊያ ላይ በከፍተኛ ደረጃ በመጎዳታቸው ከዛን ጊዜ ጀምሮ በጡረታ ላይ ይገኛሉ፡፡

ነሐሴ 6፣ 1999 ዓ.ም መቶ አለቃ ታደሰ ገብረ ክርስቶስ ቢሯቸው ውስጥ ቃለ መጠይቅ በመስጠት ተባበሩኝ፡፡ ቃለ መጠይቅ እያደረግኋቸው ሳለ በኮሪያ ዘመቻቸው ወቅት ከፍተኛ ጀብድ ስለፈጸሙ ዘማች አነሱና የበለጠ ማብራሪያ እንድጠይቅበት አሳሰቡኝ፡፡ እኔ ሁንም ዘማች ከቢሯቸው ስልክ በመደወል አገኟቸውና ስለጥናቱ ካስረዷቸው በኋላ ቀጠሮ አሰጡኝ፡፡ በቀጠሮው ቀን ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ ሚካኤል በጉለሌ ክፍለ ከተማ መነን ትምህርት ቤት አካባቢ በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ቃለ መጠይቅ ሰጡኝ፡፡

በሌላ ጊዜ በኢትዮጵያ ኮሪያ ዘማቾች ማህበር ጽ/ቤት ውስጥ የሚሰራው ኤፍሬም የተባለ ወጣት ለስራ ጉዳይ ወደ ማህበሩ ከመጡት ኮሌኔል አለማየሁ ካሳ ጋር አገናኘኝ፡፡ እሳቸውም ቀጠሮ ሰጥተውኝ ነሐሴ 21፣ 1999 ዓ.ም ቦሌ ቀበሌ 19 መዝናኛ ክበብ ውስጥ ተገናኝተን ቃለ መጠይቅ አደረግኋቸው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የኢትዮጵያ ኮሪያ ዘማቾች ማህበር ሴክሬተሪ የሆነችው እቴነሽ ተ/ስላሴ ብርጋዴየር ጀኔራል ደስታ ገመዳን በስልክ አገናኘ ችኝ፡፡ የጥናቱን አላማ ለጀኔራሉ ከአስረዳኋቸው በኋላ ቀጠሮ ሰጡኝ፡፡ ነሐሴ 23፣ 1999 ዓ.ም ልደታ ክፍለ ከተማ ብስራተ ገብርኤል አካባቢ በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ቃለ መጠይቅ አደረግኋቸው፡፡

አማካሪዬ የኮሪያ ዘመቻ በሙዚቃ በኩል ያበረከተው አስተዋጽኦ ሊኖር እንደሚችል በማሰብ አቶ መርዓዊ ስጦት የተባሉ የብሄራዊ ቴያትር ትረምፔት ተጫዋችን እንዳዋያቸው ጠቆሙኝ፡፡ እሳቸውም የበለጠ መረጃ ሊሰጡኝ ወደሚችሉት አምሳ አለቃ ተስፋዬ ሳህሉ መሩኝ፡፡ አምሳ አለቃ ተስፋዬ ከሁለተኛውና ከሶስተኛው ቃኘው ሻለቃ ጋር ወደ ኮሪያ የዘመቱ ሲሆን ህዳር 21፣ 2000 ዓ.ም ቂራ አካባቢ በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ቃለ መጠይቅ በመስጠት ተባብረውኛል፡፡

### 1.4.3 የመረጃው አሰባሰብ

የዚህ ጥናት መረጃዎች የተሰበሰቡት በቴፕ ሪከርደር አጋዥነት ቃለ መጠይቅ በማድረግ ነው፡፡ የመተረኪ መሳሪያው ተረክ ለመሰብሰብ ሁነኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ ይኸውም

እያንዳንዱን ተረክ ቃል በቃል ለመጨበጥና ተራኪው በለመደው የንግግር ፍጥነትና ፍሰት ገጠመኞቹን እንዲተርክ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል።

የግለተረክ ገጠመኝ መፍለቂያ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ ሁነቶችን መሰረት ያደረጉ ናሙና ጥያቄዎች ተዘጋጅተው በቃለ መጠይቅ ወቅት ለዘማቾቹ ቀርበዋል። እነዚህ ጥያቄዎች አባሪ ሆነው በጥናታዊ ጽሁፉ መጨረሻ ላይ ተቀምጠዋል። ጥያቄዎቹ ሌሎች ጥያቄና መልሶችን ስለሚጋብዙ ከናሙና ጥያቄዎቹ ተጨማሪ ሌሎች ጥያቄዎችም በቃለ መጠይቅ ወቅት ቀርበዋል። በሌላ በኩልም በዚህ ጥናት ውስጥ የተካተቱት ግለተረኮች በሚከወኑበት ወቅት የትረካውን ፍሰት ላለማደናቀፍ አጥኚው ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። ቃለ መጠይቆቹ ያበቁ የነበሩት ዘማቾቹ መጨመር ወይም መናገር የሚፈልጉት ጉዳይ ካለ በመጋበዝና በጥናታዊ ጽሁፉ ውስጥ ሙሉ ስማቸውን ጠቅሼ እንድጠቀም ፈቃድ በመጠየቅ ነው።

## 1.4.4 ስክረባ (transcription)

በዚህ ጥናት ትንታኔ ውስጥ በናሙናነት የቀረቡትና በአባሪነት የተያያዙት ግለተረኮች ቃል በቃል ወደ ጽሁፍ የሰፈሩ ናቸው። ተራኪዎቹ የአነጋገር ዘዬአቸው ይሁን ወይንም የእድሜ መግፋት መሆኑን በግልጽ ባለየሁበት ሁኔታ ቃል የማይሞሉ ድምጾችን (syntagms) በትረካቸው ወቅት እጅግ የሚያዘወትሩ በመሆኑ ይህንንም ስክርቢያለሁኝ።

## 1.5 የጥናቱ ገደብ

የዚህ ጥናት ዓላማ በኮሪያ ጦርነት ወቅት ኢትዮጵያ በአምስት ዙር ካዘመተቻቸው ወታደሮች ውስጥ የአንደኛው ቃኘው ሻለቃ አባላት ብቻ የሚሰበስቡ ግለተረኮችን መተንተን ነው። መረጃ አቀባዮቹ የአንደኛው ዙር አባላት ብቻ እንዲሆኑ የተደረገው የኢትዮጵያ ኮሪያ ዘማቾች ግለተረክ እስከ አሁን አለመሰብሰቡንና አለመጠናቱን መሰረት በማድረግ በአምስት ዙር ከዘመቱት ውስጥ የመጀመሪያ ዙር ዘማቾችን በማጥናት አካዳሚያዊ ትኩረት ለመሳብና ተከታይ አጥኚዎች የኮሪያውን ዘመቻ አምስት ዙሮች ቅደም ተከተል ይዘው እንዲሄዱ መሰረት ለመጣል ነው። ትንታኔውን በተመለከተም አላማው የዘመቻውን ታሪክ ማሳየት ሳይሆን በግለተረክ መከሰቻነት የተሰበሰቡት የዘመቻው ትውስታዎች ያላቸውን ተረካዊ መዋቅርና ጭብጥ ማሳየት ነው።

በዚህ ጥናት ውስጥ መረጃ ምንጮቹን ለመግለፅ የኮሪያ ዘማቾች ወይም የኢትዮጵያ ወታደሮች የሚሉ አገላለፆችን እያፈራረቅሁ ተጠቅሚያለሁ። እነዚህ አገላለፆች የመረጃ ምንጮቹን ለይተው በብቸኝነት የማይገልጹ ናቸው። ለምሳሌ የኮሪያ ዘማቾች የሚለው ሀረግ በአምስት ዙር ወደ ኮሪያ የሄዱትን ወታደሮች በሙሉ ሊገልፅ ይችላል። ነገር ግን በዚህ ጥናት አጠቃቀም ውስጥ የአንደኛ ዙር ዘማቾች ብቻ ለመግለጽ የዋለ ነው። የኢትዮጵያ ወታደሮች የሚለው አገላለፅም ተመሳሳይ ጠባይ አለው።

## 1.6 የጥናቱ ተጠቃሚዎች

በዚህ ጥናት የሚሰበሰቡት ግለተረኮች የኩሪያ ዘማቾችን ተረኮችና ታሪክ ለሚያጠኑ ባለሙያዎችና በግለተረክ ላይ የተመሰረተ ጥናት ለሚያካሂዱ ተማሪዎች ሊያገለግሉ ይችላሉ:: ግለተረኮቹ ተሰንደው በ«የኢትዮጵያ ኮሪያ ዘማቾች ማህበር» እና በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ሙዚየሞች ውስጥ በቅርስነት ይቀመጣሉ::

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

## 1. ክለሳ ድርሳን

በዚህ ምዕራፍ የኮሪያ ጦርነትን አጭር ታሪክ፣ የኢትዮጵያን ተሳትፎ እና የዘመቻውን አሻራዎች የተመለከቱ መረጃዎች የሚቀርቡ ሲሆን በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ስር ደግሞ ከእኔ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ ጋር ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው ጥናቶችና ጽሁፎች ይዳሰሳሉ።

### 2.1 የኮሪያ ጦርነት አጭር ታሪክ

ጃፓን እ.ኤ.አ በ1910 ዓ.ም ኮሪያን በመያዝ ቅኝ ግዛትዋ መሆንዋን አወጀች (Jun-yop 1995:5)።* ኮሪያውያን ነጻነታቸውን ለማስመለስ ከወራሪዋ ጋር የሚመጣጠን ወታደራዊ አቅም ስላልነበራቸው የሽምቅ ውጊያ ጀመሩ። ይህንን የሽምቅ ውጊያ ቀድሞ በማደራጀት በመጀመር ጉዳይ ላይ የደቡብ ኮሪያና የሰሜን ኮሪያ ዜጎች መግባባት የላቸውም።** ደቡቦቹ የመጀመሪያው የነጻነት ንቅናቄ አደራጅ ሲንግማን ሪ ናቸው ሲሉ ሰሜኖቹ ደግሞ ኪም ኢል ሱንግን የመጀመሪያው የሽምቅ ውጊያ መሪ አድርገው ይወስዷቸዋል (The History of United Nations Forces in the Korean War 1972:9)።

ይህም ሆኖ የተጀመረው የሽምቅ ውጊያ የኮሪያን ነጻነት ለማስመለስ አቅም ያልነበረው ሲሆን የሁለተኛው የዓለም ጦርነት መቀስቀስ ግን ለኮሪያውያኑ መልካም አጋጣሚን ይዞ ብቅ አለ። ጃፓን ከአሜሪካና ሶቪዬት ህብረት በተቃራኒ መሰለፏን ተከትሎ የሁለቱ ሃገራት ጦር ኮሪያ ወደ ሰፈረው የጃፓን ወታደራዊ ሃን በመገስገስ ጃፓንን አሸነፈ (Stowe 1986:9)።

የኮሪያን መልክአ ምድር አቀማመጥ በተመለከተ 34 ዲግሪ ደቡብና 43 ዲግሪ ሰሜን ላቲቲዩድ እንዲሁም 124 ዲግሪ ምዕራብና 131 ዲግሪ ምስራቅ ሎንጊቲውድ መሃል ይገኛል። 38ኛው ፓራሌልም ኮሪያን ሁለት እኩል ቦታዎች ላይ ይከፍላታል። ይህንኑ መሰረት በማድረግ ከ38ኛው ፓራሌል በላይ ያለውን ክልል ሶቪዬት፣ ከዚያ በታች ያለውን ደግሞ አሜሪካ እንድትቆጣጠረው የሁለቱ ሃገራት መሪዎች ትሩማንና እስታሊን ተስማሙ (Kaushik 1972:8)። ይህ ክፍፍል በሁለቱ ሃያላን ሃገራት ጦር መሃከል የጠራ ወሰን ለማበጀት የተካሄደ ነው ቢባልም አንድ የነበረውን የኮሪያን ግዛት ሰሜንና ደቡብ በሚል ድንበር ይከፍለዋል ተብሎ አልተገመተም ነበር።

ከጃፓን አገዛዝ መላቀቅን ተከትሎ አብዛኞቹ ኮሪያውያን ወደ ቀድሞ ነጻነታቸው መመለስን ቢጠብቁም ሳይሳካላቸው ይቀራል። ይባስ ብሎም ኦገስት 1948 ዓ.ም በሲንግማን ሪ መሪነት ሪፐብሊክ ኦፍ ኮሪያ በደቡብ እንዲሁም በሴፕቴምበር 1948 ዓ.ም በኪም ኢል ሱንግ መሪነት ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኦፍ ኮሪያ በሰሜን ተመሰረቱ። የመጀመሪያዋ ዋና ከተማዋን

---



* በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የምንከተለው የጎመቱ ምሕረት አቆጣጠር ለእንግሊዝኛ የመረጃ ምንጮች አውሮፓዊና ለአማርኛዎቹ ደግሞ ኢትዮጵያዊ ነው።

** ‹ደቡብ ኮሪያ› እና ‹ሰሜን ኮሪያ› የሚሉት ስያሜዎች አፈላላዊ አጠቃቀም የላቸውም። ነገር ግን በበርካታ ጽሑፎች ውስጥ ስያሜዎቹን የመጠቀም ዝንባሌ ስላለ ይህንኑ ለመከተል ፈቅጃለሁ።

ሴዑል ስታደርግ ሁለተኛዋም ፒዮንግያንግ አደረገች። አሜሪካ ለደቡቧ፣ ሶቪዬት ህብረት ደግሞ ለሰሜኗ እውቅናን በመስጠት ደቡብና ሰሜን ኮሪያ የሚባሉ ሃገራት እንዲፈጠሩ አስተዋጽኦ አበረከቱ (Stowe 1986:22)።

ሁለቱም ኮሪያውያን ነጻ መንግስትነታቸውን በአወጁ ማግስት የየራሳቸውን ጦር ሰራዊት ለማደራጀት ተንቀሳቀሱ። አሜሪካ የደህንነት ዋስትናን እሰጥሻለሁ በማለት ደቡብ ኮሪያ የራሷን ጦር ኃይል እንዳታቋቁም ያገደቻት ሲሆን ሰሜን ኮሪያ ግን የራሷን ህዝባዊ ጦር አደራጀች። ይህን ተከትሎም የደህንነት ዋስትና ስጋት በደቡብ ኮሪያ ዘንድ እያየለ መጣ። ሶቪዬት ህብረትም በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሰበብ ወደ ኮሪያ የገባው የእሷና የአሜሪካ ጦር ከኮሪያ መውጣት አለበት የሚል አቋም አንጸባረቀች። ሃሳቡ በአሜሪካ ዘንድ ተቀባይነት ቢያጣም ሶቪዬት ግን ጦሯን ሙሉ በሙሉ ከሰሜን ኮሪያ አስወጣች (Steuck 1995:34)።

ደቡብ ኮሪያ ከሰሜን ኮሪያ ሊቃጣባት የሚችለውን ወረራ ለመቋቋም አቅም የለኝም በሚል የሶቪዬትን ፈለግ ተከትላ አሜሪካ ጦሯን እንዳታስወጣ ተማጸነች። የሰሜን ኮሪያ መንግስት እጅ አለበት ተብሎ የሚገመት ከፍተኛ ህዝባዊ አመጽ በደቡብ ኮሪያ መቀስቀስ የወረራ ስጋቱን ይበልጥ አባባሰው። የሬዲዮ ፕሮፓጋንዳ ዘመቻም በሁለቱ መንግስታት መካከል ተጠናክሮ ቀጠለ። በዚህ መካከል የተባበሩት መንግስታት ማንኛውም የውጪ ኃይል ከኮሪያ ለቆ መውጣት አለበት የሚል ውሳኔ አሳለፈ። አሜሪካ ውሳኔውን በመቀበል ጦሯን በጁን 1949 ዓ.ም ከደቡብ ኮሪያ አስወጣች (Kaushik 1972:25)።

በኦክቶበር 1949 ዓ.ም የሰሜን ኮሪያ መንግስት ደቡብ ኮሪያን በመቆጣጠር የሁለቱን ኮሪያዎች ዲሞክራሲያዊ ውህደት እውን የማድረግ እቅድ እንዳለው ለተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሃፊ በደብዳቤ አሳወቀ። ይህ ሁኔታ በዛው ሰሞን ከአሜሪካ ጦር ባለስልጣናት ሰላሳ ስምንተኛውን ፓራሌል መጎብኘት ጋር ተዳምሮ የአካባቢውን ውጥረት አናረው። በመጨረሻም ጁን 25፣ 1950 ዓ.ም ሰሜን ኮሪያ በደቡብ ኮሪያ ላይ ጦርነት ከፈተች (Skordilcs 1954:5)።

የሰሜን ኮሪያ ጦር ሁለቱን ሃገራት የሚለየውን ድንበር ጥሶ በመግባት በከፍተኛ ፍጥነት እየገሰገሰ ወደ ደቡብ ኮሪያ ገባ። የደቡብ ኮሪያ ዋና ከተማ የሆነችውን ሴዑልም ጁን 28፣ 1950 ዓ.ም ተቆጣጠረ። የደቡብ ኮሪያ ጦር በወቅቱ የሰሜኖቹን ጥቃት መቋቋም የሚያስችል አቅም በማጣቱ የአሜሪካ እግረኛ ጦር ከጃፓን ተነስቶ ወደ ደቡብ ኮሪያ በመግባት ሰሜኖቹን ቀድሞ ወደ ነበሩበት ሰላሳ ስምንተኛው ፓራሌል ድንበራቸው መለሳቸው። በዚህ መሃከል የተባበሩት መንግስታት የደህንነት ምክር ቤት ተሰብስቦ አካባቢውን የተመለከተ ባለሶስት ነጥብ ውሳኔ ያሳለፈ ሲሆን እነሱም የጦርነቱን በአስቸኳይ መቆም፣ የሰሜን ኮሪያን ከደቡብ ኮሪያ ግዛት መውጣትና የተባበሩት መንግስታት አጣሪ ኮሚሽን የተፈጠረውን ችግር መርምሮ ለምክር ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርግ የሚጠይቁ ናቸው (Kaushik 1972:62)።

ይህ ውሳኔ በዩጎዝላቪያ ብቸኛ ድምጸ ተአቅቦ ተቀባይነት አግኝቷል። ነገር ግን ሰሜን ኮሪያ ለተላለፈው ውሳኔ ተገዥ ባለመሆንዋ ማንኛውም የተባበሩት መንግስታት አባል ሀገር

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ሉአላዊነቱ በኀይል ከተጣሰ በተቀሩት አባላት የጋራ እርምጃ መቀልበስ አለበት የሚለውን በድርጅቱ መተዳደሪያ ህግ አንቀፅ አንድ ላይ የሰፈረውን አቋም ለማስከበር ተንቀሳቀሰ:: ይህን ተከትሎም ጁን 27፣ 1950 ዓ.ም የተጠራው ስብሰባ የድርጅቱ አባል ሀገራት ጥቃቱን ለማስወገድ ድጋፋቸውን ለደቡብ ኮሪያ እንዲሠጡ አሳሰበ:: እነዚህ የደህንነት ምክር ቤቱ ሁለት ውሣኔዎች ሲተላለፉ ምንም አይነት ተቃውሞ ያልገጠማቸው ሲሆን ይኸውም ሶቪየት ህብረትና ቻይና ራሳቸውን አግልለው ስለነበረ ነው (The History of United Nations Forces in the Korean War 1972:46)::

በመጨረሻም የተባበሩት መንግስታት ጦር ከደቡብ ኮሪያ ጎን እንዲሰለፍ የሚጠይቀው የደህንነት ምክር ቤቱ የውሳኔ ሀሳብ በአሜሪካ ጠያቂነት ለተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ከሃምሳ ዘጠኝ አባል ሀገራት ውስጥ ሃምሳ ሶስቱ ደገፉት:: ከእነዚህ ሀገራት ውስጥ አስራ ስድስቱ ወታደራዊ ድጋፍ እስከመስጠት ሲሄዱ የተቀሩት ስምንቱ ደግሞ የሎጂስቲክ ድጋፍ ሰጥተዋል (O' Ballance 1969:161)::

በተባበሩት መንግስታት ባንዲራ ስር የተዋቀረው ጦር በአሜሪካዊው ጀኔራል ማካርተር መሪነት ሴፕቴምበር 27፣ 1950 ዓ.ም ሁለቱን ኮሪያዎች ወደ የሚለየው ድንበር በመጠጋት የሰሜን ኮሪያ ጦር ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ትጥቁን እንዲፈታ ጠየቀ:: ለዚህ ጥያቄ ሰሜን ኮሪያ አዎንታዊ ምላሽ ባለመስጠትዋ የተባበሩት መንግስታት ጦር ድንበሩን ተሻግሮ እንዲሄድ ታዘዘ:: በዚህ መሀከል የቻይና መንግስት የተባበሩት መንግስታት ጦር ሰላሳ ስምንተኛውን ፓራሌል አልፎ ከሄደ ከሰሜን ኮሪያ ጎን ለመሰለፍ እንደምትገደድ አስጠነቀቀች:: የተባበሩት መንግስት ጦር ግን የቻይናን ማስጠንቀቂያ ችላ በማለት 38ኛውን ፓራሌል አልፎ በመሄድ ኦክቶበር 19፣ 1950 ዓ.ም የሰሜን ኮሪያን ዋና ከተማ ፒዮንግያንግ ተቆጣጠረ:: በቀናት ልዩነትም ሰሜን ኮሪያን ከቻይና በሚለየው ድንበር ላይ ደረሰ:: ይህንን አጋጣሚ ተከትሎም ኦክቶበር 26፣ 1950 ዓ.ም ቻይና ጦሯን በማንቀሳቀስ ወደ ሰሜን ኮሪያ ገባች (Kaushik 1972:99):: ይህን ተከትሎም በአሜሪካ ሃሳብ አቅራቢነት የተባበሩት መንግስታት የደህንነት ምክር ቤት ቻይናን ወራሪ በማለት አወገዘ (Kaushik 1972:133)::

ቻይና ግን የድርጅቱን ውሳኔ ባለመቀበል ወታደሮቿን ከሰሜን ኮሪያውያን ጋር በማስተባበር ውጊያውን ቀጥላበት ዲሴምበር 4፣ 1951 ዓ.ም ፒዮንግያንግን ያዘች:: በሶቪየት ህብረት የአየር ኃይል ጥቃት በመታገዝም በዲሴምበር ማለቂያ ላይ ሰላሳ ስምንተኛውን ፓራሌል በማቋረጥ ጃንዋሪ 4፣ 1951 ዓ.ም የደቡብ ኮሪያ ዋና ከተማ ሲዑልን ተቆጣጠረች:: በዚህ መካከል በአሜሪካን መሪነት ከደቡብ ኮሪያ ጎን የተሰለፉት የተባበሩት መንግስታት ወታደሮች በመልሶ ማጥቃት ውጊያ ሲዑልን ከመቆጣጠር አልፈው የቻይናን ጦር ወደ ሰላሳ ስምንተኛው ፓራሌል መለሱት (Skordiles 1954:6):: በዚህ የጦርነቱ ሂደት መካከል ኢትዮጵያ የላከችው ቃኘው ሻለቃ ጦር በተባበሩት መንግሥታት ጥላ ስር ደቡብ ኮሪያን በመወገን በኮሪያ ጦርነት ለመሳተፍ ውቅያኖስ አቋርጦ ደቡብ ኮሪያ ወደብ ግንቦት 6፣

1943 ዓ.ም ደረሰ (ቃኘው፡1995፡19)። የኮሪያ ጦርነት ለሶስት አመታት ከተካሄደ በኋላ በ1954 ዓ.ም በሰሜንና ደቡብ ጎራ በተሰለፉ የውጭ ሃገራት ተሳትፎ የጦርነት ማቆም ስምምነት በመፈራረም የኮሪያ ጦርነት አበቃ (Stowe 1986:213)።

**2.2 በኮሪያ ጦርነት የኢትዮጵያ ተሳትፎ**

ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ጁን 27፡ 1950 ዓ.ም ያሳለፈውን ውሳኔ ከደገፉት ሃገሮች ውስጥ አንዷ ስትሆን በወር ውስጥ ወታደርና 100.000 (መቶ ሺህ ብር) ለማበርከት ፈቃደኛ መሆኗን የሚገልፅ ቴሌግራም ለመንግስታቱ ድርጅት ዋና ጸሐፊ ላከች (Dereje 1993:11)። የድጋፍ ሃሳቧ ተቀባይነት ማግኘቱን ተከትሎም ወደ ኮሪያ የሚዘምቱ ወታደሮችን የመመልመሉና የማዘጋጀቱ ስራም በከፍተኛ ፍጥነት ተጀመረ። ይህ ጦር በወቅቱ ዘመናዊ አደረጃጀት ከነበረው የክብር ዘበኛ ጦር መሀከል እንዲመለመል ተወሰነ።

የክብር ዘበኛ ጦር በ1917 ዓ.ም ከተቋቋመው የመትረየስ ተኳሽ ተውጣጥቶ የተቋቋመ ሲሆን በወቅቱ ዘመናዊ የሚባልና የጣሊያን ወረራ ወቅት ንጉሡ ማይጨው ላይ የመሩት ጦር ነው። ከጣሊያን ወረራ በኋላ ንጉሡ የክብር ዘበኛን ጦር ይበልጥ አደራጁት። የክብር ዘበኛ ጦር በወቅቱ የነበረው ሚና ንጉሰ ነገስቱን ቤተመንግስቱንና ዋና ከተማዋን መጠበቅና በብሔራዊ በአላት አክባበር ላይ መሳተፍ ነው (Dereje 1993:11)።

በኮሪያ ጦርነት ለመሣተፍ ኢትዮጵያ ቃል መግባቷን ተከትሎ ለዚሁ ዘመቻ የሚሆኑ ወታደሮች ከዚሁ ጦር መሃል ተመለመሉ። የዘማቾቹ ምልመላና ዝግጅት ትዕዛዝ ለክብር ዘበኛ ጦር መሪ ብርጋዲየር ጀኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ከንጉሡ የተላለፈ ሲሆን የማደራጀቱን ስራም በበላይነት እንዲመሩ የክብር ዘበኛ ጦር ምክትል አዛዥ ለነበሩት ኮሎኔል መንግስቱ ንዋይ ተሡጠ። በክብር ዘበኛ ውስጥ የተካሄደው የመጀመሪያ ስራ በሙያዊ ብቃታቸው ላይ ተመስርቶ ወታደሮችን ከየጦር ክፍሉ መመልመል ሲሆን በዚህም መሠረት ከክብር ዘበኛ እግረኛ ብርጌድ መሃል አራት ሻለቃ እግረኛ ጦር እና አንድ ከባድ መሣሪያ ተኳሽ ተመልምሎ ተዋቀረ። ወደ ኮሪያ የሚዘምተው ጦር አዛዦችና የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ክፍሎችም ተዋቀሩ (Dereje 1993:18)።

ዘማቹ ጦር ተደራጅቶ ካለቀ ኋላ "selected battalion" የሚል ስያሜ በአዛዦቹ ተሰጠው። ይህ ስያሜ ተቀይሮ ጦሩ "maneuver battalion" ተባለ። ስያሜውም ወደ ኮሪያ ለመንቀሳቀስ ሳምንታት እስኪቀር ድረስ የጦሩ መጠሪያ ሆኖ አገልግሏል። በሁለቱም ስያሜዎች ስር ምልምሎቹ በሦስት ተከፍለው ስልጠናቸውን ለስምንት ወራት ያህል አካሄዱ (ቃኘው፡1994፡9)። የአዛዦች ቡድን ስልጠና ለግማሽ ቀን በክፍል ውስጥ የሚካሄድ ሲሆን የእግረኛ ጦር ልምምድ ደግሞ ቀኑን ሙሉ ይካሄድ ነበር። ሦስተኛው ቡድን ደግሞ ከባድ መሣሪያ ተኳሾች ሲሆኑ የከባድ መሳሪያ አጠቃቀም ይለማመዱ ነበር። ምልምሎቹ የመስክ ልምምዳቸውን ከአዲስ አበባ ሰሜንና ሰሜን ምስራቅ በሚገኙ ተራሮች ሲያካሄዱ ቆዩ።



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ለምምዱም የተጠናቀቀ ሲሆን ጦሩም «የኮሪያ ሻለቃ» የሚል ሶስተኛ ስያሜ መጋቢት መጨረሻ 1943 ዓ.ም ተሰጠው (Dereje 1993:20)።

ወደ ኮሪያ ለመሄድ ሁለት ሳምንት ሲቀራቸው ለምልምሎቹ የዝግጅታቸው አላማ ወደ ኮሪያ ለመዝመት መሆኑ ተገለጸላቸው። ጥቂት ቀናት ሲቀራቸውም እያንዳንዱ ወታደር በጦር ሜዳ ቢወድቅ ጡረታው ለማን እንደሚሰጥ እንዲያሳውቅና ቤተሰቡንም ተሰናብቶ እንዲመለስ ታዘዘ። ይህን ተከትሎም የኮሪያ ዘመቻ ወሬ በሃገሪቱ ውስጥ በፍጥነት የተሰራጨ ሲሆን አንዳንድ ወታደሮችም ቤተሰቦቻቸውን ለመሰናበት እንደሄዱ ሳይመለሱ ቀሩ። የተወሰኑ ወላጆችም የቤተሰባቸው አባል የሆነው ወታደር ከዘመቻው እንዲቀነስ እስከማመልከት ደረሱ። አብዛኞቹ ወታደሮች ግን ወደ ኮሪያ ለመዝመት ዝግጁ ሆኑ (Dereje 1993:20)።

ለኮሪያ ሻለቃ ጦር አባላት ሚያዚያ 4፣ 1943 ዓ.ም በጃንሜዳ ኦፊሴላዊ የሽኝት ስነስርአት ተዘጋጀላቸው። ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴም በከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ታጅበው በመድረስ ንግግር ያደረጉ ሲሆን በንግግራቸው ውስጥ ቀጥሎ ያለው ይገኝበታል።

> ሩቅ በሆነ ሀገር ሄዳችሁ እንድትዋጉ ስትላኩ የምትታገሉት በኢትዮጵያ ሆነን እንደምንረዳው ለነጻነትና በራስ ለመገዛት መብት ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያ በራቀ መሬት ላይ ሆናችሁ በንብረት ስራ የአለም ጸጥታ ለሚድንበት ለሲኩሪቲ ኮሌክቲፍ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ተሳስራ ለኖረችበት ለዚህ ለተቀደሰ መሰረታዊ ነገር ትከላከላላችሁ (አዲስ ዘመን፣ 1943፣ 2)።

ንጉሱ በመቀጠል ለዘመቻው ጠቅላይ አዛዥ ለኮሎኔል ከበደ ገብሬ የኢትዮጵያን ባንዲራ ያስረከቡ ሲሆን ፓትሪያርኩ አቡነ ባስልዮስም የዘማቾቹ ተልዕኮ እንዲሳካ ፀሎት አደረሱ።

በዚሁ የሽኝት ንግግራቸው ላይ ንጉሡ ኮሪያ ዘማቹን ጦር «ቃኘው ሻለቃ» ብለው ሰየሙት። «ቃኘው» የሚለው ቃል ለዘማቾቹም ሆነ ለሌላው ህዝብ አዲስ አልነበረም። ይህ ቃል ከራስ መኮንን ፈረስ ስም የተወሰደ ሲሆን ፈረሱ «አባ ቃኘው» ይባል ነበር። ንጉሱ ከኮሪያ ዘማች ጦር ስያሜንት በፊት ቃሉን በኢጣሊያ ወረራ ወቅት ንጉሱ ላስመጡት አውሮፕላን መጠሪያነት አውለውታል። ንጉሡ ኋላ ላይ ደግሞ ይህንን ስም ለኮሪያው ዘማች ሻለቃ መጠሪያ አደረጉት። ይህ ስም ከኮሪያ ጦርነት በኋላም ቢሆን አስመራ ለሚገኘው የኢትዮጵያና አሜሪካ ጦር ማዕከል ስያሜንት ውሏል። በክብር ዘበኛ ጦር ማዘዣ ማዕከል ውስጥ የነበረ የህክምና ክፍልም በዚህ ስያሜ ተጠርቷል (Dereje 1993:21-22)።

ሚያዚያ 5፣ 1943 ዓ.ም የአንደኛው ቃኘው ሻለቃ አባላት ከጃንሜዳ ተነስተው ለገሀር ድረስ ከፍተኛ ቁጥር ባለው ህዝብ ታጅበው የደረሱ ሲሆን ባቡር ተሳፍረው ወደ ጅቡቲ አቀኑ። ዘማቾቹም ጅቡቲ ደርሰው ጄኔራል ማክሬይ በተባለ የአሜሪካ የጦር መርከብ ተሳፍረው እ.ኤ.አ ሚያዚያ 16፣ 1951 ዓ.ም ወደ ኮሪያ ጉዞ ጀመሩ (ቃኘው፣ 1996፣ 9)። ከሃያ አንድ ቀን ጉዞ በኋላ እ.ኤ.አ ግንቦት 7፣ 1951 ዓ.ም ደቡብ ኮሪያ ወደብ ፑዛን ደረሱ። የደቡብ ኮሪያ ፕሬዚደንት፣ የተባበሩት ጦር አዛዦችና ሲቪል ህዝብ አቀባበል አደረጉላቸው። ከዚያ

በኋላ ዶንግሬ በሚባለው ስፍራ ወደሚገኘው የተባበሩት መንግስታት ካምፕ በመንቀሳቀስ የውጊያ ልምምድ ለስድስት ሳምንታት አደረጉ:: ልምምዱ እንዳለቀም ሐምሌ 4፣ 1951 ዓ.ም በአሜሪካ ሰባተኛ ክፍለ ጦር ዘጠነኛ ኮር ሰላሳ ሁለተኛ ብርጌድ አራተኛ ሻለቃ ስር ተደራቢ ሆነው ተሰለፉ:: ከአንድ ዓመት የኮሪያ ቆይታቸው በኋላም ሚያዝያ 23፣ 1952 ዓ.ም አዲስ አበባ ገቡ (ቃኘው፣1994፣9)::

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ በአምስት ዙር ወደ ኮሪያ የላከቻቸው ወታደሮች ብዛት 6037 ሲሆን 1280ዎቹ የአንደኛ ቃኘው አባላት ነበሩ:: ለኮሪያ ጦርነት ከተላኩት ወታደሮች ውስጥ 121 በውጊያው ላይ ሲሞቱ 536 ደግሞ ቆስለዋል:: «ቃኘው ሻለቆች በኮሪያ በተደጋጋሚ ባደረጉት ውጊያ አንድም ወታደር ጠመንጃውን አሽቀንጥሮ፣ ትጥቁን ፈትቶ እጁን ወደ ላይ ሰቅሎ አልተማረከም:: አንድም የኮሪያ ዘማች አቅጣጫውን ስቶም ይሁን ሞቶ የጠፋበት፣ አሬሳው ጠላት እጅ የገባበት ታሪክ አልተከሰተም» (ቃኘው፣1994፣19)::

## 2.3 የኮሪያ ዘመቻ አሻራዎች

ይህ ክፍል የዚህ ጥናት መረጃ አቀባዮች የተሳተፉበት የኮሪያ ጦርነት ያሳረፈውን ፈርጀ ብዙ ጉልህ አሻራ ለማሳየት ያለመ ነው::

### 2.3.1 ዲፕሎማሲያዊ አሻራ

ኢትዮጵያ በኮሪያ ጦርነት መሳተፏን መሰረት አድርጎ በርካታ ሃገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ አንድምታ ያላቸው ጉዳዮች ተፈጥረዋል:: ከእነዚህ ውስጥ አንደኛ ሀገሪቱ በአለም አቀፍ መድረክ የነበራት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መጠናከር ነው:: በተለይ ከአሜሪካ ጋር የነበራት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መጠናከር በሀገራዊ ጉዳይ ላይ ጉልህ ሚና ተጫውቷል:: ለዚህም ማሳያው የኤርትራ ጉዳይ ነው:: "It was the Korean war that convinced the United States that all of Eritrea should be integrally federated with Ethiopia." (Marcus 1982:353) «የኢትዮጵያ በኮሪያ ጦርነት መሳተፍ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋርሙሉ በሙሉ እንድትዋሀድ አሜሪካንን ያሳመነ ምክንያት ሆኗል::»

ከዲፕሎማሲያዊው ግንኙነት በተጨማሪ በወታደራዊና በኢኮኖሚ መስክም የሁለቱ ሃገራት ትብብር በእጅጉ ሊጠናከር ችሏል (Dereje 1993:53)::

የኢትዮጵያን በኮሪያ ጦርነት መሳተፍ ተከትሎ ሃገሪቱ ከተባበሩት መንግስታት ጋር የነበራት ግንኙነት በእጅጉ የተጠናከረ ሲሆን የተለያዩ የድርጅቱ ተቋማትም የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ ማድረጋቸውን ደረጀ ጠቅሷል::

> The year 1951 was a landmark for Ethiopia to receive valuable support from the United Nations Organization. In 1951 and 1952 the food and agriculture Organization [FAO], the World Health Organization [WHO] and the United Nations Childrens' Fund [UNICEF] entered Ethiopia with their experts and



IES LIBRARY ADDIS

> technical units. In general from 1951 on United Nations Organization launched a development programm in Ethiopia, which costs in millions dollar including expert assignments and recruiting Ethiopian service men. (1993:53)

ከዚህ በተጨማሪ የኢትዮጵያ በኮሪያ ጦርነት መሳተፍ በሩቅ ምስራቅ ከምትገኘዋ ጃፓን ጋር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ለመመስረት ምክንያት ሆኗል:: በጦርነቱ ወቅት ቶኪዮ የነበረው የአገናኝ መኮንኖች ቢሮ ወደ ኤምባሲነት አድጓል:: ደቡብ ኮሪያን በተመለከተም ዘመቻው ከኢትዮጵያ ጋር «በደም የተሳሰረ ግንኙነት» እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል (ቃኘው፣ 1997፣ 23):: ኢ.ኤ.አ በ1963 ዓ.ም ደቡብ ኮሪያ ኤምባሲዋን በአዲስ አበባ የከፈተች ሲሆን ሁለት የኢትዮጵያ መሪዎችም ሃገሪቱን ጎብኝተዋል:: ይኸውም ኢ.ኤ.አ በ1968 ዓ.ም ቀዳማዊ ሐይለ ስላሴና ኢ.ኤ.አ በ2000 ዓ.ም ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ደቡብ ኮሪያን ጎብኝተዋል:: ሁለቱም መሪዎች በጉብኝታቸው ወቅት በኮሪያ ጦርነት ለተሰዉ የኢትዮጵያ ወታደሮች መታሰቢያ በቹን ቾን ከተማ በቆመው ሀውልት ስር የአበባ ጉንጉን አኑረዋል (ቃኘው፣ 1994፣ 1998)::

በደቡብ ኮሪያውያን በኩልም የቹን ቾን ከተማ ከንቲባ አዲስ አበባን የጎበኙበትና የኢትዮጵያ ወዳጅ ደቡብ ኮሪያውያን ሙዚየምና መታሰቢያ ሀውልት አስገንብተው ለኢትዮጵያ ኮሪያ ዘማቾች ማህበር አስረክበዋል (ቃኘው፣ 1994፣ 1998)::

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ በኮሪያ ጦርነት መሳተፍ ከተለያዩ ሃገራትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ለመፍጠር አስችሏታል:: እነዚህ ግንኙነቶችም ለሀገሪቱ የተለያዩ አስተዋጽኦዎችን አበርክተዋል:: ይህ ደግሞ በኮሪያ ጦርነት የተሳተፉ ወታደሮችን ሃገራዊ ውለታ እንዳይዘነጋ የሚያደርግ ነው::

### 2.3.2 ባህላዊ አሻራ

የኢትዮጵያ በኮሪያ ጦርነት መሳተፍ ከሌሎች ሃገራት ጋር የነበራትን ዲፕሎማሲያዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ከማጠናከር በተጨማሪ የተወሰኑ ባህላዊ አሻራዎችን አሳርፏል:: ከእነዚህ አሻራዎች ውስጥ የሚጠቀሱት ሙዚቃና ስነጽሁፍ ናቸው:: ሙዚቃውን በተመለከተ ኮሪያ ደርሰው የተመለሱ ወታደሮች የሩቅ ምስራቅ ሙዚቃዎችን ያስተዋወቁበትና በህዝቡም ዘንድ ሰፊ ተደማጭነትን ያገኙበት አጋጣሚ ተጠቃሽ ነው (አምሳ አለቃ ተስፋዬ ሳህሉ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 2፣ ስክርብ ገጽ 7-12፣ ህዳር 21፣ 2000 ዓ.ም"):: በኮሪያ ቆይታቸው የሙዚቃ ችሎታቸውን በእጅጉ ያሳደጉና ወደ ሀገር ቤት ተመልሰው በሙዚቃ ባንዶች ውስጥ እስከመጫወት የደረሱ ዘማቾችም ነበሩ:: ከእነዚህ ውስጥ ተስፋዬ ሳህሉና ካሳ ተሰማ ተጠቃሽ ናቸው (አምሳ አለቃ ተስፋዬ ሳህሉ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 2፣ ስክርብ ገጽ 8፣ ህዳር 21፣ 2000 ዓ.ም"):: 

ከዚህም ሌላ የኮሪያ ዘመቻን መሰረት አድርገው የተፈጠሩ ሙዚቃዎች ያሉ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ የካሳ ተሰማ «እልም አለ ባቡሩ» እና የጥላሁን ገሰሰ «እሩቅ ምስራቅ ሳለሁ



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ጃፓንዋን ወድጄ» ዘፈኖች ተጠቃሽ ናቸው (ዳዊት፣1998፣131፤ ቃኘው፣1988፣20-21)። የኮሪያ ዘመቻ በኢትዮጵያ ሙዚቃ ላይ ስላለው አሻራ በአማካሪዬ አስታዋሽነት መረጃ እንዲሰጡኝ የቀረብኳቸው አምሳ አለቃ ተስፋዬ ሳህሉ ወይም በተለምዶ አበባ ተስፋዬ ቢያንስ በድህረ ምረቃ ደረጃ የሚሰራ የተረክ ጥናት የሚጋብዙ «ስታዬሊሽ» ተራኪ መሆናቸውን አስተውያለሁ።

የኮሪያ ዘመቻ ካሳረፋቸው ባህላዊ አሻራዎች ውስጥ ሊጠቀሱ የሚችሉ ቢያንስ አንድ ልቦለድና የግጥም መድበል አሉ። ልቦለዱ ታገል ሰይፉ በ1990 ዓ.ም ያሳተመው ሃምሳ አለቃ ገብሩ ቢሆንም ቢሆንም መጽሐፍ ሲሆን የግጥም መድበሉም በ1943 ዓ.ም ቃኘው ሻለቃ የእሳቱ ላንቃ በሚል ርእስ ቢያዝን መኮንን ለአንባቢ ያቀረበው ናቸው። የታገል ሰይፉ መጽሀፍ አቀንቃኝ ዋና ገጸባህሪ በኮሪያ ጦርነት ተሳታፊ የነበሩ ሲሆን የኮሪያ ዘማችነታቸው ከሌሎች ገጸባህሪያት ጋር በሚያደርጓቸው ምልልሶች፣ ግለወጎችና ገለጻዎች ተንጸባርቋል። የልቦለዱ ታሪክ ግን ከኮሪያ ዘመቻ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌለውና በአቀንቃኝ ገጸባህሪው ከኮሪያ ዘመቻ መልስ በነበረ የፈጠራ ታሪክ ላይ የተመሰረተ ነው።

የቢያዝን መኮንን ግጥሞች በተመለከተ በኢትዮጵያውያን ወታደሮች የኮሪያ ዘመቻ መሰረት ያደረጉና የዘማቾቹን ቁርጠኝነት፣ የአላማ ጽናትና ስኬታማ የተልእኮ አፈጻጸም የሚያወድሱ ናቸው። በመጨረሻም የኮሪያ ዘመቻ አሻራ በድርጅትና በሰፈር ስያሜ ላይ የሚታይ ሲሆን እነሱም አዲስ ከተማ የሚገኘው «ቃኘው ሻለቃ ሆቴል» እና የካ ክፍለ ከተማ የሚገኘው ኮሪያ ሠፈር (ቃኘው፣1987፣50) ተጠቃሽ ናቸው።

## 2.4 የግለተረክ ተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንኡስ ክፍል የግለተረክ ጥናት በአለምና በሃገራችን ያለው ገጽታ፣ በተለያዩ የትግል መድረኮች የተሳተፉ ግለሰቦች የግል ተሞክሮ በመጽሃፍና በቃለ መጠይቅ የማቅረብ ጥረቶችና ከኮሪያ ዘማቾች ጋር የተያያዙ ታሪክ ነክ ጽሁፎች በአጭሩ ይዳሰሳሉ።

ግለተረክ ራሱን እንደቻለ የተረክ ዘውግ ሳይቆጠርና በህይወት ታሪክ [life history] መልክ መሰብሰብ የጀመረው ከሃያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ አንስቶ ሲሆን ይኸውም በፎክሎሪስቶች፣ አንትሮፖሎጂስቶችና የባህል ጥናት ባለሙያዎች አማካይነት ነበር (Clements 1980:106-7)። ግለተረክን [personal experience narrative] የተረክ ዘውግ አድርጎ በመረዳትና በማጥናት ረገድ ቀዳሚው የስነልሳን ተመራማሪው ዊሊያም ላቦቭ (William Labov) ሲሆን በ1967 ዓ.ም ከጆሹአ ዋልቴዝኪ (Joshua Waltezky) ጋር መጥምረት በጻፉት መጣጥፍ የግለተረክን መዋቅር መርምረዋል (Bauman 1986:33)።

የፎክሎሪስቶችን ትኩረት ወደ ግለተረክ በመሳብ በኩል ደግሞ ሳንድራ እስታህል (Sandra Stahl) ከፍተኛ ሚና መጫወቷን ሪቻርድ ቦውማን (Richard Bouman) ጠቅሷል (1986:33)። ሳንድራ በግለተረክ ላይ በርካታ ጥናታዊ ጽሁፎችን ያቀረበች ሲሆን ከእነዚህ



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ውስጥ በአንደኛው ግለተረክ የሃገረሰባዊ ተረክ [folk narrative] አንድ ቅርጽ መሆኑን ለማስረገጥ ሞክራለች (Stahl 1977:9-30)::

ኢሊዮት ኦሪንግ (Elliot Oring) ግለተረክ ከሃገረሰባዊ ተረክ ዘውጎች ውስጥ አንዱ መሆኑን በጠቀሰበት ጽሁፉ ውስጥ እስከ 1970ዎቹ ድረስ በግለተረክ ላይ ያተኮረ ፎክሎራዊ ጥናት አለመካሄዱን አስረድቷል (in Jones,ed 1994:123):: ከ1970ዎቹ በኋላ ግን ግለተረክ የፎክሎሪስቶችን ትኩረት በአስደናቂ ሁኔታ ሊያገኝ ችሏል (Clements 1980:106):: ለግለተረክ አካዳሚያዊ ትኩረት ማግኘት የስመጥሩ ፎክሎሪስት ሪቻርድ ዶርሰን አስተዋጽኦ አለበት::

> In 1970 article he [Dorson] told folklorists to cast aside worries over whether the personal history is a traditional oral genre, and urged them to collect the thousands of sagas created from life experiences that deserve, indeed cry for, recording. (Titon 1980:276) [ሪቻርድ ዶርሰን] በ1970 በጻፈው መጣጥፍ ውስጥ ፎክሎሪስቶች ግለታሪክ የስንቃል ዘውግ ህልውና ያለው ወይም የሌለው ስለመሆኑ ያላቸውን ጭንቀት ወደ ጎን ትተው ከግል ገጠመኝ የመነጩትንና መሰነድ የሚገባቸውን እልፍ አእላፍ ገድሎች እንዲሰበስቡ አስከመማጸን ደርሶ ነበር::

የዶርሰንን ተማጽኖ ተከትሎ የተፈጠረ በሚመስል መነቃቃት ከ1970ዎቹ ወዲህ ፎክሎሪስቶች ከጭብጥ፣ ከመዋቅር፣ ከስልት፣ ከፋይዳና ከታዳሚ ጋና አንጻሮች ግለተረክን ማጥናት ጀመሩ (Clements 1980:107):: ግለተረክ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍተኛ አካዳሚያዊ ትኩረትን እያገኘ የመጣው ከፎክሎርና ስነልሳን በተጨማሪ በሶሲዮሎጂ፣ በሳይኮሎጂ፣ በታሪክ፣ በህክምናና በህግ የጥናት ዘርፎች ጭምር ነው (Bauman 1986:33; May 2007:1; Squire 2007:92)::

ግለተረክ በተለያዩና በተራራቁ አካዳሚያዊ ዘርፎች ውስጥ የሚጠናው ተመሳሳይ ድፍየና ኖሮት ሳይሆን ሁሉም አጥኚዎች የሚጋሯቸውን መሰረታዊ ጠባያት ታሳቢ በማድረግ ነው (May 2007:1):: ከእነኚህ የግለተረክ ጠባያት ውስጥ ዋነኛው ቅደም ተከተላዊ ትስስሮሽ ያላቸው ሁነቶች (events) ዘገባ መሆኑ ነው (Bauman 1986:45; Dijk 1976a:550; Gilbert 2002:227; Labov 2006:37; Oring 1986:121; Squire 2007:94):: አንድ ግለተረክ የተረክነት ህልውና ይኖረው ዘንድ ቢያንስ ሁለት ያህል ቅደም ተከተላዊ ትስስሮሽ ያላቸው ነጠላ ሁነቶች ይኖሩት ዘንድ ግድ ነው (Labov 2006:37; Squire 2007:94)::

በሌላ አገላለጽ ነጠላ ሁነቶቹ «እና» ወይንም «ከዚያም» በሚሉ መስተጻምራዊ ሚና ባላቸው ቃላት መተሳሰር ይገባቸዋል።

የተለያዩ የስነተረክ አጥኚዎች አንድ ተረክ ሊያካትታቸው ይገባል የሚሏቸው የተለያዩ መሰረታዊ ገጽታዎች አሉ። እነዚህ ገጽታዎች ከአጥኚዎቹ የትኩረት ነጥብ መለያየት አንጻር በርካታ መሆናቸውን ጊልበርት ይጠቅሳል።

> On one extreme are those who see a narrative as including almost any form of ordered communication...Most typical are those who require that a particular set of elements be present. These include a sequence that is temporally ordered, with a beginning, a middle, and an end; events; characters; stance taking, or perspective; intentionality, that is motivation of characters; an underlying time frame; thematic organization, entrance and exit talk; and metacommentary. (Gilbert 2002:227) በአንደኛው ጽንፍ በኩል ተረክ ማለት ማንኛውንም አይነት ትርጉም ሰጪ ስርአታዊ ተግባቦት ያካትታል የሚሉ ይገኛሉ። በሁለተኛው ጽንፍ ውስጥ የሚገኙት አጥኚዎች ደግሞ ለተረክ ድፍየና መሟላት የሚገባቸውን ጉዳዮች መሰረት የሚያደርጉ ሲሆን እነዚህም በጊዜ ቅደም ተከተል የተዋቀሩ ተለጣጣቂነት ማለትም መግቢያ፤ መሀከልና መጨረሻ፤ ሁነቶች፤ ገጸባህሪያት፤ የተረክ አንጻር፤ የገጸባህሪያት ድርጊት የመፈጸም ተነሳሽነት ወይም ውሳኔ፤ የጊዜ ቢጋር፤ የጭብጥ አደረጃጀት፤ የተረክ አጀማመርና አጨራረስ፤ እንዲሁም በትረካ ወቅት ከተተራኪ ጊዜው ወጥቶ ወደ ትረካ ክዋኔ ጊዜው በመግባት የሚሰጣቸው ገለጻዎች ናቸው።

በዚህ ጥናት ውስጥ አንድ ተረክ ሊያካትታቸው ይገባል ከሚባሉት የተለያዩ መሰረታዊ ገጽታዎች ውስጥ ቅደም ተከተላዊ ትስስሮሽ ያላቸውን ሁነቶች መዘገብ አጽንኦት ይሰጠዋል። ግለተረክ የተረክ አንድ ቅርጽ በመሆኑ (Bauman 1986:54; Oring 1986:121-123) እና ማንኛውም ግለተረክ ተረክ ማለት በእውን ተከስተዋል ተብለው የሚታመኑ ተሞክሮዎች ቅደም ተከተላዊነታቸውን ጠብቀው በቃል የሚዘገቡበት ስልት ነው (Oring 1986:121) የሚለውን ድፍየና የሚያሟላ ስለሆነ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ሁለቱን ቃላት በተተካኪነት የመጠቀም አጋጣሚ ይኖራል።

በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ዝግጅት ወቅት የግለተረክ ጥናት በሃገራችን ያለበትን ሁኔታ ለመቃኘት ጥረት ተደርጓል። በዚህም ወቅት በኢትዮጵያ ቋንቋና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት የቅድመና ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ተማሪዎች ለስነቃል ጥናት ከፍተኛ ዝንባሌ ያላቸው መሆኑን በሚጠቁም መልኩ በተለያዩ የስነቃል ዘውጎች ላይ እጅግ በርካታ ጥናቶች ማካሄዳቸውን ለመገንዘብ ተችሏል (Fekade 2001:43-85)። ይህም ሆኖ በግለተረክ ላይ የተካሄደ ጥናት ግን የለም። ይህ ሁኔታ ለግለተረክ የተሠጠው አካዳሚያዊ ትኩረት ዝቅተኛ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ግለተረክ ለጥናት ያለው ምቹነት ከሌሎች የስነቃል ቅርጾች ጋር ሲነጻጸር እጅግ ምቹ መሆኑን የስነቃል አጥኚዎች ያስረዳሉ (Clements 1980:107-8)። ግለተረክ ለተጠኚነት ካሉት ምቹ ገጽታዎች ውስጥ በየትኛውም ግለሰብ የሚከወን መሆኑ፣ የሚተርካቸው ርእሰ ጉዳዮች ባእድ አለመሆንና መስክ ወጥቶ ለመሰብሰብም የማይቸግር መሆኑ ይጠቀሳሉ። ስለዚህም ቢያንስ ከላይ በተጠቀሱትን ምቹ ሁኔታዎች ከግምት በማስገባት የቅድመና ድህረ ምረቃ ጥናታዊ ጽሁፎች በግለተረክ ላይ እንዲሰሩ ማበረታት ተገቢ ነው።

ከጥናቴ ጋር በተገናኘ ተዛማጅ ስራዎችን በምፈልግበት ወቅት ያስተዋልኩት ሌላው ጉዳይ የፎክሎር ተማሪዎች በወታደሩ የህብረተሰብ ክፍል ትኩረታቸው ያልተሳበ መሆኑን ነው። በወታደሮች ላይ የአተኮረ ምንም አይነት ጥናት አላጋጠመኝም። እርግጥ ነው ገፋ አድርጎ የሄደበት ተማሪ ባይኖር ነው እንጂ የክፍሉ ተማሪዎች ወታደሮችን ለጥናታቸው ታሳቢ እንዲያደርጉ የተጠቆመበት አጋጣሚ ግን አለ (ፈቃደ፣1991፣121)። ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል ጋር በማስተያየት ወታደሮች ለተረኮች መፍለቂያነትና ተስተላልፎ ከፍተኛ ምቹነት እንዳላቸው ሃሮልድ ማርከስ (Harold Marcus) የተባለው ፎክሎሪስት እንዲህ ያስረዳል።

> Whether they are from the same branch of the service, the same subspeciality, or the same company, members of the armed services recycle the repertoire of their immediate predecessors and invent new stories to fit their immediate circumstances. (Burke 2002:4) ከተመሳሳይ የስራ መስክ፣ በተመሳሳይ የስራ ምድብ ወይም አንድ ምድብ ውስጥ የሚገኙ ወታደሮች ከእነሱ በፊት የነበሩትን የሙያ አቻዎቻቸውን ፈጠራ የመድገምና ከራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚሄዱ አዳዲስ ስነቃሎችን የመፍጠር ጠባይ አላቸው።

በዚህ ክፍተት ላይ ከአማካሪዬ ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ ጋር ታህሳስ 11፣ 2000 ዓ.ም ስንወያይ ስለወታደሮች የተሰበሰበና ለህትመት ያልበቃ ፎክሎር በእጃቸው እንደሚገኝ ገልጸውልኛል። በአጠቃላይ በግለተረክ ዘውግ ላይ የተመሰረተ ጥናት አላጋጠመኝም።

በሌላ በኩል ከጦርነት ጋር በተያያዘ ግለሰቦች የፈጸሟቸውን ድርጊቶች በጽሁፍ ቅርጸ ለማቆየት የተደረጉ ጥረቶች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ የሚጠቀሰው በአምስት ተከታታይ ቅጾች የቀረበው ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ የሚባለው መጽሃፍ ነው። መጽሃፉ የተዘጋጀው «በኢህአዴግ በኢህአፓና በሌሎችም የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ ታቅፈው ሲታገሉ ድንቅ ገድል የፈጸሙ ታጋዮችን ታሪክ ቆፍረን ማውጣት ይገባናል።» በሚል ተነሳሽነት መሆኑን አዘጋጁ አካል በቅጽ ሁለት መግቢያ ላይ ገልጿል (1990)።

በዚህም መሰረት መጽሃፉ በአምስቱ ቅጾቹ በተማሪዎች ንትናቱ፣ በአርሶ አደሮች አመጽ፣ በፖለቲካ ድርጅቶች በተለይም በኢህአፓ፣ በኢህደኢንና በህወሃት ውስጥ ጉልህ ቦታ የነበራቸውን ግለሰቦች ታሪክ በቃለመጠይቅና በጽሁፍ መረጃ ምንጮች በማስደገፍ አቅርቧል:: የመጽሃፉ አቀራረብ በህይወት ስለሌሉ ግለሰቦች፣ ስለህዝባዊ አመጾችና ልዩ የትግል አጋጣሚዎች በሌሎች ሰዎች የተዘጋጁ ጽሁፎችንና በህይወት ያሉት ደግሞ ስለራሳቸው የጻፉትን ያካተተ ነው:: መጽሃፉ የሰዎች ንግግሮችና አድራጎቶች የመረሳት እድል ያላቸው መሆኑን በተረዳ መንፈስ መጻፉ ጠንካራ ጎኑ ነው:: መጽሃፉ ቃለ መጠይቆችን በመረጃ ምንጭነት የተገለገለ በመሆኑ በአጼውና በደርግ ስርአት የተካሄዱትን ተቃውሞዎችና የትጥቅ ትግሎች መሰረት በአደረጉ ግለተረኮች ላይ ጥናት ለሚያካሂድ አጥኚ የመረጃ ምንጭ በመሆን ሊያገለግሉ ይችላሉ:: የዚህ ጥናት አትራቢ ለመጽሃፉ ዝግጅት የዋሉት ቃለ መጠይቆች በመዘክር ውስጥ እንደተቀመጡ የሚያምን ሲሆን ያልተቀመጡ ከሆኑ የመጽሃፉን አዘጋጅ በማግኘት መዘክር የሚገቡበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ጥረት ያደርጋል::

ከላይ ከተጠቀሰው መጽሃፍ በተጨማሪ ግለሰቦች በጦር ሜዳ ውሏቸው የፈጸሟቸውንና የሚያስታውሷቸውን ገጠመኞች በቴሌቪዥን የተረከቡት የቅርብ አጋጣሚ አለ:: ይኸውም በዘንድሮው የግንቦት 20 በአል ዋዜማ የኢህአዴግ ወታደሮች ከደርግ ወታደሮች ጋር ያካሄዱትን ውጊያ መሰረት አድርገው በቴሌቪዥን በተከታታይ ሲቀርቡ የነበሩት ቃለ መጠይቆች ናቸው:: እነዚህ ቃለ መጠይቆች በጦር ሜዳ የተፈጸሙ ሁነቶችን የሚተርኩ ግለተረኮች ያሏቸው በመሆኑ የስነቃል ተማሪዎችን ትኩረት የመሳብ አቅም አላቸው::

ከእነዚህ ከትግል ጋር ተያያዥነት ካላቸው ስራዎች በተጨማሪ ከጥቂት አመታት ወዲህ በተለያየ የሙያ ዘርፍ የተሰማሩ ግለሰቦች የግል ተሞክሯቸውን በመጽሃፍ መልክ ቀርሶ የማቆየት ጥረቶች ሲያካሂዱ ይታያል:: እነዚህ ጥረቶች ግለሰቦች የግል ገጠመኞቻቸውን በተለያዩ መቅረጫ መሳሪያዎች እገዛ የመቅረስ ዝንባሌ የሚያሳድሩበት ወቅት እሩቅ አለመሆኑን የሚጠቁም ነው:: ይህ ደግሞ በተራው ለስነቃል ተማሪዎች ስራ የመረጃ ምንጭ በመሆን የሚያገለግል ይሆናል::

የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ትኩረት ከሆኑት የኮሪያ ዘማቾች ጋር በተያያዘ ሶስት ታሪክ-ነክ ጽሁፎች አሉ:: የመጀመሪያው Kimon Skordiles የሚባል ግሪካዊ የጦር ሜዳ ዘጋቢ በ1954 ዓ.ም Kagnew: The History of the Ethiopian Fighters in Korea በሚል ያዘጋጀው መጽሐፍ ነው:: መጽሃፉ ሶስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን በክፍል ሁለት ውስጥ አምስቱም ቃኘው ሻለቆች በኮሪያ ጦርነት የፈጸሙትን ተግባር ያስረዳል:: ደራሲው መጽሃፉን የጻፈው በሰነዶች ላይ ተመስርቶ ሲሆን ይህም የመጽሃፉን መረጃዎች ተአማኒ እንደሚያደርጋቸው በመግቢያው ላይ እንዲህ በማለት ገልጿል:: "The information which I here present originates from official sources as well as from press information, and therefore forms a reliable, graphic account." (1954)



ILS LIBRARY

በእርግጥም መጽሃፉ በኢትዮጵያ የኮሪያ ጦርነት ተሳትፎ ላይ ያተኮረና ጠቃሚ መረጃዎችን የያዘ ብቸኛ የህትመት ውጤት ነው::

በሌላ በኩል መጽሃፉ ከባለታሪኮቹ አንጻር ቅሬታ ያሳደረ ለመሆኑ ፍንጭ አለ:: ይኸውም መጽሃፉ በኮሪያ ጦርነት ላይ የፈጸሙትን አስደናቂ ተግባር ከገለጻላቸው ዘማቾች ውስጥ አንዱ ብርጋዲየር ጀኔራል ደስታ ገመዳ ናቸው (Skordilcs 1950:56):: እኚህ ጀኔራል በኮሪያ ጦርነት ስለፈጸሙት ተግባር እስኮርዲሊስ የጻፈበትን ሁኔታ «ጥራዝ ነጠቅ» በማለት ተችተዋል (ብርጋዲየር ጀኔራል ደስታ ገመዳ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 12፣ ነሐሴ 23፣ 1999 ዓ.ም):: ይህ ቅሬታ ደራሲው በካልአይ የመረጃ ምንጭ ላይ በብቸኝነት መመስረቱና ለቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ትኩረት አለመስጠቱ የፈጠረው እንደሆነ መገመት ይቻላል:: በመሆኑም በቅርበት ለመከታተል አስቸጋሪ የሚመስለ የጦርነት ሁነቶችን የተመለከተ መጽሃፍ በማዘጋጀት ሂደት የሁነቱን ተሳታፊዎች በመረጃ ምንጭነት ማካተት ተገቢ ነው:: ከዚህም በተጨማሪ ካልአይ የመረጃ ምንጭን እንደብቸኛ ተአማኒ የመረጃ ምንጭ መውሰድ ክፍተት የሚፈጥር መሆኑን የወደፊት ጸሃፊዎች መገንዘብ ይኖርባቸዋል::

የኢትዮጵያን የኮሪያ ጦርነት ተሳትፎ የተመለከተ መረጃ ያለው ሌላው ስራ ዳምጤ አስማኸኝ በ1950 ዓ.ም ያሳተመው ጠቅልና ሰራዊቱ የተባለው መጽሃፍ ነው:: ይህ መጽሃፍ ሶስት ክፍሎች ያሉት ትልቅ ጥራዝ ሲሆን ስለክብር ዘበኛ አመሰራረትና በወቅቱ ስለነበረበት ደረጃ በዝርዝር የሚያትት ነው:: በመጽሃፉ ክፍል ሶስት ውስጥ ከሚገኙ ሶስት ንኡስ ክፍሎች አንደኛው «የቃኘው ሻለቃ በሩቅ ምስራቅ ኮሪያ የፈጸመው የጀግንነት ታሪክ» የሚል ሲሆን በውስጡም አምስቱ ቃኘው ሻለቆች በኮሪያ ጦርነት የነበራቸውን ተሳትፎ የተመለከቱ መረጃዎች በስእል አስደግፎ አቅርቧል:: ይህ መጽሃፍ ስለኢትዮጵያውያን የኮሪያ ዘመቻ የመረጃ ምንጭ በመሆን ሊያገለግል ይችላል::

በኢትዮጵያ የኮሪያ ጦርነት ተሳትፎ ላይ መሰረት በማድረግ ከተሰራው ጥናታዊ ጽሁፍ ደረጀ ተክሌ በ1993 ዓ.ም "The History of Qagnew Battalions in Korea" በሚል ርእስ ለታሪክ ክፍለ ትምህርት ያቀረበው ዲግሪ ነው:: የጥናቱ ዓላማ በኮሪያ ጦርነት በአምስት ዙር የተሳተፈውን የኢትዮጵያ ሰራዊት በጦርነቱ ወቅት የተጫወተውን ሚና መፈተሽ ነው:: ይህ ጥናት የኮሪያ ዘማቾችን ቃለ መጠይቅ በማድረግ የተሰራ መሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር ቢያመሳስለውም ከጥናቱ ዓላማና በተለያዩ ዙሮች ወደ ኮሪያ የሄዱትን ዘማቾች ሳይነጥል ያቀፈ መሆኑ ከእኔ ይለየዋል::

በአጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ የኮሪያ ጦርነትን አጭር ታሪክ፣ የኢትዮጵያን ተሳትፎና የዘመቻውን አሻራዎች የተመለከቱ መረጃዎች የሚቀርቡ ሲሆን የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት በተመለከተም ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸውን ጽሁፎች ለመዳሰስ ተሞክሯል:: ቀጥሎ ደግሞ የግለተረክን ትውራዊ ዳራ የተመለከተው ምእራፍ ይቀርባል::



ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIV

## 3. የግለተረክ ትውራዊ ዳራ (Theoretical background)

በዚህ ምዕራፍ ስለ ግለተረክ ድፍየና፣ መዋቅር፣ ጭብጥ፣ ተተራኪነትና ክልሰፋ የተመለከቱ ትውራዊ ዳራዎች ይቀርባሉ፡፡

### 3.1 የግለተረክ ድፍየና (Definition)

ግለተረክ የተለያዩ የጥናት መስኮችን ትኩረት የሳበ መሆኑን በምእራፍ ሁለት ተመልክተናል፡፡ በሁሉም መስኮች ውስጥ የሚገኙ አጥኚዎችን ሙሉ ተቀባይነት ያገኘ ድፍየና የሌለው መሆኑም ተጠቅሷል፡፡ ግለተረክ በተረክ አጥኚዎች ዘንድም ቢሆን ወጥ የሆነ ድፍየና የለውም (May 2003:9)፡፡ ነገር ግን ግለተረክ በተለያዩ የጥናት መስኮች ውስጥ የሚገኙ አጥኚዎች የሚጋሩት መሰረታዊ ጠባያት ያለው ሲሆን ይኸውም ቅደም ተከተላዊ ትስስሮሽ ያላቸው ሁነቶች ዘገባ የሚል ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥም ታሳቢ የሚደረገው የግለተረክ ድፍየና ቅደም ተከተላዊ ትስስሮሽ ያላቸው፣ በእውነታው አለም የተከሰቱ፣ የግል ገጠመኝ ሁነቶች ዘገባ የሚል ነው፡፡

### 3.2 የግለተረክ መዋቅር

ግለተረኮች ከሌላው የተረክ ዘውግ በተለየ መዋቅራዊ ገጽታዎች አሏቸው፡፡ እነዚህ መዋቅራዊ ገጽታዎች የግለተረክ መገለጫ ከመሆን ባለፈ ግለተረኮችን ለመደፍየንና ለመከልሰፍም የሚያገለግሉበት አጋጣሚ አለ (Robinson 1981:58)፡፡ በግለተረክ ጥናት ግንባር ቀደምት ተጠቃሽ የሆነው ላቦቭ እንደ ግለተረክ ስድስት ያህል መዋቅሮች እንዳሉት የሚገልጽ ሲሆን እነሱም አጠቃሎ፣ እውቅያ፣ ሴራ፣ ምዘና፣ ልቀትና ኮዳ ናቸው (Bauman 1986:33)፡፡ ይህ ሰው በግለተረክ ጥናት ከፊር ቀዳጆች ውስጥ የሚጠቀስ ሲሆን ለግለተረክ ጥናት የሚያገለግሉ ሜቶዶሎጂና ትውሮችን አበርክቷል (Robinson 1981:58; Squire 2005:94)፡፡ በግለተረክ ጥናት ሌላው ተጠቃሽ አጥኚ ቫን ዲይክ ሲሆን በቀጣዩ ክፍል የሚቀርበው የግለተረክ መዋቅር ማስተዋወቂያም በሁለቱ አጥኚዎች ትውሮች ላይ ይበልጡኑ የተመሰረተ ነው፡፡

እነዚህን የግለተረክ መዋቅሮች ምንነት ይበልጥ ለመረዳት እንዲያግዘን ኮርኒ ስኪውር የተባለች የስነተረክ አጥኚ አንድን ግለተረክ በመዋቅር ከፋፍላ ቀጥሎ በቀረበው መልክ አስቀምጣለች፡፡ ይህ ግለተረክ ቀጠሮ አርፍዶ በመጣ አንድ ግለሰብ የተተረከ ተደርጎ የሚታሰብ ነው፡፡

> I had a terrible time getting here. (abstract)
> I started out an hour ago, and I only live a couple of miles away. (orientation)
> I was standing at the bus stop for ages, and then when the first bus came it was full, and I had to wait another 20 minutes for the next one. (complicating action)

I was getting so worried; I really thought you'd be gone by the time I arrived. (evaluation)
Still, I got here in the end. (resolution)
I'll know to start earlier if we meet here again, though. (coda)
(Squire 2007: 94)

ይህ ግለተረክ የተከፋፈለበትን መዋቅሮች ልዩነትና ምንነት ቀጥሎ ከሚቀርበውና በስነተረክ ጥናት ለእያንዳንዱ መዋቅር የተሰጠውን ድፍየና ከሚያስረዳው ጽሁፍ ግንዛቤ እናገኛለን::

### 3.2.1 የአጠቃሎ መዋቅር (Abstract)

ግለተረክ ስድስት መዋቅሮች ሊኖሩት እንደሚችሉ ቀደም ተብሎ የተጠቀሰ ሲሆን የመጀመሪያው መዋቅር አጠቃሎ ይባላል:: "[abstract] describes what the story is about." (Squire 2007:94) አጠቃሎ አንድ ግለተረክ ስለምን ጉዳይ እንደሚተርክ በቁጥብ የሚገልጽ ነው:: የዚህ መዋቅር ፋይዳ አንድ ሊተረክ የተፈለገ ግለተረክ ስለ ምን እንደሚያወራ አስቀድሞ ለታዳሚው በማሳወቅ በታዳሚው ዘንድ ሙሉ ተረኩን የማዳመጥ ወይም የማንበብ ፍላጎትን መቀስቀስ ነው:: ታዳሚው በአጠቃሎ መዋቅር ውስጥ የቀረበለትን መረጃ ከአዳመጠ በኋላ ጉጉት ያደረበት ወይም ፈቃደኛ የሆነ መሆኑን ይገልጻል፤ አለበለዚያም ተረኩን ለመታደም የማይፈልግ መሆኑን ያሳውቃል (Dijk 1976:31):: በአጠቃሎ መዋቅር ውስጥ ሊቀርቡ ከሚችሉ ገለጻዎች ውስጥ የሚከተሉት በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ::

ምሳሌ፡- -ትናንት ስታዲየም ምን እንዳጋጠመኝ ነግሬሀለሁ?

-እሺ ተማሪዎች፤ ቀጥዬ ከሼፊልድ ዩኒቨርሲቲ ዘበኛ ጋር ስለተጋጨሁበት አጋጣሚ ላጫውታችሁ::

### 3.2.2 የእውቅያ መዋቅር (Orientation)

ከአጠቃሎ ቀጥሎ የሚመጣው የግለተረክ መዋቅር እውቅያ ይባላል:: "An orientation given information on the time, place of the events of a narrative, the identities of the participants and their initial behavior." (Labove 1997: 6) የአጠቃሎ መዋቅር ስለተረኩ መቼት፤ ስለገጸተረኮቹ ማንነትና ስለነበሩበት አውድ መረጃ የሚሰጥ ነው:: በዚህ መዋቅር ውስጥ የሚቀርበው መረጃ ለተረኩ ሴራ ፍሰት ቀጥተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት መሆን ይኖርበታል:: አንድ ተራኪ ስለምን ጉዳይ እንደሚተርክ ከገለጸ በኋላ የተረኩን መቼትና ገጸተረኮች ማንነት በቁጥብ ማስተዋወቅ አለበት (Dijk 1976:314):: አንድ ተራኪ የእውቅያ መረጃዎችን በማቀበል ሂደት ከተዘረከረከ «ወደ ነጥቡ ና» ወይም «ጅረ አሳጥረው» የሚል አስተያየት ከታዳሚው ሊሰነዘርበት ይችላል::

### 3.2.3 የሴራ መዋቅር (Complicating action)

አንድ ግለተረክ ስለምን እንደሚያወራ በአጠቃሎ መዋቅር፣ የተረኩን መቼትና የገጸተረኮች ማንነት ደግሞ በእውቅያ መዋቅሩ ከአስተዋወቀ በኋላ የሚመጣው ሶስተኛ መዋቅር ሴራ ይባላል:: "Complicating action is a sequential clause that reports a next event in response to a potential question 'and what happened [then]?'" (Labov 1997:6) የሴራ መዋቅር «ከዛስ በኋላ ምን ሆነ?» ለሚል የታዳሚ ጥያቄ መልስ የሚሆን ገለጻ የሚቀርብበት ነው:: ይህ ሁነት በእውቅያ መዋቅር የተገለጸውን ነባር አውድ የመለወጥ አቅም ያለው ሲሆን የተፈጠረውን ለውጥ ለመግለጽም «ድንገት»፣ «ሳይታሰብ»፣ «በዚህ መሀል» ወዘተ የሚሉ ተውሳከ ግሶችን ተራኪው ሊጠቀም ይችላል::

በሴራ መዋቅር ምክንያታዊ ትስስር ያላቸው ሁነቶች ገለጻ የሚቀርብ ሲሆን የሁነቶቹ በአንጻራዊነት በእውቅያ መዋቅር የተገለጸውን የመቼት፣ የገጸተረኮችና ገጸተረኮቹ የነበሩበትን አውድ የመለወጥ ወይም የማናጋት ብቃት አላቸው (Dijk 1976:316):: በሴራ መዋቅር የሚቀርበው የሁነቶች ገለጻ እውቅያ መዋቅር የተዋወቁት ገጸተረኮች አንዳች ፈተና ላይ ሲወድቁ ወይም ቁማታ ውስጥ ሲገቡ የሚያሳይ ነው:: ከእነዚህ ሁነቶች ውስጥም የግለተረኩ ቁንጮ ተተራኪ ሁነት ይገኝበታል::

በዚህ ጥናት ውስጥ የቁንጮ ተተራኪ ሁነት ምንነትን የምንረዳው በላቦቭ እይታነው:: "A most reportable event is the event that is less common than any other in the narrative and has the greatest effect upon the needs and desires of the participants in the narrative." (Labov 1997:10) ቁንጮ ተተራኪ ሁነት በአንድ ተረክ ውስጥ ከሚገኙ ሁነቶች ያነሰ አዘቦታዊነት ያለውና በገጸተረኮቹ ፍላጎትና መሻት ላይ የጎላ ተጽእኖ የሚያሳድር ሁነት ማለት ነው::

### 3.2.4 የልቀት መዋቅር (Resolution)

ከስድስት ያህል የግለተረክ መዋቅሮች ውስጥ አራተኛው ልቀት ይባላል:: "The resolution, is a set of descriptions of actions removing the obstacles interfering with the original actions or states of affairs or with the actions of resolving the predicament themselves." (Dijk 1971:331) የልቀት መዋቅር ነባር ድርጊቶችን ወይም ሁኔታዎችን ወይም ገጸተረኮች ከገቡበት ፈተና ለመውጣት የወሰዷቸውን የመፍትሄ እርምጃዎች የሚያውኩ እንቅፋቶች ስለተወገዱበት ሁኔታ ገለጻ የሚያቀርብ ነው:: ይህ መዋቅር ገጸተረኮች ከገቡበት ፈተና ሲወጡ የሚያሳይ የድርጊት ገለጻ የሚያቀርብ ሲሆን

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በሴራ መዋቅር ውስጥ የሚገኘውን ቁንጮ ተተራኪ ሁነት ተከትሎ ይመጣል (Labov 1997:16)::

በልቀት መዋቅር ውስጥ የሚጠበቅ አንድ ጉልህ ገጽታ አለ:: "In accounts of conflict between human actors, or the struggle of human actors against natural forces the narrator and the audience inevitably assign praise and blame to the actors for the actions involved." (Labov 1997:12) በሰዎች መካከል ወይም ሰዎች ከተፈጥሮ ሀይላት ጋር የገቡበትን ግጭት መሰረት በአደረገ ተረኮች ከዋኔ ወቶት ተራኪውና ታዳሚው በገጸተረኮቹ አድራጎት ላይ ተመስርተው ሙገሳ ወይንም ወቀሳ ማቅረባቸው አይቀሬ ነው::

### 3.2.5 የምዘና መዋቅር (Evaluation)

አንድ ግለተረክ ርእሰ ጉዳዩን ጠቁሞ፣ ዳራውን አስተዋውቆ፣ ሴራውን ተርኮና ልቀቱን አሳይቶ አያበቃም:: ይልቁንም የተረኩ ሁነቶች በተራኪው ላይ የፈጠሩትን ስሜት ማሳወቅ ይኖርበታል:: "Personal narrative must have a point; and that will typically be an explanation of the narrator's subjective reaction to the events described and specifications of the relationships of the events to significant values and beliefs." (Robinson 1981:63-64) ግለተረክ ምዘና ይኖረው ዘንድ ግድ ሲሆን ይህም አብዛኛውን ጊዜ ተራኪው ስለተተራኪ ሁነቶቹ ያለውን ግላዊ አመለካከትና ሁነቶቹ ከዋነኛ እሴቶችና እምነቶች ጋር ያላቸውን ቀጥተኛ ግንኙነት የሚያብራራ ነው::

አንድ ተራኪ ስለተረከው ሁነት ያለውን ምዘናዊ አጸፋ የሚጠቁሙ ገለጻዎች በመላው ተረክ ውስጥ የመሰራጨት ጠባይ ያላቸው ሲሆን በቀጥታ ወይንም በተዘዋዋሪ መንገድ ሊቀርቡ ይቻላሉ:: ለምሳሌ አንድ ተራኪ በትረካው መሃከል የሚቆዝምበት ወይንም በረጅሙ የሚተነፍስበት አጋጣሚ የተረኩ ሁነቶች የፈጠሩበትን ስሜት የሚጠቁሙ ናቸው (Squire 2007:94):: በምዘና መዋቅር ውስጥ ሊቀርቡ ከሚችሉ ገለጻዎች ውስጥ የሚከተለው በምሳሌነት ሊጠቀስ ይችላል::

- «መጥፎ ነበር በዕውነቱ:: እጅግ በጣም አሸባሪ ነበር» (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ ሚካኤል፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 3፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)::
- «ሙቹ ነበር» (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ ሚካኤል፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 6፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)::

### 3.2.6 የኮዳ መዋቅር (Coda)

ኮዳ መጨረሻ ላይ የሚመጣ የግለተረክ መዋቅር ነው። 'The end of a narrative is frequently signaled by a *coda*, a statement that returns the temporal setting to the present, precluding the question, "and what happened then?"' (Labov 2007:34) ተተራኪ ጊዜውን ወደ መተረኪያ ጊዜው በመመለስ በታዳሚ ሊነሱ የሚችሉትን «ከዚያስ ምን ሆነ?» የሚሉ ጥያቄዎች የሚያስቀር ገለጻ የሚያቀርብ ነው። በሌላ አባባል ተራኪው ከተረክ አለም ወደ እውነ አለም የሚመለስበት ነው። ከዚህም በተጨማሪ ኮዳ ተራኪው የመናገር ተራውን (turn taking) ለታዳሚው ማስተላለፉን የሚያውጅበት ነው (Robinson 1981:73)።

### 3.3 የግለተረክ ጭብጥ

በግለተረክ ላይ የሚካሄዱ ጥናቶች አንደኛው የትኩረት አትጣጫ በተረኮቹ ውስጥ የሚገኙትን ጭብጦች አውጥቶ ማሳየት ነው። ይህንን አትጣጫ ተከትሎ ስነተረካዊ ጥናት ማካሄድ እንደሚቻል የሚጠቁሙ ጽሁፎች አሉ (Clements 1980:107; Gilbert 2002:223-239; Jenkins and et al 2007; Ratner 2001; Squire 2007:92-93)። እነዚህንና ሌሎችንም ጥናታዊ ጽሁፎች በመመርመር ሂደት ጭብጥ የሚባለውን ጽንሰ ሃሳብ በወጉ የደፈየኑ አላጋጠሙም። ስለጭብጥ የተሻለ ማብራሪያ ሰጥቷል ብዬ የማስበው የዘሪሁን አስፋውን የስነጽሁፍ መሰረታውያን መጽሃፍ ነው። የዘሪሁን መጽሃፍ በስነጽሁፍ ላይ ይበልጥ ትኩረት ያደረገ ሲሆን ስነቃልንም ያካተተ ስራ ገለጻ አለው። በመጽሃፉ ውስጥ ፔሪን ሎረንስ የሰጠውን የጭብጥ ድፍየና የቀረበ ሲሆን ይኸውም «በልቦለዱ[ድ] ውስጥ ስለህይወት የተሰጡ ሃሳቦችን የሚቆጣጠር፣ ህልውናው በገሃድ ወይንም በውስጠ ታዋቂ የሆነ ማእከላዊ ትኩረት ነው።» የሚል ነው (1998:185)።

ዘሪሁን በመጽሃፉ ውስጥ ጭብጦች የተለያየ ደረጃ እንዳላቸውና አቢይና ንኡስ ተብለው እንደሚጠሩም አስረድቷል። አንዳንድ ሃያስያን የአንድን ስነጽሁፋዊ ስራ ትልቅነት የሚመዝኑት በያዘው ጭብጥ ዓይነት ላይ ተመስርተው መሆኑን ዘሪሁን ይጠቅሳል። በሃያስያኑ እይታ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው የጭብጥ አይነት የሰውን መሰረታዊ ባህርያት እሚያንጸባርቅ፣ ሰው ከተፈጥሮና ከማህበራዊ አካባቢው ያለውን ግንኙነት እሚነካ፣ የሰው ልጅን የአኗኗር ስርአትና ለመኖር ሲል የሚፈጥራቸውን አይቀሬ ግንኙነቶች የሚጠቅስ ሲሆን ነው (1998:185)። ዘሪሁን ያነሳው ሌላው ቁምነገር ከአንድ ጥበባዊ ስራ ውስጥ ጭብጥን ማውጣት አስቸጋሪ ነው ይላል። አስቸጋሪነቱም «በአንድ ቦታ ወይንም አንቀጽና ገጽ ላይ በቁሙ ፈጦ የሚገኝ ሳይሆን ከጠቅላላው ታሪክ ተጨሕምቆ ወይም ተፈልቅቆ የሚወጣ» በመሆኑ ነው ብሏል (1998:189)። ይህም ሆኖ ጭብጥን በማውጣት ሂደት ከልቦለዳዊው



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

አለም በተጨማሪ በእውኑ ዓለም ባለው ገጠመኝና አስተሳሰብ ላይም ማተኮር ተገቢ መሆኑን ጸሃፊው ያስገነዝባል::

ግለተረክን ታሳቢ አድርጎ የቀረበ ጽሁፍ ጭብጥን ለማውጣት በተለያዩ ነገሮች ላይ ማትኮር ተገቢ መሆኑን ይመክራል:: "We must be concerned not only with what was said but also with what was presupposed, implied, suggested, or conveyed by what was said" (Ratner 2001:3) የአንድን ተረክ ማእከላዊ ጭብጥ በማውጣት ሂደት በቀጥታ ከተገለጸው ጉዳይ እኩል ታሳቢ በተደረጉ ሃሳቦች፣ አንድምታዎችና ጥቆማዎች ላይ ትኩረት ማድረግ ተገቢ መሆኑ ተገልጾ ይገኛል::

በአጠቃላይ በዚህ ክፍል የጭብጥን ድፍየና፣ ከአንድ ልቦለድም ሆነ ግለተረክ ውስጥ ጭብጥን ማውጣት ያለውን አስቸጋሪነት፣ እንዲሁም ጭብጥን በማውጣት ሂደት ሊተኮርባቸው የሚገቡ ነጥቦችን በአጭሩ ተመልክተናል:: የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ አንደኛው የትንታኔ ትኩረት ከኑሪያ ዘማቾች በተሰበሰቡ ግለተረኮች ውስጥ አጥኚው ያስተዋላቸውን አበይት ጭብጦች መተንተን ነው:: ትንታኔው የተካሄደውም ጭብጥ ማለት በእያንዳንዱ ግለተረክ ውስጥ የሚገኙት አቀንቃኝ ገጸተረኮች ከሌሎች ገጸተረኮች እንዲሁም ከተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ አካባቢያቸው ጋር ያላቸውን መስተጋብር አስመልክቶ በቀጥታ ወይንም በተዘዋዋሪ ገጸተረኮቹ የሰነዘሯቸውን ወይንም አጥኚው «ኢንፈር» ያደረጋቸውን ድምዳሚዎች የሚገልጽ ጽንሰ ሃሳብ ነው:: ከዚህ ለወቅታዊ አገልግሎት ብቻ ታሳቢ ከሆነ የጭብጥ ብያኔ ጋር ተደጋጋፊነት ያለው ብያኔ የሚከተለው ነው::

> [Theme is] A central message or insight into life revealed through the literary work. It's not a condensed summary of the plot. Instead, it is a generalization about people or life about that is communicated through the literary work. (www.teacherslounge.editme.com) ጭብጥ ማለት በአንድ ጥበባዊ ስራ ውስጥ ስለተገለጸ ሕይወት የሚናገር ማእከላዊ መልእክት ወይንም አስተውሎት ነው:: ጭብጥ በአጭሩ የቀረበ ሴራ ሳይሆን በኪነጥበባዊ ስራው ውስጥ ስለሚገኙት ሰዎችና የኑሮ መልክ ያለው አጠቃላይ ድምዳሜ ነው::

### 3.4 ተተራኪነት (Tellability)

የተረክን ድፍየና በተመለከተ በስነቃላዊውም ሆነ በስነጽሁፉ መስክ በሚገኙ ምሁራን ዘንድ ቅደም ተከተላዊ ትስስር ያላቸው ሁነቶች ዘገባነቱ ጉልህ ባህርይው ተደርጎ እንደሚወሰድ ምእራፍ ሁለት ውስጥ መጠቀሱ ይታወሳል:: ግለተረክም ቢሆን በዚህ መሰረታዊ ባህርይ ላይ የሚተርከው ርእሰ ጉዳይ አይነት በዘርፉ አጥኚዎች ዘንድ ትኩረት

የሚሰጠው ነው:: በዚህም መሰረት በርካታ የተረክ ምሁራን የግለተረክን ርእስ ጉዳይ አይነት በተመለከተ አስደናቂ፣ አስገራሚ ወይንም ያልተለመደ መሆን እንዳለበት ይጠቅሳሉ (Bauman 1986:20, Dijk 1976:554; Robinson 1981:59):: ለምሳሌ ቫን ዲይክ በዚህ ጉዳይ ላይ እንዲህ ይላል::

> A narration; i.e; the act of uttering a narrative discourse; is an appropriate speech act if the actions or events told about are more or less spectacular or if the narrative discourse is itself spectacular. This means that the events do not occur in most normal possible worlds. (Dijk 1976:554) አንድ ትረካ ወይም የተረክ ክዋኔ ተገቢ የንግግር ድርጊት የሚባለው ተተራኪ ሁነቶቹ በአንጻራዊነት አስደናቂ ሲሆኑ ወይም የተረኩ ክዋኔ ራሱ ሳቢነት ሲኖረው ነው:: ይህም ማለት ሁነቶቹ በለት ተለት ህይወት የማያጋጥሙ ናቸው::

ለግለተረክ ርእስ ጉዳይነት ብቃት አላቸው ተብለው ከተጠቀሱ ሁነቶች ውስጥ ሞትና ለሞት የመዳረግ ብቃት ያላቸው አደጋዎች ተጠቃሽ ናቸው (Labov 2007:5):: ኮርኒ ስኪውር በበኩሏም የኤች.አይ.ቪ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ በሚገኝ ደቡብ አፍሪካውያን ላይ የአካሄደችውን የግለተረክ ጥናት መሰረት በማድረግ ኤች.አይ.ቪ ፖዘቲቭ ወይንም ኔጌቲቭ መሆን ለግለተረክ ብቁ ከሆኑ ርእስ ጉዳዮች ውስጥ እንደሚገኝ ገልጻለች (Squire 2007:97)::

እዚህ ጋ ከላይ የተጠቀሰው የግለተረክ ርእስ ጉዳይ ብቁነት መሰፈርት አንጻራዊ መሆኑን አጥኚዎቹ የሚቀበሉ ሲሆን በትረካ ዓውዱ ጠባይ፣ በታዳሚው የህይወት ተሞክሮ ስፋት እንዲሁም በተራኪና ታዳሚ መካከል ባለው ግንኙነት ላይ የሚመሰረት መሆኑን ይገልጻሉ (Labov 2007:59; Robinson 1980:59-63):: ለምሳሌ አንዳንድ ርእስ ጉዳዮች በቤተሰብ ወይም በጓደኞች መካከል ብቻ የመተረክ ብቃት ሲኖራቸውና በሌላ ዓውድ ግን የተተራኪነት ብቃት ሊያጡ ይችላሉ::

በአጠቃላይ በግለተረክ ጥናት ውስጥ የተተራኪነት ጽንሰ ሃሳብ ትኩረት የሚሰጠው መሆኑን የተመለከትን ሲሆን በዚህ ላይ ተመስርተን ይህጥናት ከኩረያ ዘማቾች የሰበሰባቸውን ግለተረኮች ስንፈትሽ ይበልጡኑ ከተራኪዎቹ የኩረያ ተልእኮ ጠባይ በመነጨ የግለተረኮቻቸው ርእስ ጉዳዮች በገጸተረኮች ሞትና ህይወትን አደጋ ላይ በጣሉ ሁነቶች ዙሪያ የሚሽከረከሩ ናቸው:: አብዛኛዎቹ ግለተረኮች አግራሞትን የሚያጭሩ ሁነቶችን የሚያካትቱ መሆናቸው በስብስብ ላይ በብዛት የቀረቡ ግለተረኮችን በማንበብ መረዳት እንደሚቻል ተጠቁሟል:: ይህንንም ሁኔታ የጥናቱን የትንታኔ ክፍልና ስብስብ ግለተረኮችን በማየት ማረጋገጥ ይቻላል::

### 3.5 የግለተረክ ክልስፋ (Classification)

የተረክ አጥኚዎች ግለተረኮችን በተለያዩ መንገዶች ከልስፈዋል። ሊንዳ ዴግ በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተመስርታ ግለተረኮችን ሶስት ቦታ ከልስፋለች።

> [Experience stories] can be characterized largely by three topics: (1) the tragic, thrilling or humorous narration of an extraordinary experience in everyday life; (2) narration of experiences during a temporary absence from the community; (3) narration of life experiences in newly formed communities. (1970:221) (1) በለት ተለት ህይወት የሚያጋጥምን አስቃቂ፣ አስፈሪ ወይም አስቂኝ ልዩ ገጠመኝ የተመለከቱ ተረኮች (2) ከሚኖሩበት ማህበረሰብ ለተወሰነ ጊዜ በተለዩበት ወቅት ስለነበረ ተሞክሮ የተመለከቱ ተረኮች (3) አዲስ በተደራጁ ማህበረሰቦች መካከል የነበረን ተሞክሮ መሰረት ያደረጉ ተረኮች ናቸው።

ላቦቭ የተባለ የተረክ አጥኚም መዋቅሮችን መሰረት በማድረግ ግለተረኮችን ሶስት ቦታ እንደከለሰፈ ሮቢንሰን ይጠቅሳል። የመጀመሪያው "fully developed narratives" የሚባሉት ሲሆኑ እነዚህ አጠቃሎ፣ እውቅያ፣ ሲራ፣ ልቀት፣ ምዘናና ኮዳ የተባሉትን ስድስቱንም የግለተረክ መዋቅሮች ያሟሉ ናቸው። ሁለተኛው ክልስፍ "complete narratives" የሚባል ሲሆን ስድስቱን መዋቅሮች ያላሟሉ ግለተረኮች የሚካተቱበት ነው። ሶስተኛው "minimal narratives" የሚባሉት ደግሞ ሁለት ተለጣጣቂ ሃረጎች (sequential clauses) ያሏቸው ሲሆኑ እነዚህ ሃረጎች «በፊት» እና «ቀጥሎ» በሚሉ መስተጻምሮች የሚያያዙ ናቸው (Robinson 1980:73; Labov 1997:4)።

ሌላዋ ግለተረክን የመከልሰፍ ጥረት ያደረገችው ሳንድራ ስታህል ስትሆን በተራኪው የትረካ አንጻር ላይ በመመስረት "other-oriented" እና "self-oriented" በሚል ግለተረኮችን ከልስፋለች።

> Other-oriented narrators underplay their personal role in the story to emphasize the extraordinary nature of things that happen in the tale. ... Whereas 'self-oriented tellers' delight in weaving fairly elaborate tales that build upon their own self-images and emphasize their own actions as either humorous or exemplary (Bauman 1986:34)



ILS LIBRARY ADDIS ABABA

ሌላው በግለተረክ አጥኚዎች ተተግብሮ ያገኘሁት ክልስና "small story" እና "big story" የሚል ነው፡፡ "small story" የሚባለው አንድ ተናጋሪ በንግግሩ መካከል ሃሳቡን ለማጠናከር የሚተርከው ገጠመኝ ሲሆን "big story" ደግሞ በቃለ መጠይቅ ቀስቃሽነት የሚተረክ ገጠመኝ ነው (Freeman 2008:2)፡፡

ከላይ የተጠቀሱት የግለተረክ ክልሰፋ መንገዶች በአንድ ዘውግ ላይ የተተገበሩ የተለያዩ አካሄዶች ናቸው፡፡ ከእነዚህ አካሄዶችም ወጥ የሆነ የግለተረክ አከለሳሰና እንደሌለ መረዳት ይቻላል፡፡ ከእኔ ጥናት ጋር በተያያዘ የሲንዳ ዶግን አከለሳሰና ልገለገልበት የምችልበት እድል ነበር፡፡ ይኸውም ከኩሪያ ዘማቾች የአገኘኋቸው ግለተረኮች ተራኪዎቹ ከነበሩበት ማህበረሰብ ተለይተው የነበሩበትን ወቅት መሰረት ያደረጉ በመሆናቸው በሁለተኛው ክልስና ውስጥ ሊካተቱ መቻላቸው ነው፡፡ ሆኖም ግን ይህ የክልሰፋ መንገድ ቢያንስ በመዋቅርና በጭብጥ የሚለያዩትን እጅግ በርካታ የዘማቾቹን ግለተረኮች ሙሉ በሙሉ በአንድ ጎራ የሚከታቸው በመሆኑ ልከተለው አልፈቀድኩም፡፡

የላቦቭ አከለሳሰናም ቢሆን አንድ ግለተረክ የት ጋ ጀምሮ የት ጋ ያቆማል? የሚለውን በማያከራክር ሁኔታ ለመወሰን በግልጽ የተቀመጠ ስነልሳናዊ መስፈርት የሌለና ይበልጡንም በአጥኚው ፍካሬ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ "fully developed"፣ "complete" እና "minimal" የሚሉት ገላጭ ቃላት በግለተረኮች መካከል አላስፈላጊ የጥራት ፍረጃ የሚያስከትሉ ስለመሰለኝ አልተገለገልኩበትም (Riessman 2002:699)፡፡

ሳንድራም ብትሆን በሁለቱ የግለተረክ ክልሰፎች መካከል ያለውን ልዩነት በወጉ ያላብራራች መሆንዋን በውማን የሚተች ሲሆን አንድ ተራኪ በሚተርከው ግለተረክ ሁነቶች ውስጥ ያለውን የተሳትፎ መጠን ለመለካት የሚያስችል በቂ መስፈርት ማግኘት ባለመቻሌ በሳንድራ አካሄድ ከኩሪያ ዘማቾች የተሰበሰቡትን ግለተረኮች ለመክልሰፍ አልደፈርኩም፡፡ በአጠቃላይ ግለተረኮችን የመክልሰፍ ጥረት በስነተረክ አጥኚዎች ዘንድ መኖሩን አይተናል፡፡ ይህም ሆኖ አንድ ወጥ የሆነና ሰፊ ተቀባይነት ያለው የግለተረክ አከለሳሰና በለማስተዋሌ ከኩሪያ ዘማቾች የተሰበሰቡትን ግለተረኮች መክልሰፍ አልቻልኩም፡፡ የግለተረክ አከለሳሰፍን አስመልክቶ የቀረበው ማብራሪያ አላማም የዘውጉን አጥኚዎች የክልሰፋ ጥረቶች ማሳወቅና ለወደፊት አጥኚዎች የትኩረት አቅጣጫ መጠቆም ነው፡፡

## 4. የኮሪያ ዘማቾች ግለተረኮች የመዋቅርና የጭብጥ ትንተና

በዚህ ምዕራፍ ከኮሪያ ዘማቾች የተሰበሰቡ ግለተረኮች ላይ የተካሄደ የመዋቅርና ጭብጥ ትንተና ይቀርባል።

### 4.1 የኮሪያ ዘማቾች ግለተረኮች የመዋቅር ትንተና

በዚህ ክፍል ከኮሪያ ዘማቾች ከተሰበሰቡት ግለተረኮች ውስጥ ሁለት ናሙናዎችን በመውሰድ የተካሄደ መዋቅራዊ ትንተና ይቀርባል። የትንተናውን አቀራረብ በተመለከተ በትድግያ ሙሉ ተረኩ በመዋቅሮች ተከፍሎ ይቀርባል። እያንዳንዱ መዋቅር በሚተነተንበት ጊዜም የመዋቅሩ ክፋዮች ለበለጠ ግልጽነት ተነጣጥለው ይቀርባሉ። አንድ ግለተረክ በተለይም የሴራ መዋቅሩ በውስጡ የተለያዩ ሁነቶች ሊኖሩት ስለሚችል በትንታኔ ወቅት እያንዳንዱ ሁነት ተቀንጭቦ ይቀርባል።

እያንዳንዱ የግለተረክ መዋቅር የት ጋ ጀምሮ የት ጋ ያቆማል የሚለውን ለመወሰን በግልፅ የተቀመጠ ስነልሳናዊ መስፈርት የሌለ በመሆኑ ናሙና ግለተረኮቹ በመዋቅር የተከፋፈሉት የመዋቅሮቹን ድፍየና መሰረት በአደረገ ፍካሬ ነው። በአጠቃላይ የዚህ ጥናት መዋቅራዊ ትንታኔ አላማ ግለተረክ ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ ተብለው በተረክ አጥኚዎች የተገለጹ መዋቅሮች ከኮሪያ ዘማቾች በተሰበሰቡ ግለተረኮች ውስጥ በምን ሁኔታ እንደሚገኙ ናሙና ግለተረኮችን በመተንተን ማሳየት ነው።

#### 4.1.1 የናሙና ግለተረክ አንድ የመዋቅር ትንተና

ከዚህ ቀጥሎ አንድ ናሙና ግለተረክ የቀረበ ሲሆን በመዋቅሮቹ ላይ የተካሄደው ትንታኔ ይከተላል።

> ቀን ቀን እንቀጠቅጣለን፣ መርከብ እንሰራለን። ይሄንን የሻገተ ቀለም እንጠርጋለን። እነሱ ቀለም ይቀባሉ። ግማሹም ኳስ ይጫወታሉ። በኋላ አንድ ዝናቡ የሚባል መገናኛ ታመመና እ ሆስፒታል ገባ። እኔ አማን ዘንድ ነበርኩ። ያን ጊዜ ምክትል አስር አለቃ ነኝ። አማን ዘንድ ነበርኩ። አማን ዘንድ ነበርኩ። «እስቲ ያንን ሰው ሄጄ አያለሁ» አልኳቸውና እሳቸው መጽሐፋቸውን ያገለባብጣሉ። ታች ሁለት ቁጥር ነው ያለነው፣ ቀዝቃዛ ቦታ ነው። ስወርድ፣ ብረት ካዝና አቅርበው እሱ ሞቷል፣ ባህር ውስጥ ሊጨምሩት። የመርከቡ ትዕዛዝ፣ ደንቡ ነው አሉ።
>
> አሁን እየሮጥኩ ወጣሁና «ጌታዬ» አልኳቸው። «አቤት» አሉ። «ኧረ ያ መገናኛ እኮ፣ ዝናቡ የሚባለው ሞተ እኮ» አልኳቸው። «እና መርከብ ብረት አቅርበው ባህር ውስጥ ሊጨምሩት ነው» አልኳቸው። ይሄን ጊዜ ቁምጣ ነበር የለበሱት ከነቁምጣ እየወረዱ፣ ወረዱ፣ ሆስፒታል ወረዱ። «አይወርድም!» አሉ። ለጃንሆይ ቴሌግራም አደረጉ። ያ የመርከቡ አዛዥ ጨኸት አቀረቡ። «ከየት መጡ እነዚህ?» አሉ። ግሪኮችም ከእኛ ጋራ ነው ያሉት። ብዙ አሉ። ብዙ ሰዎች አሉ። ብዙ አሉ። በኋላ ግሪኮችም አሉ ብዙ። መርከብ ሙሉ ስንት ነው። ቢቃ ፈረንሳዮችም አሉ። ግሪኮችም አሉ። እኛ ተፈረንሳዎች ጋራ ነው ያለነው። ግሪኮችም አሉ። ከዛም በኋላ እሳቸው ወጡ። ተጣሉ። በእንግሊዘኛ



ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

> ሲናገሩ በቃ ተናደደ:: ጃንሆይ «መልሱ፡ ክሳራውን እኛ እንመልሳለን:: መሬት መውረድ አለበት:: ለምን? እንዲ ያለ ህግ የለም::» የፈለገ ነገር ይምጣ ተባለ፣ ተስማ:: በረዶ ውስጥ አስገቡት:: ቀዝቃዛ ቦታ ገባ:: (አስር አለቃ አሰፋ እስፋው፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 4-5፣ ሐምሌ 30፣ 1999 ዓ.ም)::

ይህ ናሙና ግለተረክ በአንድ ግለተረክ ውስጥ ሊገኙ ከሚችሉ ስድስት መዋቅሮች ውስጥ አራቱን አካቷል:: የእነዚህ መዋቅሮች በተረክ ጥናት አላቸው ተብለው ከሚታሰቡት ጠባያት አንጻር ቀጥለው ይተነተናሉ::

#### 4.1.1.1 የእውቅያ መዋቅር

እውቅያ የተተራኪ ሁነቶችን መቼትን፣ የገጸተረኮችን ማንነት እና ቀደም ብለው የነበሩበትን አውድ የሚያስተዋውቅ መዋቅር መሆኑን በትወራ ዳራ ላይ አይተናል:: የናሙና ግለተረኩ እውቅያ መዋቅር እነዚህን መረጃዎች ለታዳሚው ያቀረበ ሲሆን ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን::

> ቀን ቀን እንቀጠቅጣለን፤ መርከብ እንሰራለን:: ይሄንን የሻገተ ቀለም እንጠርጋለን:: እነሱ ቀለም ይቀባሉ:: ግማሹም ኳስ ይጫወታሉ::

በአብዛኞቹ ተረኮች ውስጥ ሶስት ዓይነት ገጸተረኮች የሚገኙ ሲሆን እነርሱም አቀንቃኝ፣ ተቀናቃኝና የሶስተኛ ወገን ምስክሮች ናቸው (Labov 2007:7):: የአንድ ግለተረክ የእውቅያ መዋቅርም በተረኩ ሁነቶች ውስጥ የሚሳተፉ ገጸተረኮችን ማስተዋወቅ ይጠበቅበታል:: ከላይ የቀረበው ናሙና ግለተረክ እውቅያ በወል የተገለጹ ሁለት አይነት ገጸተረኮችን ይጠቁማል:: እነዚህም ቀጥቃጮች፣ መርከብ ሰሪዎችና ጠራጊዎች በአንድ ወገን፣ ቀለም ቀቢዎችና ኳስ ተጫዋቾች ደግሞ በሌላ ወገን ናቸው:: ተራኪው የመጀመሪያውን ቡድን አባላት የሚገልጸው በአንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር በመሆኑ የዚሁ ቡድን አባል መሆኑን የትረካ አንገቱ ያስረዳል:: በዚህም ተራኪውና እሳቸው የሚገኙበትን ቡድን አባላት በአቀንቃኝ ገጸተረክነት ልንወስዳቸው እንችላለን:: ተራኪው ሌሎቹን ገጸተረኮች በሶስተኛ መደብ ብዙ ቁጥር ስለገለጸቸው ተቀናቃኝ ገጸተረኮች ናቸው ለማለት በቂ መረጃ ባይኖርም ከአቀንቃኞች ውጪ እንደሚገኝ ቡድን ሊታሰቡ ይችላሉ:: የግለተረክ እውቅያ በመላው የተረኩ ክፍሎች ውስጥ ተሰራጭቶ የመገኘት ጠባይ ስላለው የናሙና ግለተረኩን አቀንቃኝና ተቀናቃኝ ገጸተረኮች ማንነት ይበልጥ በቀጣይ መዋቅሮች ውስጥ ተገልጾ እንደሚያገኘው አንባቢው መጠበቅ ይችላል (Squire 2007:94-956)::

የናሙና ግለተረኩ የተተራኪ ሁነቶች መቼት መርከብ ላይ እንደሆነ የእውቅያ መዋቅሩ በግልጽ አስተዋውቋል:: ገጸተረኮቹ ያሉበትን አውድ በተመለከተ ተራኪው የተካተቱበት ቡድን አባላት መርከብ በመቀጥቀጥ፣ በመስራትና በመጥረግ ላይ ሲገኙ ሌሎቹ ደግሞ ቀለም



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

በመቀባትና ኳስ በመጫወት ላይ ናቸው:: በዚህ ገለጻ መሰረት ገጸተረኮቹ የሚገኙበትን መርከብ ተጋግዘው በመስራትና በመንከባከብ ተግባር ላይ በጋራ የሚሳተፉ ይመስላሉ:: ከዚህም በመነሳት የሁለቱ ቡድን ተሳታፊዎች ከሁለት ቡድን ከመከፈላቸው በስተቀር ሠላማዊ ወይም ኒውትራል በሆነ ዓውድ ውስጥ የሚገኙ ናቸው ብሎ መገመት ይቻላል (Dijk 1976:316):: ከላይ እንዳየነው የናሙና ግለተረክ እውቅያ መዋቅር የሚጠበቅበትን መቼት፣ ገጸተረኮችና ገጸተረኮቹ የነበሩበትን አውድ የማስተዋወቅ ሚና በአግባቡ ተወጥቷል::

#### 4.1.1.2 የሴራ መዋቅር

በዚህ ክፍል የናሙና ግለተረክ ሴራ መዋቅር የሚተነተን ሲሆን ሴራው በውስጡ በርካታ ሁነቶች ስላሉት ለትንታኔ አስፈላጊ የሆኑት ተቀንጭበው አንድ በአንድ ይተነተናሉ::

> በኋላ አንድ ዝናቡ የሚባል መገናኛ ታመመና እ ሆስፒታል ገባ:: እኔ አማን ዘንድ ነበርኩ:: ያን ጊዜ ምክትል አስር አለቃ ነኝ:: አማን ዘንድ ነበርኩ:: አማን ዘንድ ነበርኩ:: «እስቲ ያንን ሰው ሄጄ እያለሁ» አልኳቸውና እሳቸው መጽሐፋቸውን ያገለባብጣሉ:: ታች ሁለት ቁጥር ነው ያለነው፡ ቀዝቃዛ ቦታ ነው:: ስወርድ፣ ብረት ካዝና አቅርበው እሱ ሞቷል፡ ባህር ውስጥ ሊጨምሩት:: የመርከቡ ትዕዛዝ፣ ደንቡ ነው አሉ::

ትንጭብ አንድ

> በኋላ አንድ ዝናቡ የሚባል መገናኛ ታመመና እእእ ሆስፒታል ገባ:: እኔ አማን ዘንድ ነበርኩ:: ያን ጊዜ ምክትል አስር አለቃ ነኝ:: አማን ዘንድ ነበርኩ:: አማን ዘንድ ነበርኩ::

ከግለተረክ መዋቅሮች ውስጥ እውቅያን ተከትሎ የሚመጣው ሴራ እንደሆነ በትወራ ዱ ላይ አይተናል:: ገጸተረኮች የነበሩበትን ዓውድ የሚቀይር ሁነት ሲያጋጥማቸው የሚታይበት ሲሆን ከእነዚህ ሁነቶች ውስጥ አንደኛው የግለተረኩ ቁንጮ ተተራኪ ሁነት (most reportable event) መሆን ይጠበቅበታል:: ይህ ሁነት በአብዛኛው ገጸተረኮች የሚጋፈጡት ፈተና ሲሆን በተረኩ የሆነ ክፍል ላይ መፈታት ወይም መወገድ ይገባዋል (Dijk 1971:331)::

በዚህ መሰረት የሴራውን የመጀመሪያ ትንጭብ ስንመለከት ዝናቡ የተባለ ገጸተረክ ታሞ ሆስፒታል ገብቷል:: በዚህም ተጋግዘው መርከብ ከሚሰሩ ገጸተረኮች ውስጥ አንዱ ታምሞ ሆስፒታል በመግባቱ ከመሀላቸው አንድ አጋዥ ጎድሎባቸዋል:: ይህንንም ሁነት በተለይ ተራኪው ከሚገኝበት የእቀንቃኝ ገጸተረኮች አንጻር ስናየው ስሜታቸውን ሊጎዳ የሚችል ነው:: ይህ ክስተት በናሙና ግለተረኩ የሴራ መዋቅር የቀረበ የመጀመሪያው የሁነት



ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

ገለጻ ሲሆን ቁንጮ ተተራኪ ሁነት ማቅረብ ይቀረዋል። በዚህም ቀጣዩ ተግባር በሴራ መዋቅር ውስጥ ቁንጮውን ተተራኪ ሁነት መፈለግ ይሆናል። እዚህ ጋ የዚህ ንኡስ የትንታኔ ክፍል አላማ ቁንጮውን ተተራኪ ሁነት ፈልጎ ማግኘት የትንታኔው አላማ አይደለም። ነገር ግን በሴራ መዋቅር ውስጥ የሚገኙትን ሁነቶች በመተንተን ሂደት ቁንጮውን ተተራኪ ሁነት በአንክሮ መከታተል ተገቢ ሲሆን ይኸውም የአንድ ግለተረክ የልቀት መዋቅር የሚጀምረው ቁንጮውን ተተራኪ ሁነት ተከትሎ በመሆኑ ነው (Labov 1997:16)።

ዝናቡ የተባለው ገጸተረክ ታምሞ ሆስፒታል የገባበት ሁነት የናሙና ግለተረኩ ቁንጮ ተተራኪ ሁነት የመሆን ብቃት የለውም። ለዚህ አንዱ መጠነኛ ምክንያት ተራኪዎች የትረካ ክዋኔያቸውን የተረኩ ቁንጮ በሆነ ሁነት የሚጀምሩበት አጋጣሚ በስፋት የማይስተዋል መሆኑ ነው (Labov 1997:6)። መሰረታዊው ምክንያት ግን የገጸተረኩ መታመምና ሆስፒታል መግባት በናሙና ግለተረኩ ውስጥ ከሚገኙት ክስተቶች ጋር ሲነጻጸር እንግዳ አለመሆኑና በገጸተረኮቹ ስሜት ላይ ጉልህ ተጽእኖ አለማሳደሩ ነው። ይህን ለማለት የሚያስደፍረው በመርከብ ጉዞ ላይ የተሳፋሪዎች መታመም ወይንም አደጋ ማጋጠም በገጸተረኮች ዘንድ ሊከሰት እንደሚችል የታመነ ሁነት ይመስላል። ለዚህ ማስረጃው በመርከቡ ላይ ለዚሁ አላማ የተዘጋጀ ሆስፒታል መኖሩ ነው። በእነዚህ ከላይ የተጠቀሱ ምክንያቶች የገጸተረኩ ታሞ ሆስፒታል የመግባት ሁነት በሴራ መዋቅር ውስጥ መኖር የሚገባው ቁንጮ ተተራኪ ሁነት ባለመሆኑ ወደ ቀጣይ የሴራ ሁነቶች እንሄዳለን።

ከዚያ በፊት ግን በሴራ መዋቅሩ ውስጥ የሚገኘውን የሶስት ገጸተረኮች ገለጻ እንመልከት። አንደኛው ገጸተረክ ዝናቡ ተብሎ የሚጠራና ሙያው መገናኛ ነው። ሁለተኛው ተራኪው ሲሆን አማን ከሚባለ ገጸተረክ ጋር የሚገኙ የእስር አለቃ ማዕረግ ያላቸው ወታደር ናቸው። ሶስተኛው አማን ተብለው የሚጠሩ ከመሆናቸው ውጪ በቀጥታ የተገለጸ መረጃ የለም። እዚህ ጋ ተራኪው «አማን ዘንድ ነበርኩ» የሚለውን ዓረፍተ ነገር ሦስት ጊዜ መደጋገማቸው አማን ከተባሉት ገጸተረክ ጋር በቅርብ የሰሩ መሆናቸውን የተረኩ ታዳሚ እንዲያውቅላቸው መፈለጋቸውን ያሳያል (Riessman 2002:703)። ተራኪው በግለተረኩ አቀንቃኝ ገጸተረኮች ውስጥ የሚካተቱ ከመሆናቸውና አማን ዘንድ የነበሩ ባለማዕረግ ወታደር መሆናቸውን መሠረት በማድረግ አማንን በአቀንቃኝ ገጸተረኮች አዛዥነት ልንወስዳቸው እንችላለን። ይህ ገለጻ ሁለቱ ገጸተረኮች ቀጥለው በሚመጡት የናሙና ግለተረኩ መዋቅሮች ውስጥ ቢያጋጥሙ ማንነታቸው አዲስ በማይሆንበት መልክ ለታዳሚው ይበልጥ ያስተዋውቀ ነው።

ትንጥብ ሁለት

«እስቲ ያንን ሰው ሄጀ አያለሁ» አልኳቸውና እሳቸው መጽሐፋቸውን ያገለባብጣሉ። ታች ሁለት ቁጥር ነው ያለነው፣ ቀዝቃዛ ቦታ ነው።

IES LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

የናሙና ግለተረኩ ሴራ ሁለተኛው የሁነት ገለጻ ተራኪው ታሞ ሆስፒታል የገባውን ገጸተረክ ሄደው ለመጠየቅ ከአማን ፈቃድ ሲጠይቁ ያሳያል:: ይህም ቢሆን የናሙና ግለተረኩ ቁንጮ ተተራኪ ሁነት አይደለም:: ሁነቱ በተረኩ ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች ሁነቶች ጋር ሲነጻጸር እንግዳነት የሌለው ተራ የእለት ተእለት ድርጊት ነው::

ትንጭብ ሶስት

ስወርድ ብረት ካዝና አቅርበው እሱ ሞቷል፡

ይህ ትንጭብ ታሞ ሆስፒታል የገባው ገጸተረክ መሞቱን ያስረዳል:: ገጸተረኩ የሞተበት ሁነት ግን የናሙና ግለተረኩ ቁንጮ ተተራኪ ሁነት አይደለም:: ይህን ለማለት ምክንያት የሆነው እስከ አሁን ከቀረቡት የግለተረኩ ሁነቶች ጋር ሲነጻጸር ሁነቱ ሳይታሰብ ድንገት የተከሰተ አለመሆኑ ነው:: ይኸውም የሞተው ገጸተረክ ቀደም ብሎ ታሞ ሆስፒታል የገባ ነው:: ከዚህም በተጨማሪ ሟቹ ገጸተረክ ሊገድል በማይችል ወይም ሊሞትበት በማይገባ ህመም ለመያዙ ምንም አይነት ፍንጭ የለም:: ይህንን ተከትሎም ታምሞ ሆስፒታል የገባው ገጸተረክ ሞት በሌሎቹ ገጸተረኮቹ ላይ የጎላ ተጽእኖ አሳድሯል ለማለት ይከብዳል:: የሁነቱ ገለጻ ያለው ሚና ቢኖር ቀጣዮቹን ተተራኪ ሁነቶች የማወቅ ጉጉት በታዳሚ ውስጥ መፍጠር ብቻ ይመስላል::

ትንጭብ አራት

ባህር ውስጥ ሊጨምሩት:: የመርከቡ ትእዛዝ፣ ደንብ ነው አሉ::

ይህ ትንጭብ የናሙና ግለተረኩን ቁንጮ ተተራኪ ሁነት ይዟል:: ለዚህም ሁለት ምክንያቶችን ማቅረብ ይቻላል:: የመጀመሪያው ሬሳን ባህር ለመጣል የመዘጋጀት ድርጊት በተረኩ የእውቅያና የሴራ መዋቅር ውስጥ ከሚገኙት ሁነቶች ጋር ሲነጻጸር እንግዳ ነው:: አብሮ መስራት፣ መጫወት፣ ታምሞ ሆስፒታል መግባትና መሞት የለት ተለት ክስተቶች ሊባሉ የሚችሉ ናቸው:: ሬሳ ባህር የሚጣልበት ሁኔታ ግን እንግዳ ይመስላል:: ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ቀደም ባሉት ገለጻዎች የአቀንቃኝና ተቀናቃኝ ገጸተረኮች በመተጋገዝ የተሳፈሩትን መርከብ ሲንከባከቡ፣ አንድ ገጸተረክ ታሞ ሆስፒታል ሲገባና እዛው እያለ ህይወቱ ማለፉን አይተናል:: እነዚህ ድርጊቶች በየትኛውም አቀንቃኝ ወይም ተቀናቃኝ ገጸተረክ አስፈጻሚነትም ሆነ ፈጻሚነት ሲከሰቱ አልተስተዋሉም:: አሁን ግን በሌላ ጎራ በሚገኝ ገጸተረክ ላይ ድርጊት ሊፈጽሙ ተዘጋጅተዋል:: ከዚህም በተጨማሪ የትኛውም ሁነት ለመከሰቱ ተገቢነት ምክንያት ሲቀርብ አልተስተዋለም:: ለሬሳው ባህር መጣል ተገቢነት ግን የመርከቡ ደንብ ተጠቅሷል:: የደንቡ መጠቀስ ሬሳ ባህር የመጣል ድርጊት በሁሉም ገጸተረኮች ዘንድ ሙሉ ተቀባይነት ባይኖረው ነው ለማለት ያስደፍራል:: ከዚህም በመነሳት የዝናቡ ሬሳ



ILS LIBRARY
ADDIS ... UNIVERSITY

ወደ ባህር ሊጣል መዘጋጀት ተራኪውን ጨምሮ የሌሎች ገጸተረኮችንም ስሜት ሊጎዳ እንደሚችል መገመት ይቻላል::

ከላይ በቀረቡት ምክንያቶች የናሙና ግለተረክ ቁጥር አንድ ቁንጮ ተተራኪ ሁነት የዝናቡ ሬሳ ወደ ባህር ሊጣል የተዘጋጀበት ሁኔታ ነው በሚል መደምደሚያ ላይ ተደርሷል:: አንድ ግለተረክ ቁንጮውን ተተራኪ ሁነት መያዙ ወይንም ማቅረቡ ብቻውን ምሉእ ስለማያደርገውና የልቀት መዋቅር መሸጋገሪያ በመሆኑ ወደዚሁ መዋቅር ትንተና እንሄዳለን::

**4.1.1.3 የልቀት መዋቅር**

የልቀት መዋቅር የሚጀምረው ቁንጮውን ተተራኪ ሁነት ተከትሎ ሲሆን ፈተና ውስጥ የወደቁ ገጸተረኮች የመፍትሄ እርምጃዎችን ሲወስዱ የሚያሳይ ገለጻ የሚቀርብበት ነው:: እነዚህን የልቀት ጠባያት ይዘን የናሙና ግለተረኩን የልቀት መዋቅር እንመለከታለን::

> አሁን እየሮጥኩ ወጣሁና «ጌታዬ» አልኳቸው:: «አቤት» አሉ:: «ኧረ ያ መገናኛ እኮ ዝናቡ የሚባለው ሞተ እኮ» አልኳቸው:: «እና መርከብ ብረት አቅርበው ባህር ውስጥ ሊጨምሩት ነው» አልኳቸው:: ይህን ጊዜ ቁምጣ ነበር የለበሱት ከነቁምጣ እየወረዱ፣ ወረዱ፤ ሆስፒታል ወረዱ:: «አይወርድም!» አሉ:: ለጃንሆይ ቴሌግራም አረጉ:: ያ የመርከቡ አዛዥ ጨኸት አቀረበ:: «ከየት መጡ እነዚህ?» አሉ:: ግሪኮችም ከእኛ ጋራ ነው ያሉት:: ብዙ አሉ:: ብዙ ሰዎች አሉ:: ብዙ አሉ:: በኋላ ግሪኮችም አሉ ብዙ:: መርከብ ሙሉ ስንት ነው ቢቃ ፈረንሳዮችም አሉ:: ግሪኮችም አሉ:: እኛ ተፈረንሳዎች ጋራ ነው ያለነው:: ግሪኮችም አሉ:: ከዚያም በኋላ እሳቸው ወጡ:: ተጣሉ:: በእንግሊዘኛ ሲናገሩ ቢቃ ተናደደ:: ጃንሆይ «መልሱ፣ ከሳራውን እኛ እንመልሳለን:: መሬት መውረድ አለበት:: ለምን? እንዲ ያለ ህግ የለም::» የፈለገ ነገር ይምጣ ተባለ፣ ተሰማ:: በረዶ ውስጥ አስገቡት:: ቀዝቃዛ ቦታ ገባ::

እስከአሁን በማየት ላይ ባለነው ናሙና ግለተረክ ውስጥ አቀንቃኝና ተቀናቃኝ ገጸተረኮች መኖራቸውን ተረድተናል:: ተራኪው፣ ሚቹና አማን ከአቀንቃኝ ገጸተረኮች ጎራ ናቸው:: ከእነሱ ውጪ ደግሞ ተቀናቃኝ ገጸተረኮች የሚገኙ ሲሆን እነዚህም የሚቹን ሬሳ ወደ ባህር ለመጣል የተዘጋጁት ናቸው:: በሬሳው ላይ ሊወሰድ የተዘጋጀው እርምጃ ደግሞ ለአቀንቃኝ ገጸተረኮች ፈተና ሆኖባቸዋል:: ይህንን ፈተና ግን በጸጋ ከመቀበል ይልቅ ተጋፍጠው ማስወገድ መርጠዋል:: በዚህም የተነሳ ተራኪው የዝናቡ ሬሳ ወደ ባህር ሲጣል መዘጋጀቱን እንዲያውቁ መረጃውን ለአማን በፍጥነት አሳውቀዋል:: አማንም መረጃው እንደደረሳቸው ሁለት የመፍትሄ እርምጃዎችን ወሰዱ:: አንደኛው በታቀደው ድርጊት ላይ ያላቸውን ተቃውሞ በአካል ቀርበው ለመርከቡ አዛገሮች መግለጻቸውና መጣላታቸው ነው:: ከዚህም ሌላ ከአጋጠማቸው ፈተና ለመውጣት ጃንሆይ በሚል ለተገለጹ ሌላ ገጸተረክ የአጋጠማቸውን ሁኔታ አሳወቁ:: አቀንቃኝ ገጸተረኮቹ በወሰዷቸው በእነዚህ እርምጃዎች ምክንያትነትም ለከፍተኛ ቁጣ የዳረጋቸው ፈታኝ ሁኔታ ሊወገድ ቻለ:: ሲገመዱ የመጡት



ADDIS ABABA UNIVERSITY

የሴራ ሁነቶችም ልቀት አገኙ:: ወደ ባህር ሊጣል የተዘጋጀው ሬሳም አቀንቃኝ ገጸተረኮቹ በሚፈልጉት መልክ ተቀመጠ::

የናሙና ግለተረክ ሴራ ልቀት ያገኘበት ሁኔታ የታዳሚን አድናቆት ወይንም ሙገሳ የመጋበዝ አቅም አለው:: ለዚህ በምክንያትነት የሚጠቀሰው በተረክ ጥናት የተረክ ታዳሚን ሙገሳ የመጋበዝ ብቃት እንዳለው የሚታመንበት ቅድመ ሁኔታ ተሟልቶ መቅረቡ ነው:: ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ ቫን ዲይክ በተረክ ክዋኔ የሙገሳ አጸፋ ሊሰነዘር የሚችለው ተራኪ ገጸተረኩ የልቀት ድርጊቱን ሆን ብሎ ሲፈጽምና ፈተናውን በአቦሰጡኝ ያላስወገደ ሲሆን ነው ብሏል:: "...an appraisal is possible only when the agent-teller intentionally brought about his resolving action, and did not merely succed by good luck to solve his predicament." (1971:320) በዚህ ላይ ተመስርተን ናሙና ግለተረክ ቁጥር አንድ ልቀቱን የአገኘበት ሁኔታ ሙገሳን የመጋበዝ አቅም እንዳለው በቀላሉ መረዳት ይቻላል::

#### 4.1.1.4 የምዘና መዋቅር

ማንኛውም ግለተረክ የተረኩን ዳራ አስተዋውቆ፣ ሴራውን ገልጾና ልቀቱን አሳይቶ አያበቃም:: ተራኪው ስለተረኩ ሁነቶች ያለውን ስሜት ወይንም አመለካከት በተዘዋዋሪ አለበለዚያም በቀጥታ ማሳወቅ ይኖርበታል:: በዚህም መሰረት የናሙና ግለተረኩን የምዘና መዋቅር ስንመለከት ተራኪው ተረኩን አስመልክተው በግልጽ ያቀረቡት ሃሳብ የለም:: ነገር ግን ምዘና መዋቅር ሊቀርብ ከሚችልባቸው የተለያዩ መንገዶች ውስጥ በይፋ ሳይገለጽ ለታዳሚው «ኢንፈረንስ» ክፍት የሆነ ነው:: ይኸውም በናሙና ግለተረክ ሴራ ውስጥ ለአቀንቃኝ ገጸተረኮች ፈተና የሆነባቸው የባልደረባቸው ሬሳ ወደ ባህር ሊጣል መዘጋጀት በወስዷቸው እርምጃዎች ሊቀለበስ ችሏል:: ይፈለግ የነበረው ውጤት ተገኝቷል:: በናሙና ግለተረኩ የምዘና መዋቅር ውስጥ የሴራውን ልቀት አስመልክቶ በይፋ የቀረበ የተራኪው ምዘና ባይታይም እንኳን የባልደረባችንን ሬሳ ወደ ባህር ከመጣል ታግለን አስጣልነው የሚል አንድምታ እንዳለው መገመት ይቻላል::

በአጠቃላይ አንድ ግለተረክ ሊኖሩት ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ መዋቅሮች ከኮሪያ ዘማቾች በተሰበሰቡ ግለተረኮች ውስጥ ሊኖራቸው የሚችለውን ገጽታ በናሙና ግለተረክ አማካይነት ለማሳየት ተሞክሯል:: ይህንኑ መዋቅራዊ ትንተናም አንድ ናሙና በመጨመር እናዳብረዋለን::

### 4.1.2 የናሙና ግለተረክ ሁለት የመዋቅር ትንተና

በተረክ ጥናት አንድ ግለተረክ ስድስት ያህል መዋቅሮች ሊኖሩት እንደሚችል ይታሰባል:: ናሙና ግለተረክ ቁጥር አንድ አራት መዋቅሮች እንዳሉት አይተናል:: ቀጥለን ደግሞ አምስት መዋቅሮች ያሉትን ናሙና ግለተረክ በዝርዝር እናያለን::

የሴራ ሁነቶችም ልቀት አገኙ:: ወደ ባህር ሊጣል የተዘጋጀው ሬሳም አቀንቃኝ ገጸተረኮቹ በሚፈልጉት መልክ ተቀመጠ::

የናሙና ግለተረኩ ሴራ ልቀት ያገኘበት ሁኔታ የታዳሚን አድናቆት ወይንም ሙገሳ የመጋበዝ አቅም አለው:: ስለዚህ በምክንያትነት የሚጠቀሰው በተረክ ጥናት የተረክ ታዳሚን ሙገሳ የመጋበዝ ብቃት እንዳለው የሚታመንበት ቅድመ ሁኔታ ተሟልቶ መቅረቡ ነው:: ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ ቫን ዳይክ በተረክ ክዋኔ የሙገሳ አጸፋ ሊሰነዘር የሚችለው ተራኪ ገጸተረኩ የልቀት ድርጊቱን ሆን ብሎ ሲፈጽምና ፈተናውን በአቦሰጡኝ ያላስወገደ ሲሆን ነው ብሏል:: "...an appraisal is possible only when the agent-teller intentionally brought about his resolving action, and did not merely succed by good luck to solve his predicament." (1971:320) በዚህ ላይ ተመስርተን ናሙና ግለተረክ ቁጥር አንድ ልቀቱን የአገኘበት ሁኔታ ሙገሳን የመጋበዝ አቅም እንዳለው በቀላሉ መረዳት ይቻላል::

### 4.1.1.4 የምዘና መዋቅር

ማንኛውም ግለተረክ የተረኩን ዳራ አስተዋውቆ፣ ሴራውን ገልጾና ልቀቱን አሳይቶ አያበቃም:: ተራኪው ስለተረኩ ሁነቶች ያለውን ስሜት ወይንም አመለካከት በተዘዋዋሪ አለበለዚያም በቀጥታ ማሳወቅ ይኖርበታል:: በዚህም መሰረት የናሙና ግለተረኩን የምዘና መዋቅር ስንመለከት ተራኪው ተረኩን አስመልክተው በግልጽ ያቀረቡት ሃሳብ የለም:: ነገር ግን ምዘና መዋቅር ሊቀርብ ከሚችልባቸው የተለያዩ መንገዶች ውስጥ በይፋ ሳይገለጽ ለታዳሚው «ኢንፈረንስ» ክፍት የሆነ ነው:: ይኸውም በናሙና ግለተረኩ ሴራ ውስጥ ለአቀንቃኝ ገጸተረኮች ፈተና የሆነባቸው የባልደረባቸው ሬሳ ወደ ባህር ሲጣል መዘጋጀት በወሰዷቸው እርምጃዎች ሊቀለበስ ችሏል:: ይፈለግ የነበረው ውጤት ተገኝቷል:: በናሙና ግለተረኩ የምዘና መዋቅር ውስጥ የሴራውን ልቀት አስመልክቶ በይፋ የቀረበ የተራኪው ምዘና ባይታይም እንኳን የባልደረባችንን ሬሳ ወደ ባህር ከመጣል ታግለን አስጣልነው የሚል አንድምታ እንዳለው መገመት ይቻላል::

በአጠቃላይ አንድ ግለተረክ ሊኖሩት ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ መዋቅሮች ከኮሪያ ዘማቾች በተሰበሰቡ ግለተረኮች ውስጥ ሊኖራቸው የሚችለውን ገጽታ በናሙና ግለተረክ አማካይነት ለማሳየት ተሞክሯል:: ይህንኑ መዋቅራዊ ትንተናም አንድ ናሙና በመጨመር እናዳብረዋለን::

### 4.1.2 የናሙና ግለተረክ ሁለት የመዋቅር ትንተና

በተረክ ጥናት አንድ ግለተረክ ስድስት ያህል መዋቅሮች ሊኖሩት እንደሚችል ይታሰባል:: ናሙና ግለተረክ ቁጥር አንድ አራት መዋቅሮች እንዳሉት አይተናል:: ቀጥለን ደግሞ አምስት መዋቅሮች ያሉትን ናሙና ግለተረክ በዝርዝር እናያለን::

ለአረፍት ተመለስ ተባልን አንድ ጊዜ። ተመለስ ተብለን በምንሄድበት ጊዜ በረዶው ራስ ያንሸራትታል። ይደርቃል በረዶው ይከመር ይከመርና ይደርቃል። ያ ካንሸራተተህ መመለሻ የለህም። ግራና ቀኝ ገደል ነው። መንገዱ ጠባብ መንገድ ነው። ያንን በምንሄድበት ጊዜ አንድ ጓደኛዬ ከኔ ፊት ለፊት ይሄዳል። ደግሞ የምንመለሰው በጨለማ እንጅ በብርሀን አይደለም። ምክንያቱም አውሮኘላን ይመታናል። እና ስንመለስ ያ ጓደኛዬ ይንሸራተታል። ሲንሸራተት በቃ መጨረሻ እንትን ላይ ለመድረስ ሲል አንድ የተቆረጠ እንጨት ነበር። የዚህ አይነት ጥድ። ከዚያ ያዘለው ሻንጣ እዛ ውስጥ ይገባና አዳነው። ይሄ በጣም እንደ ታሪክ አድርጌ ነው የምቆጥረው። ምክንያቱም ህይወቱን አዳነው። ወደ ታች ዝቅ ቢል ኖሮ ተሰባብሮ እዛው ነበር የሚቀረው። ሆረን ብዙ መንገድ ሄደን ነው የምናገኘው እንጅ አናገኘውም። እና ይሄ ትዝ ይለኛል (መቶ አለቃ ታደሰ ገብረ ክርስቶስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 9፣ ነሐሴ 6፣ 1999 ዓ.ም)።

### 4.1.2.1 የእውቅያ መዋቅር

የግለተረክ እውቅያ መዋቅር መቼት፣ የገጸተረክ ማንነትና ገጸተረኮቹ የነበሩበትን ኍውድ ማስተዋወቅ እንደሚጠበቅበት ከናሙና ግለተረክ አንድ መዋቅራዊ ትንተና ይበልጥ ተረድተናል። ቀጥለን ደግሞ የናሙና ግለተረክ ቁጥር ሁለት የእውቅያ መዋቅር ያለውን ገጽታ የምንመለከት ሲሆን መዋቅሩም የሚከተለው ነው።

> አንድ ጊዜ ለአረፍት ተመለስ ተባልን። የምንሄድበት በረዶ ራስ ያንሸራትታል። ይደርቃል በረዶው ይከመር ይከመርና ይደርቃል። ያ ካንሸራተተህ መመለሻ የለህም። ግራና ቀኝ ገደል ነው። መንገዱ ጠባብ መንገድ ነው።

መቼቱን በተመለከተ የጊዜ ገለጻው «አንድ ጊዜ» የሚል ሲሆን ይህም በተረክ የእውቅያ መዋቅር ውስጥ ተዘውታሪነት ያለው ነው (Babcock 1977:68)። የቦታ ገለጻውም ዝርዝርና ቀጥሎ ከሚመጣው የግለተረኩ ሴራ ጋር ተያያዥነት አለው። ቦታው በረዶ የተጋገረበት፣ ግራና ቀኝ ገደላማ ሲሆን በዚህ መሃል ጠባብ መንገድ ይገኛል። መልክዓ ምድራዊ ገለጻው ምስል ከሳች የሚባል ነው።

ገጸተረኮችን በተመለከተ ዝርዝርና ግልጽ መረጃ ባይቀርብም በአንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር የተገለጸ ቡድን አለ። «ተመለስ» እና «ተባልን» በሚሉት ቃላት ውስጥ ከሚገኙት ድህረ ቅጥያዎች ተራኪው ከግለተረኩ ገጸተረኮች መሃል አንዱ መሆኑን መረዳት ይቻላል። በአጠቃላይ የናሙና ተረኩ እውቅያ አስፈላጊ ገለጻዎችን በተለይም የቦታ ገለጻን ልብ ስቃይ በሆነ መንገድ አቅርቧል።

### 4.1.2.2 የሴራ መዋቅር

ሴራ በእውቅያ የነበረውን የገጸተረኮች ነባራዊ ሁኔታ የሚቀይሩ ሁነቶች ገለጻ የሚያቀርብ ሲሆን ቁንጮውን ተተራኪ ሁነትም ያካትታል። እነዚህ ሁነቶች አብዛኛውን ጊዜ በናሙና ገጸተረኮች የሚገጥባቸው ፈታኝ ሁኔታዎች ናቸው። ቀጥለን እነዚህ ሁኔታዎች በናሙና

ADDIS ABABA UNIVERSITY IES LIBRARY

ግለተረክ ቁጥር ሁለት ውስጥ ያላቸውን መልክ የምንፈትሽ ሲሆን መዋቅሩም የሚከተለው ነው።

> በምንሄድበት ጊዜ፣ አንድ ጓደኛዬ ከኔ ፊት ለፊት ይሄዳል። ደግሞ የምንመለሰው በጨለማ እንጂ በብርሀን አይደለም። ምክንያቱም አውሮኘላን ይመታናል። እና ስንመለስ ያ ጓደኛዬ ይንሸራተታል። ሲንሸራተት፣ በቃ መጨረሻ እንትን ላይ ለመድረስ ሲል አንድ የተቆረጠ እንጨት ነበር። የዚህ አይነት ጥድ።

ይህ የናሙና ግለተረክ ቁጥር ሁለት የሴራ መዋቅር የጎላ ምክንያታዊ ትስስሮሽ ያላቸው ሁነቶች ገለጻ አቅርቧል። ከተራኪው ፊት ለፊት የሚጓዝ ገጸተረክ ሲንሸራተት ይስተዋላል። የተራኪው ጓደኛ የተንሸራተተበት ሁነት የግለተረኩ ማጠንጠኛ ሲሆን እጅግ ምክንያታዊነት አለው። ይኸውም በአውቶያው የቀረበው ገጸተረኮቹ የሚጓዙበት መልክዓ ምድር በረዷማነትና ገደላማነት ገለጻ ለተፈጠረው የመንሸራተት ሁነት ተጠባቂነት (expectable) አመቺ ዳራ ሆኗል። ከዚህም በተጨማሪ የገጸተረኩ መንሸራተት ላለመንሸራተት የሚያመች ሁኔታ የተከሰተ አይደለም። ገጸተረኮቹ ይጓዙ የነበረው በብርሃን ሳይሆን በጨለማ መሆኑ የተራኪው ጓደኛ ይንሸራተት ዘንድ የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል። በጨለማ መሄዱም ቢሆን ተገቢነት እንደነበረው «የምንመለሰው በጨለማ እንጂ በብርሀን አይደለም። ምክንያቱም አውሮኘላን ይመታናል» በማለት ተራኪው አስረድተዋል። ይህም በጨለማ ተጉዘው እንደ ሰው መንሸራተቱ በብርሃን ተጉዘው የቡድኑ አባላት በሙሉ ለጠላት የአውሮኘላን ድብደባ ከሚጋለጡ የተሻለ አማራጭ መሆኑን የሚያጸና ነው። በሌላ አገላለጽ በጨለማ መሄድ ያስከተለውን ፈታኝ ክስተት ለማስቀረት በጨለማ አለመሄድ መፍትሄ ሳይሆን ይብልጥ የከፋ ፈተና ውስጥ የሚጥል ነው።

ይህ የመንሸራተት ክስተት የናሙና ግለተረኩ ቁንጮ ተተራኪ ሁነት ሲሆን ለዚህም ማሳያዎች አሉ። አንደኛው ለእረፍት ከሚሄዱ ገጸተረኮች ውስጥ የአንደኛው መንሸራተት ከሁነቱ አንሸራታችነት አንጻር የሚጠበቅ ክስተት ቢሆንም በተራኪው ላይ ግን ከፍተኛ የስሜት መረበሽ የማስከተል ብቃት አለው። ይኸውም ስፍራው አደገኛ ገደላማነት ስላለው የተንሸራታቹ ህይወት ስጋት ውስጥ ሊገባና ተራኪውንም ጭምር ሊያስጨንቅ የሚችል ነው። «ከንሸራተተህ መመለሻ የለህም።» በሚል የቀረበው ገለጻም የቦታውን አደገኛነት የሚያሳይ ነው። ይህ ዙሪያው ገደላማና መመለሻ ሊያሳጣ በሚችል በረዶ ላይ የተከሰተ የመንሸራተት ሁነት ገለጻ የታዳሚን ትጉት ሊያጭርና «ቀጥሎስ ምን ይሆን?» እንዲል የማስገደድ አቅም አለው። በአጠቃላይ የገጸተረኩ መንሸራተት የናሙና ግለተረክ ቁጥር ሁለት ቁንጮ ተተራኪ ሁነት ሲሆን በተከታዩ የልቀት መዋቅር ውስጥ ሲወገድ ለማየት ታዳሚውን የሚያጓጓ ነው።

#### 4.1.2.3 የልቀት መዋቅር

ልቀት በሴራ መዋቅር ላይ አቀንቃኝ ገጸተረኮች ከገቡበት ፈታኝ ሁኔታ ሲወጡ የሚያሳይ የሚያተርብ ነው። በዚህ መሰረት የናሙና ግለተረክ ቁጥር ሁለት የልቀት መዋቅር ያለውን ገጽታ የምንመለከት ሲሆን መዋቅሩም የሚከተለው ነው::

> ከዚያ ያዘለው ሻንጣ እዛ ውስጥ ይገባና አዳነው::

ይህ ገለጻ በአንሸራታች በረዷማ ገደል ላይ ቁልቁል መንሸራተት የጀመረው ገጸተረክ ከገባበት ፈታኝ ሁኔታ ሲወጣ ያሳያል። ይህ ደግሞ ከልቀት መዋቅር የሚጠበቅ ገለጻ ነው:: ይህንን ልቀት ከናሙና ግለተረክ ቁጥር አንድ የሚለየው ጉልህ ገጽታ ያለ ሲሆን ይኸውም ልቀቱ የተገኘው ገጸተረኩን በሚያስሞግስ መልኩ አለመሆኑ ነው:: ፈታኝ ሁኔታው የተወገደው በአቀንቃኝ ገጸተረኮች እርምጃ ሳይሆን በግኡዙ አካል እርዳታ ነው:: በዚህም የተነሳ ታዳሚው ለአቀንቃኝ ገጸተረኮቹ ተግባር የሙገሳ ወይንም የአድናቆት አጸፋ እንዲሰነዝር የሚያስገድደው አንዳችም ምክንያት የለም። በአጠቃላይ ሲታይ ግን የልቀት መዋቅሩ የሚጠበቅበትን አቀንቃኝ ገጸተረኮች ከአጋጠማቸው ፈታኝ ሁኔታ ሲወጡ የሚያሳይ ገለጻ ለታዳሚው አቅርቧል።

#### 4.1.2.4 የምዘና መዋቅር

የምዘና መዋቅር ስለተረኩ ሁነቶች ተራኪው ያለውን ስሜት ወይንም አመለካከት በተዘዋዋሪ አለበለዚያም በቀጥታ የማሳወቅ ሚና አለው። ይህን ታሳቢ በማድረግ የናሙና ግለተረክ ቁጥር ሁለት የምዘና መዋቅር ያለውን ገጽታ የምንፈትሽ ሲሆን መዋቅሩም የሚከተለው ነው።

> ይሄ በጣም እንደ ታሪክ አድርጌ ነው የምቆጥረው:: ምክንያቱም ህይወቱን አዳነው። ወደ ታች ዝቅ ቢል ኖሮ ተሰባብሮ እዛው ነበር የሚቀረው:: ዞረን ብዙ መንገድ ሄደን ነው የምናገኘው እንጂ አናገኘውም::

የናሙና ግለተረክ ቁጥር ሁለት ተራኪ የተረኩን ሴራ ልቀት ላይ ከአቀረቡ በኋላ ወደ ምዘና ሄደዋል። ገጸተረኩ ያጋጠመው ፈታኝ ሁኔታ በልቀት ላይ ከተገለጸው በተቃራኒው ቢፈታ ኖሮ ከሚያደርሰው ጉዳት ጋር በማነጻጸር ምዘናቸውን አሳውቀዋል:: ይኸውም ተራኪው ጓደኛቸው ያጋጠመው ቁልቁል ወደ ገደል የመንሸራተት ሂደት በዛፍ እገዛ ባይቀለበስ ኖሮ ሕይወቱን ሊያጣ እንደሚችል ገልጸዋል።

የተራኪው ምዘና አንድ ተራኪ ሁነቶችን የሚመዝነው በተጨባጭ ካልተከሰቱ ሁነቶች ጋር በማነጻጸር ነው ከሚለው የላቦቭ እይታ ጋር የተጣጣመ ነው:: "A narrator evaluates events by comparing them to with events in an alternative reality that was not in fact realized." (1997:6)

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

#### 4.1.2.5 የኮዳ መዋቅር

ኮዳ በግለተረክ መዋቅሮች ውስጥ መጨረሻ ላይ የሚመጣና ታዳሚው «ከዚያስ ምን ሆነ?» የሚሉ ጥያቄዎችን ሊያነሳ በማያስችለው መልኩ ትረካው የሚደመደምበት ነው። ቀጥሎን የናሙና ግለተረክ ቁጥር ሁለት የኮዳ መዋቅር ያለውን መልክ የምንፈትሽ ሲሆን መዋቅሩም የሚከተለው ነው።

እና ይሄ ትዝ ይለኛል።

በዚህ መሰረት የናሙና ግለተረክ ቁጥር ሁለትን ኮዳ ስናይ ተራኪው ትረካቸው መደምደሙን ለታዳሚ ያሳወቁበት ነው። የትኛውም ታዳሚ በአንድ ተረክ ማብቂያ «እና ይሄ ትዝ ይለኛል» የሚል አባባል ከሰማ በኋላ ጥያቄ፣ አስተያየት ወይንም ተጨማሪ ተረክ እንዲከወንለት መጠየቅ እንጂ የመጀመሪያው ትረካ ማለቁን የሚጠራጠርበት መሰረት የለውም። ስለዚህም የናሙና ግለተረክ ቁጥር ሁለት ኮዳ ተራኪው የመናገር ተራውን በግልጽ ሁኔታ ለታዳሚ የለቀቁበት ነው።

በዚህ የትንተና ምዕራፍ ንኡስ ክፍል ከኮሪያ ዘማቾች በተገኙ ሁለት ናሙና ግለተረኮች ላይ መዋቅራዊ ትንተና ቀርቧል። በአንድ ግለተረክ ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ ተብለው በስነተረክ አጥኚዎች ከሚታመኑት ስድስት ያህል መዋቅራዊ አሃዶች ውስጥ ናሙና ግለተረክ ቁጥር አንድ አራት፣ ቁጥር ሁለት ደግሞ አምስት ያህሉን ማካተታቸውን ተመልክተናል። በናሙና ግለተረኮቹ ውስጥ የሚገኙት መዋቅሮች የሚጠበቅባቸውን መቼትና ገጸተረክ የማስተዋወቅ፣ ገጸተረኮች የሚገቡባቸውን ፈታኝ ሴራዊ ሁነቶች የመግለጽ፣ ገጸተረኮች ከፈታኝ ሁኔታዎች ሲወጡ የማሳየት፣ ተራኪው ስለተረኩ ሁነቶች ያለውን ግላዊ ምዘና የማቅረብና የመናገር ተራው የታዳሚው መሆኑን የሚገልጽ አዋጅ የማቅረብ ሚናቸውን በአጥጋቢ መልኩ መወጣታቸውን አስተውለናል።

### 4.2 የኮሪያ ዘማቾች ግለተረኮች የጭብጥ ትንተና

በሚቀጥለው ክፍል ከኮሪያ ዘማቾች የተሰበሰቡ ግለተረኮች ጭብጥ ላይ ትንታኔ ይቀርባል። ከዘማቾቹ የተሰበሰቡት ግለተረኮች ሁለት ጭብጦች ያሏቸው ሲሆን እነሱም ተራኪዎቹ በኮሪያ ጦርነት ተልእኳቸው ወቅት በጋሬጣማ ሁነቶች ውስጥ አልፈው ተልእኳቸውን በስኬት መደምደማቸውን የሚያሳዩ ናቸው። የጭብጥ ትንታኔው አቀራረብ ተራኪዎቹ ያለፉባቸውን የኮሪያ ዘመቻ ሂደቶች ቅደም ተከተል መሰረት ያደረገ ነው። የሁለቱም ጭብጦች ትንታኔ በርካታ ንኡሳን ክፍሎች ያሉት ሲሆን ጭብጦቹን አጉልተው የሚያሳዩ ተተራኪ ሁነቶችን (narrated events) መሰረት በአደረጉ አንድ ወይንም ሁለት ናሙና ግለተረኮች ይደገፋሉ። የአንድን ግለተረክ ጭብጥ ለማዳበር ከሌሎች ግለተረኮች፣ መጻህፍት፣ ጋዜጦችና መጽሄቶች ሃሳቦች ተቀንጭበው ሊወሰዱ ይችላሉ።

### 4.2.1 የኢትዮጵያ ዘማቾችን ኮሪያ ጦርነት ተሳትፎ ጋሬጣማ ሂደቶች የሚያሳዩ ግለተረኮች የጭብጥ ትንተና

በዚህ ክፍል ከኮሪያ ዘማቾች በተሰበሰቡ ግለተረኮች ውስጥ በሚገኘውና በተልእኮው ጋሬጣማነት ላይ በሚያጠነጥነው ጭብጥ ላይ በናሙና ግለተረኮች የተደገፈ ትንታኔ ይቀርባል። በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ውስጥ ጋሬጣ የሚለው ቃል ኢትዮጵያን ወታደሮች በኮሪያ ጦርነት የተሰጣቸውን ተልእኮ በመፈጸም ሂደት በተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ሁነቶች ምክንያትነት ያጋጠሟቸውን የስሜት፣ የአካልና የአእምሮ ጉዳቶች ለመግለጽ የዋለ ነው። ከኮሪያ ዘማቾች የተሰበሰቡትና የኮሪያ ተልእኳቸውን ጋሬጣማነት የሚያሳዩት ግለተረኮች ከሽኝታቸው ጀምሮ እውደ ግንባር እስከገቡበት ድረስ ያለፉባቸውን ሁነቶች የሚተርኩት ሲሆኑ እነርሱም በአዲስ አበባው ሽኝታቸው፣ በመርከብ ጉዟቸው፣ ኮሪያ በገጠማቸው አቀባበልና በአነኒዷቸው ልምምዶች ላይ ያተኩራሉ።

#### 4.2.1.1 አሸባሪው ሽኝት

ከኮሪያ ዘመቻ ዓቢይ ሂደቶች ውስጥ ሽኝታቸው ተጠቃሽ ሲሆን ይህንኑ የተመለከቱ በርካታ ግለተረኮች ከዘማቾቹ ተሰብስበዋል። እነዚህ ሽኝት ተኮር ግለተረኮችም የጋሬጣ ጭብጥ በተለይ የሚንጸባረቅባቸው ናቸው። አንደኛው ቃኘው ሻለቃ ወደ ኮሪያ የተላከው በኦፊሴላዊና ህዝባዊ ሽኝቶች ነበር። ኦፊሴላዊው የሽኝት ስነ ስርዓት ሚያዚያ 4፣ ቀን 1943 ዓ.ም በጃንሜዳ የተካሄደ ሲሆን ንጉሡና ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ተገኝተውበታል (ቃኘው፣1998፡ 24)። ዘማቾቹ ከኦፊሴላዊው ሽኝት በኋላ እዛው ጃንሜዳ አደሩ። በበነጋታው ወደ ለገሀር ባቡር ጣቢያ ጉዞ አደረጉ። ጉዞው በአዲስ አበባ ከተማ ህዝብ የታጀበ ሲሆን እንደ ኦፊሴላዊው ሽኝት በርቶትን ያስነቀ ሣይሆን በዘማቾቹ ላይ አሸባሪ ስሜት የፈጠረባቸው ነበር። ይህንን ሁኔታ ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ ሚካኤል ሽኝታቸውን በተመለከተ እንዲተርኩልኝ ባቀረብኩላቸው ጥያቄ ተስቶሽንት ከሰጡት ግለተረክ መረዳት ይቻላል።

> እሱ ነው ትልቁ መልእክት ላስተላልፈው ምፈልገው። በውነቱ እኛ ሚያዝያ ሶስት ተመረቅን። ሚያዝያ አራት ከቤተመንግስት ወይም ከኢትዮጵያ ህዝብ ጃልሜዳ በሰልፍ ተሰናበትን። አዳር እዛው ሆነ። አልወጣንም። እዛው ከሰልፍ መጥተን እዛ ምግባችን እራት ሁሉ ተዘጋጅቶልናል። እዛ አደርን። በውነቱ የማይረሳ በህይወት ዘመን ያ ቀን ነው። እንኳንስ አዲስ አባ ያለው ህዝብ ይቅርና ከአካባቢ ጭምር መጥቶ ጃልሜዳን ከበባት። ሌሊት ልቅሶ በልቅሶ ነው።እኛ ውስጥ ነው ያለነው። የማይዘምተው ጦር አጥሩን ከቦ ሰው እንዳይገባ ይከለክላል። ሬሣ እንደሚሸኙ ለቅሶ ነበረ። ከፍተኛ ሽብር ተሰማን። በውነቱ እንደማንመለስ ያን ጊዜ ነው ጦርነቱ የገባን ማለት የሚቻለው። እና ሌሊት እዛው አደርን። እና ህዝቡ መንገድ ከጃልሜዳ ጀምሮ እስከ ለገሐር ድረስ ግራና ቀኝ ተሰልፎ እያለቀሰ ነው የሸኘን። መጥፎ ነበር በውነቱ፡ እጅግ በጣም አሸባሪ ነበር (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ ሚካኤል፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክሪብ ገጽ 3፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)።



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

በዚህ ናሙና ግለተረክ ኢትዮጵያውያኑ ወታደሮች የኮሪያ ተልእኳቸውን የጀመሩት የአዲስ አበባ ህዝብ በአደረገላቸው አሸባሪ ሽኝት ነው፡፡ ተራኪው በኮሪያ ዘመቻቸው አነሳስ ላይ ያጋጠማቸውን ሽኝት «በውነቱ እንደማንመለስ ያን ጊዜ ነው የገባን» (ዝኒ ከማሁ)፡፡ በማለት እጅግ አሉታዊ ስሜት ፈጥሮባቸው እንደነበር ገልጸውታል (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ ሚካኤል፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 3፣ ነሐሴ. 10፣ 1999 ዓ.ም)፡፡ በሌላ አገላለጽ እንደኛ ቃኘው ሻለቃ ላይመለስ የሚሄድ ጦር መሆኑን አውቆ ነበር የተነሣው ለማለት ያስችላል፡፡ ይህ ደግሞ የዘማቾቹን ስሜት ሊጎዳ እንደሚችል መገመት አይከብድም፡፡ ከኮሪያ ዘማቾች ያገኘኋቸው ግለተረኮች እንደኛው ጭብጥ የሆነው የጋሬጣ ጉዳይ የጀመረው ወታደሮቹ ገና ሃገራቸውን ሳይለቁ በተደረገላቸው አሸባሪ አሸኛኘት ነው፡፡ የሽኝታቸውን አሸባሪነት መሰረት ያደረገና የተልእኳቸውን ጋሬጣማነት በጭብጥነት የያዙ ተጨማሪ ግለተረኮች በስብስብ ላይ በቁጥር 1፣ 2 እና 3 ስለሚገኙ አንባቢው እንዲመለከታቸው ተጋብዟል፡፡

4.2.1.2 ፈታኙ የመርከብ ጉዞ

ቀጥሎ የተራኪዎቹን የኮሪያ ተልእኮ ጋሬጣማነት በጭብጥነት የያዙና ከጅቡቲ ወደብ ተነስተው ደቡብ ኮሪያ ወደብ እስከደረሱበት ያለፉባቸውን ሁነቶች መሰረት ያደረጉ ግለተረኮች የጭብጥ ትንታኔ ይቀርባል፡፡ ግለተረኮቹ ተራኪዎቹ የተሳፈሩበት መርከብ በፈጠረባቸው አገሬ ሞት፣ ጉዟቸው ለጤና ተስማሚ አለመሆኑንና ከመሃላቸው አንዱ በጉዞ ላይ መሞቱን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡

4.2.1.2 የመርከቡ አግራሞት

ተሸብረው ከሀገራቸው የወጡት ወታደሮች በባቡር ተጉዘው ጅቡቲ ይደርሳሉ፡፡ ጅቡቲ ሁለት አዲስ ነገር ይገጥማቸዋል፡፡ ተራኪዎቹ ኮሪያ እንዲገዙ የቀረበላቸው መጓጓዣ ፈጽሞ የማያውቁት እንደነበር ግለተረኮቻቸው ያሳያሉ፡፡

> መርከብ ከዚያን በፊት አላየንም፡፡ ሁላችንም ወደዚያ የሄድነው አላየንም፡፡ ግን በምናይበት ጊዜ መርከቡ ግዙፍ ነገር ነው፡፡ ባህር ላይ ውሀ ላይ ቆሟል፡፡ ይሄ ነገር ውሃ ላይ እንዴት ሊቆም ቻለ? ብለን ይገርመን ነበር (መቶ አለቃ ታደሰ ገብረ ክርስቶስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 3፣ ነሐሴ. 6፣ 1999 ዓ.ም)፡፡

4.2.1.2.2 ጤና ነሺው የመርከብ ላይ ቆይታ

ከኮሪያ ዘማቾች ከተሰበሰቡ ግለተረኮች ውስጥ የመርከብ ጉዟቸው ከምግብ ጋር በተያያዘ ለጤናቸው ተስማሚ ያልነበረ መሆኑን መሰረት ያደረጉና የጋሬጣ ጭብጥ ያላቸው በርካቶች ናቸው፡፡ በትድሚያ ግን አመጋገባቸውን በተመለከተ ይቀርቡላቸው የነበሩትን ምግቦች ወደዋቸው እንደነበር መጥቀስ ይገባል፡፡ ኢትዮጵያውያኑ ዘማቾች እንደነሱው በኮሪያ



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ጦርነት ለመሳተፍ በጉዞ ላይ ከነበሩ ከግሪክና ሆላንድ ወታደሮች ጋር ተገናኙ:: ምግባቸው ለተቀላቀሏቸው የሌሎች ሃገራት ወታደሮች ከሚቀርበው ጋር ተመሳሳይ ነው:: ለእነሱ ተብሎ የሚዘጋጅ ምግብ አልነበረም:: የተባበሩት መንግስታት ለሰላም ማስከበር ተልዕኮ ከተለያዩ አባል ሃገራት እያውጣጣ በሚልካቸው ወታደሮች መካከል በርካታ ከምግብ ጋር የተያያዙ ችግሮች እንደሚስተዋል ጸሀፎች ይጠቁማሉ:: "Food problems were numerous: Pakistanis need to have their chicken killed in a certain way; Arabs would not eat Israeli jam; Norwegians would not eat Portuguese sardines; and so on." (Doorn 1968:364) ፓኪስታኖች የሚመገቧቸው ዶሮዎች በልዩ መንገድ እንዲታረዱላቸው ይፈልጋሉ፤ አረቦች እስራኤል ሀገር የተመረተ ማርማላታ አይበሉም፤ ኖርዌያውያን ፖርቱጋል ውስጥ የተዘጋጀ ሰርዲን አይመገቡም፤ ወዘተ::

ይህ የአንደኛው ሃገር ወታደሮች ከእነርሱ ባህል ውጪ የሚቀርብላቸውን ምግብ ለመመገብ የሚቸገሩበት ሁኔታ በኢትዮጵያውያኑ ዘማቾች ላይ አልታየም:: ዘማቾቹ የማያውቋቸው የምግብ ዓይነቶች ቢቀርቡላቸውም አብዛኞቹን ወደዋቸዋል (ኮሎኔል ገብረ አረጋዊ ሚካኤል፤ ቃለ መጠይቅ፤ ካሴት ቁጥር አንድ፤ ስርክብ ገጽ 4፤ ነሐሴ 10፤ 1999 ዓ.ም)፡፡ የእነርሱ ችግር የነበረው የቀረበላቸው ምግብ ዓይነት ሳይሆን ምግቡን ተመግበውት ሆዳቸው ውስጥ አልረጋ ማለቱ ነው:: ይህንን ሁኔታም ቀጥሎ ከቀረበው ናሙና ግለተረክ መረዳት ይቻላል::

> መርከቡ ትልቅ መርከብ ነው እንግዲህ ከሌላ ቦታ ደርሶ ነው እኛን ለመውሰድ የመጣው:: የግሪክ ወታደሮች አሉ:: ሆላንዶችም አሉ:: እና እያሠባሠበ ነው:: ትልቅ መርከብ ነው:: ምድር ቤት አለው:: ወደ ታች በጣም ይሞቃል፤ ውስጥ:: እና እኛ መኮንኖች መሀከላቸው ላይ ነን:: ወታደሮችን ለመጎብኘት ከታች ነው:: ከላይም ደግሞ እንደዚሁ መናፈሻ አለው:: እዚያ ላይ ይደረጋል:: እና እንግዲህ የመጀመሪያ ግዜያችን ስለነበረ የባሕር ማእበል አለ:: እና ይሄ በጣም አንዳንድ ግዜ ከፍ ይላል እንዴ ይወርዳል:: ወደ ታች ወደ ላይ በሚልበት ጊዜ ብዙ ከእኛ መሀከል መኮንኖችም ወታደሮችም መቋቋም አልቻሉም:: ያስታውካሉ:: እንትን ያደርጋል:: ሙቀቱ ደግሞ በኃይል ነው:: ውስጥ ሲገባ ይሞቃል:: ወደ ላይ ሲወጣ እንደው እንደ እንትን ያደርጋል:: እንዲሁ እያልን ሃያ አንድ ቀንና ሃያ አንድ ሌሊት ነው የተጓዝነው (ብርጋዲየር ጀኔራል ደስታ ገመዳ፤ ቃለ መጠይቅ፤ ካሴት ቁጥር 1፤ ስክርብ ገጽ 5፤ ነሐሴ 23፤ 1999 ዓ.ም)::

ይህ ናሙና ግለተረክ ተራኪዎቹ የመርከብ ጉዞ ላይ ያሳለፉት ቆይታ ጤና የሚነሳ እንደነበር የሚጠቁም ነው:: የተረኩ ሁነት ተራኪዎቹ የኮሪያ ተልእኳቸውን ለመፈጸም በመርከብ ያደረጉት ፈታኝ እንደነበር ያሳያል:: ይህንኑ ጭብጥ በሚያጠናክር ሌላ ግለተረክ ውስጥ በመርከብ ላይ ቆይታቸው ለጦርነት የማይመጥን ተክለ ሰውነት እስኪይዙ ድረስ ተጎድተው እንደነበር ፍንትው አድርጎ በሚያሳይ መልኩ እንዲህ ገልጸውታል:: «ወታደሮች

በጣም ተጉግቶለዋል:: መቼም ከመርከብ ሲወርዱ አሜሪካኖች ሲያዩን እውነት እነዚህ ምን ሊዋጉ ነው? የሚል ንቀት ማያድርባቸው አልቀረም::» (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር አንድ፣ ስክርብ ገጽ 8፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም):: በአጠቃላይ ኢትዮጵያውያኑ የሳምንታት የመርከብ ጉዞ ጤናን የሚነሳና አጎሳቋይ እንደነበር ግለተረኮቻቸው በጭብጥነት አሳይተዋል::

### 4.2.1.2.3 የባልደረባን ሬሳ ባህር ለመጣል መቃጣት

ከኮሪያ ዘማቾች ግለተረኮች ውስጥ የተልእኳቸውን ሂደት ጋሬጣማነት በጭብጥነት ለያዙ በርካታ ግለተረኮች መሰረት የሆነው ሁነት አንድ ኢትዮጵያዊ ዘማች በመርከብ ጉዞ ላይ መሞቱ ነው:: ይህንን ሁነት መሰረት ከአደረጉ ግለተረኮች ውስጥ አንደኛው በመዋቅራዊ ትንታኔ ክፍል የተመለከትነው ናሙና ግለተረክ ቁጥር አንድ ሲሆን ሌላው ደግሞ ተከታዩ ነው::

> አአአ! እንዲያውም ጥሩ ጥያቄ ነው ያመጣኸው:: ወታደሮቹ የማዕበሉ መገለባበጥ በጣም እ ታመሙ:: ኋላ አንድ ወታደር ሞተብን መርከብ ላይ:: በአሜሪካኖች ህግ መርከብ ላይ የሞተ ወታደር ወይንም ሰው ባህር ይጣላል እንጂ ሬሳ ተጉዞ አይሄድም በህጋቸው:: ከዛ ኋላ የእኛ ወታደር ገንዘው ኧኧኧ ባህር ለመጣል እ እኔ ተጠርቼ እንደ አጋጣሚ ሻምበል አዛገፍና ጄኔራል መርዕድ ግዛው ይባላሉ:: እምና ሞቱ:: እሳቸው እ ጥሩ ምክር መከሩኝ:: «ከቫሻምበሉ አንድ አንድ ጓድ ይመጣልህልና ወታደሮቹ እንዲያድሙ አርጋቸው:: እንዴት! የወንድማችን ሬሣ አናስጥልም:: ዓይናችን እያየ ባህር አይጣልም:: ወታደር ወንድማችን::» ብለው «እንዲያድሙ አድርግ::» አሉኝ:: /ፒፕሲና የንብስ ቆሉ እየቀረበልኝ ስለነበረ ቀርቦልኝ እስኪያልቅ ዝም አሉ/ አድርግ አሉኝ:: ከዛ በኋላ እ ወታደሮቹ ተሰበሰቡና ለወታደሮቹ ይኸን ነገርኳቸው:: እ በእውነቱ የሚደንቅህ ነገር እ ውስጥ ለውስጥ ይሄ ነገር ለአንድ ሀምሳ አለቃ የኔ የነበረው ለሱ ነገርኩትና እሱ እንዲያሳድማቸው አድርጌ ወደሚጣልበት ዴክ እንሱን ታች ትቼ ላይ ዴክ ነው እኔ የተዘጋጀው ሬሣው ወጥቼ እ ወታደሮቹ እምቢ አሉኝ አልኳቸው:: ነገርኳቸው ለሻለቃ አዛዡ:: ሻለቃ አዛዡ በቀጥታ «እኔ ምን ላድርግ? ወታደሮቹ ሬሳው እንዳይጣል ብለውኛል::» ብለው ተናገሩ:: እና ሬሣው በዚህ አስጣልነው እና የመጀመሪያ በረዶ ውስጥ ገብቶ ሳጥን ላይ ኮሪያ ደረሠ:: መጀመሪያ አፈር ውስጥ የገባ ኮሪያ የኢትዮጵያ ወታደር መርከብ ውስጥ የሞተው ነው (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር አንድ፣ ስክርብ ገጽ 5-6፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)::

ይህ ናሙና ግለተረክ የአዲስ አበባ ህዝብ በአሸባሪ ሽኝት ከላካቸው ወታደሮች ውስጥ አንደኛው በመርከብ ጉዞ ላይ እንዴት መሞቱን ይተርካል:: የሞቱ ምክንያት ቅድም የተገለጸው የጉዞው ጤና ነሺነት ለመሆኑ ናሙና ግለተረኩ በጅማሬው ላይ ፍንጭ ይሰጣል:: የባልደረባ ሞት ሊያስከትል የሚችለው ሀዘን እንደተጠበቀ ሆኖ የሟች ሬሳ አፈር የመቅመስ እድል መነፈጉ የናሙና ግለተረኩን ገጸተረኮች በእጅጉ አስቆጥቷል::

በባህር ላይ የሞተ ወታደር ወደ ባህር መጣል አለበት የሚለው የአሜሪካ ባህር ሀይል ህግ በኢትዮጵያን ዘማቾች ወታደራዊ ህግና መመሪያ ላይ የሌለና የማያውቁት ነው። በመሆኑም ህጉ ተፈጻሚ ይሆንባቸው ዘንድ አልፈቀዱም። በዚህም ለአንድ አላማ በተሰለፉ የተለያዩ ሃገራት ወታደሮች መሀል የወታደራዊ ደንብ አቀባበልና አተገባበር ልዩነት ተከስቷል። ይህ ሁነት ምናልባትም ኢትዮጵያውያን ዘማቾች ከሌሎች ሃገራት ወታደሮች ጎን በሙሉ እምነት ተሰልፈው የተላኩበትን አላማ መፈጸም ስለመቻላቸው ስጋት ሣያሳድርባቸው አይቀርም። ይህ ደግሞ ተልእኳቸውን ለማሳካት ጋሬጣማነት ተጨማሪ ምክንያት ይሆናል።

በአሸባሪ ሸኙት ከሀገራቸው የወጡት፣ ለመጀመሪያ ጊዜ መርከብ በማየታቸውና በመሳፈራቸው የተገረሙት፣ የባህር ላይ ጉዞው ያንሳቆላቸውና በጓደኛቸው ሬሳ ወደ ባህር ሊጣል መቃጣቱ ያስቆጣቸው ተራኪዎች የኮሪያ ወደብ አቀባበላቸውም ቢሆን ሰላማዊ አልነበረም።

### 4.2.1.3 አስደንጋጩ የፑሣን አቀባበል

የኢትዮጵያውያን ወታደሮች የኮሪያ ዘመቻ ጋሬጣዊ ጉዞ አሁንም ቀጥሏል። ከገለተረኮቻቸው መረዳት እንደሚቻለው የደቡብ ኮሪያ ፑሣን ወደብ የደረሱት ማታ ነበር። የተሳፈሩት የጦር መርከብ መሀልቋን መጣል ለፈታኙ የባህር ጉዟቸው መደምደሚያ ብስራት እንዳልነበረ ቀጣዩ ናሙና ግለተረክ ያሳያል።

> የደረስነው ለሊት ነው፣ ወደ ዘጠኝ ሰዓት ከሌሊቱ። መሬት ይቀልጣል ተኩሱ፣ መድፉ፣ ምን ምን ይቀልጣል። ይሄን ጊዜ «እንዴ! ጦር መሣሪያ ሳንይዝ ነው እሳት የከተቱን ወይ?» አልንና ደነገጥን እኛ። «ባዶ እጃችንን ልናልቅ ነው ወይ እዚህ መርከብ ላይ?» አልን። ለካስ እሱ ልምምድ ኖሯል። ቀድመውን የገቡት የጦር ልምምድ ነው እንጂ ጦርነት አልነበረም (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር አንድ፣ ስክርብ ገጽ 7፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)።

ናሙና ግለተረኩ ለእግረኛ ውጊያ የመጡት ወታደሮች ባህር ላይ ሳሉ ውጊያ ወረዳ ውስጥ ራሳቸውን በማግኘታቸው ለከፍተኛ ሽብር መዳረጋቸውን ያሳያል። ግለተረኩ በተደጋጋሚ እንዳዩናቸው ሁሉ ጋሬጣ ጭብጥ ያለውና ተራኪዎቹ ተልእኳቸውን ለመፈጸም ያለቀበትን ተጨማሪ ፈታኝ ሁኔታ የሚያስረዳ ነው።

### 4.2.1.4 ትራጂኮሚያዊው የልምምድ ላይ ሁነት

ኢትዮጵያውያን ዘማቾች ከመነሻቸው ጀምሮ ኮሪያ እስኪደርሱ ድረስ ያለፉባቸውን ሂደቶች በሚያሳዩ ግለተረኮቻቸው ውስጥ የጋሬጣ ጭብጥ ጎልቶ እንደሚገኝ እያየን መጥተናል። ኮሪያ ደርሰው በተሳተፉባቸው ልምምዶች ላይም ቢሆን ፈታኝ ሁነት አጋጥሟቸዋል። ኢትዮጵያውያን ወታደሮች የጦር ልምምድ ከመጀመራቸው በፊት ለኮሪያ ጦርነት የሚገለገሉባቸውን የጦር መሣሪያዎች ተረከቡ። እነዚህን ከመሣሪያዎቹ ጋር

ለመስማመድም ወደ ደቡብ ኮሪያ ገጠራማ አካባቢዎች አቀኑ፡፡ በልምምድ ላይ ሳሉ ትራጂዲያዊ ሊሆን ሁነት ተዳርገው እንደነበር ቀጣዩ ናሙና ግለተረክ ያሳያል፡፡

> እንግዲህ፣ መጀመሪያ መሣሪያ መፍታትና መግጠም ነው፡ እንደ ወታደር ህግ፡፡ እያንዳንዱን መሣሪያ መፍታት መግጠም ትምህርት ተማርን፡፡ ከዛ ኋላ ዒላማ ወረዳ ተኩስ ጀመርን፣ በየምድቡ ማለት ነው፡፡ ያው የእግረኛ ጦር መሣሪያ ነው የታጠቅነው፡፡ እና እሱ ኧ እንኳን ጊዜ አልወሰደብንም፡፡ ከዛ በኋላ የእግረኛ ትምህርት ወደ ገጠር ከዛ ከፑዛን ወጥተን የእግር ጉዞ ጀመርን፡ ልምምድ፡፡ ነገር ግን፣ አሁን አደጋ ተፈጠረ፡፡ ልምምድ ላይ እንዳለን በሻለቃ ማጥቃት በምናደርግበት ጊዜ ኧ እኔ ከፊት አጥቂ የመቶ ስለሆንኩ እግረኛ የመቶ ስለሆንኩኝ ኧ ለማጥቃት ወደ ፊት ሄጄ እርዳታ ክፍሉ ሁሉ ከኋላ ተሰልፏል፡፡ ልክ እንደዚህ ቤት ወንዝ አለ፡፡ ይህንን የሚያህል ከፍታ ያለው ወንዝ፡፡ እዚህ ላይ ትልቅ ዛፍ ነበረ፡፡ ከኋላ የተተኮሰው የወገን ጥይት የልምምድ ለልምምድ የተተኮሰው ይሄን ዛፍ መታና እንዳለ ላያችን ላይ ረገፈ፡፡ ጦሩ እንዳለ ረገፈ፡፡ እኔም ተመታሁ እዚህ ላይ፣ ይሄው ፍንጣሪ አለች፡ ተሸክሚያት እዞራለሁ በህይወቴ፡፡ እና ሁለት ወታደሮች ሞቱብኝ፡፡ ኧ ከዛ /አሳለ/ ኧ ከዛ አሁን ኧ ሌላው ግን ያልተጫረ አንድ ወታደር የለም፡፡ ሠላሳ አምስቱ በሙሉ ተጭሯል፡፡ እና ወደ ሆስፒታል ወዲያው ጦሩን ይገፉ ወደ ሆስፒታል ሄድኩኝ፡፡ ከልምምዱ ውጭ ሆንኩኝ (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር አንድ፣ ስክርብ ገጽ 8፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)፡፡

ይህ ናሙና ግለተረክ የተራኪዎቹን የኮሪያ ተልእኮ ጋሬጣማነት የሚያሳይ ጭብጥ ያለው ሲሆን ተተራኪ ሁነቱ ዘማቾቹ በልምምድ ሜዳ ያውም ከወገን በተተኮሰ ከባድ መሳሪያ የተመቱበትና ጥቂቶቹም ህይወታቸውን ያጡበት ነው፡፡ ከሌላ ተራኪ የተሰበሰበ ግለተረክም ቢሆን ኢትዮጵያውያኑ ወታደሮች የልምምድ ወቅት የተደናገጡበትን ሁነት የሚተርክ ነው፡፡

> የእግር ጉዞ ደግሞ አለ ፑሳን፡፡ አንድ ጫካ አለ፡፡ ያ ገደልና ገደል ነው፡፡ በዛ ጉዞ ተባለ (አልተሰማኝም) ከዚያ ስንማር አንድ ባርኔጣ ይወድቃል፡፡
> የማን ? [ጠያቂው]
> የእኛ፣ ከእኛ ውስጥ፡፡ ድንጋይ ይፈነቀልና በኋላ ያው ተኩስ ከፊትን ጠላት መጣ ብለን፡፡
> እንዴት? [ጠያቂው]
> ድንጋይ ሲወ ሲወ ሲወርድ እየተንኳኳ ወረደ ሻምበል ጤና ይስጥልኝ [በአጠገባችን ከሚያልፍ ሰው ጋር ሰላምታ ተለዋወጡ] ያ ባርኔጣ፣ ብረት ባርኔጣ ነው፡ ከአንድ ወታደር ላይ ይወድቃል፡፡ ያ፣ ኳ ኳ ኳ ሲል ድንጋይም አብሮ ኳ ኳ ኳ ይላል፡፡ «ጠላት መጣ» አልንና ቶክስ ከፈትን፡፡ ሜዳውን ሊሲቱን ጨረታ አስመስለን፡፡ አሁን «ኢትዮጵያውያኖች ምን ገጠማቸው? እ!» ተባለ፡፡ «ምን ገጠማቸው?» ተባለ፡፡ እ እነጀነራል አይዘንሃወር ምን ምን መጡ፡፡ እንግዲህ አማን መሆም ያቃል ነበዝ ነው፡፡ ሰበኩቸው፡፡ «በቃቸው እነሱ» አስራ አምስት ቀን ጉዞ ቀረና «ተመለሱ» ተባለ፡፡ «ተመለሱ» ተባልን፡፡ «እነዚህ ሀይለኞች ናቸው» ተባልን፡፡ አሁን እንግዲህ ተለማምደናል፡ ገባን፡፡ ከዚያን በኋላ ሁለት ቀን አድረን ከዚያን በኋላ ባቡር መጣ፡፡ ጉዞ ቀጠልን (አስር አለቃ አሰፋ አስፋው፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 7፣ ሐምሌ 10፣ 1999 ዓ.ም)፡፡



IES LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

ይህ ግለተረክ ተራኪዎቹ በልምምድ ላይ የተደናገጡበትን አጋጣሚ የሚያሳይ ሲሆን በተፈጠረው ሁኔታም አሚሪካውያኑ አሠልጣኞቻቸው ግራ መጋባታቸውን የሚያስረዳ ነው፡፡ የተፈጠረውን ችግር ለመፍታትም የአንደኛው ቃኘው አዛዥ የነበሩትን የሌተና ኮሎኔል አማን አንዶም ጥረት ጠይቋል (ቃኘው፣1994፣9)፡፡ እስካሁን በቀረበው ትንተና ኢትዮጵያውያኑ ዘማቾች ከአዲስ አበባ ከተሸኙበት ቅጽበት ጀምሮ ኮሪያ ደርሰው ልምምድ ማካሄድ እስከጀመሩበት ድረስ ያለፉባቸውን ፈታኝ ሁነቶች መሰረት ባደረጉ ግለተረኮቻቸው ውስጥ የተልእኳቸውን ጋሬጣማነት የሚያጸና ጭብጥ በተለያዩ መልኮች ሲደጋገም አስተውለናል፡፡ ቀጥሎ ደግሞ የኮሪያን ተልእኮ ስኬታማ አፈጻጸም የሚያሳይ ጭብጥ ባላቸው ግለተረኮች ላይ የተካሄደው ትንታኔ ይቀርባል፡፡

### 4.2.2 የኮሪያ ዘማቾች ግለተረኮች የስኬት ጭብጥ

በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ እንደተጠቀመው ከኮሪያ ዘማቾች የተሰበሰቡት ግለተረኮች ሁለት አቢይ ጭብጦች ያሏቸው ሲሆን አንደኛው ቀደም ብለን ያየነውና በበርካታ ግለተረኮቻቸው ውስጥ የሚደጋገመው ተልእኳቸውን ለመፈጸም በጋሬጣማ ሁነቶች ውስጥ የማለፋቸው ጉዳይ ነው፡፡ ሁለተኛውና ቀጥሎ የምንመለከተው ከኮሪያ ዘማቾች በተሰበሰቡ ግለተረኮች ውስጥ ጎልቶ የሚታየው ጭብጥ ተልእኮን በማሳካት ላይ ያተኩራል፡፡ ይህንን ጭብጥ ያቀፉትን ግለተረኮች ተተራኪ ሁነቶች ስንመለከት የተልእኳቸውን ጋሬጣማነት የሚያሳዩት ሁነቶች ከአበቁበት የሚጀምሩ ናቸው፡፡ ይኸውም የመጀመሪያዎቹ ሁነቶች ከዘማቾቹ የአዲስ አበባ ሽኝት ጀምረው ደቡብ ኮሪያ የጦር መሳሪያ ልምምድ እስከጀመሩበት ድረስ የነበሩ ሲሆን ሁለተኛዎቹ ግን ልምምድ ጨርሰው ወደ ጦር ግንባር ከገቡበት ቅጽበት የሚጀምሩ ናቸው፡፡

በምእራፍ ሶስት ትውፊቂ ዳራ ውስጥ የተተራኪነትን ጽንሰ ሃሳብ በተመለከተ አስደናቂ ወይንም ያልተለመዱ ሁነቶች በተረክ ርእሰ ጉዳይነት በአንጻራዊነት የተሻሉ እጩዎች ተደርገው በስነተረክ አጥኚዎች እንደሚወሰዱ አይተናል፡፡ በዚሁ ጉዳይ ዙሪያ ሮቢንሰን የተባለ የግለተረክ አጥኚ እንዲህ ብሏል "Personal narratives will often recount an achievement, triumph of the actor over untoward circumstances." (Robison 1981፣60) አብዛኛውን ጊዜ ግለተረኮች የገጸተረኮችን በፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ የማለፍ ስኬት የመተረክ ዝንባሌ አላቸው፡፡ ይህንን የግለተረኮች ጠባይ መሰረት አድርገን ከኮሪያ ዘማቾች የተሰበሰቡትን ግለተረኮች ስንመለከት የዘማቾቹን የኮሪያ ጦርነት ጀብዱዎች የሚተርኩ በርካታ ግለተረኮች ይገኛሉ፡፡

የስኬት ጭብጥ ያላቸው እነዚህ ግለተረኮች በሁለት ዓቢይ ሁነቶች ላይ ያተኩሩ ሲሆኑ እነሱም ግዳጅን መወጣትና ምርኮን የተመለከቱ ናቸው፡፡ ይህንን ጉዳይ ቀጥለን በስፋት የምንመለከተው ይሆናል፡፡



ILLS LIBRARY
ADDIS ABABA UNIVERSITY

#### 4.2.2.1 ግዳጅን መወጣት

የኢትዮጵያ ወታደሮች ደቡብ ኮሪያ ደርሰው የጦር መሳሪያ ልምምድ እንደጨረሱ በሰሜንና ደቡብ ኮሪያ ድንበር ላይ በሰፈረው የአሜሪካ ሰባተኛ ክፍለ ጦር፣ ዘጠነኛ ኮር፣ ሰላሳ ሁለተኛ ብርጌድብ፣ አራተኛ ሻለቃ ስር ተሰለፉ (ቃኘው 1994:9)። ነገር ግን የተቀላቀሏቸው የአሜሪካ ጦር አዛዦች ሃበሾቹ ለኮሪያ ጦርነት የሚመጥኑ መሆናቸውን ተጠራጥረው እንደነበር ብርጋዲየር ጀኔራል ደስታ ገመዳ ገልጸዋል። ይህንን ጉዳይ በወቅቱ በደቡብና በሰሜን ኮሪያ ድንበር ላይ የነበረውን የጦር አሰላለፍ በአካተተው የጀኔራሉ ትረካ ውስጥ እናገኘዋለን።

> የኮሪያ ግንባር እንደመቀነት ነው፤ ከምስራቅ እስከ ምእራብ ድረስ። እንዲህ እንዲህ [ወገባቸውን እያመለከቱ]። መቀነቱ ጎኑ ልክ የኮሪያ ሼፕ [ቅርጽ] አለው። ወገቡ ላይ ያለው እንዲህ ነው። ዩናይትድ ኔሽን [የተባበሩት መንግስታት] የያዘው ግንባር ክፍት የለም። ክፍት የለም። እንደ እንትን ነው በቃ። እዛ ላይ ሁሉ ዝግ ነው። አንድ ክፍት እዚህ መሀከል በጭራሽ አይኖርም። ምክንያቱም ኧኧኧ በመጀመሪያ ጊዜ እኛ ከመድረሣችን በፊት ኧኧኧ የተባበሩት መንግስታት የአሜሪካንም ጦር እንደዚሁ አልፎ አልፎ ነው ሚይዘው [የሚሰፍረው]። በኋላ ግን ሜዳ ሜዳ ነው እነሱ ሲይዙ የነበረ። አሁን ቻይናዎችና ሰሜን ኮሪያዎች እንትኖች ይሄንን አጥንተው ወደ ተራራ እየወጡና እንትን እያረጉ መሀል መሀል እየገቡ ብዙ ጊዜ ጉዳት እያደረሱ እስከ ፑዛን [በደቡብ ኮሪያ ደቡባዊ ጫፍ ላይ የሚገኝ ወደብ] ድረስ ገፍተዋቸው ነበር፤ እኛ ከመድረሳችን በፊት። ከዚያ በኋላ ይሄ ጥናት ተወሥደና ዝግ ነው፤ በምንም መንገድ ማንም አይሾልክም። እና፣ ሁለተኛ ደግሞ ተራራ ላይ አልነበሩም። አሁን በኋላ ላይ ወደ መጨረሻ ከፍተኛ ቦታዎች ይያዝ ነበር። ምክንያቱም ከፍተኛ ቦታ ምንም ጊዜም ብትይዝ አንተ የበላይ ነህ፤ ወደ ታች ታያለህ። አንዱ ለማጥቃት ሲመጣ ከታች ወደ አንተ ነው እንጂ የሚመጣ እንትን ነው ይሄ ጠቃሚ ስለሆነ ከፍተኛ ቦታዎች በሙሉ ይያዙ ነበር፤ በዚያን ግዜ። እና፣ አሁን ይሄንን እንግዲህ ምናልባት እኛን የኢትዮጵያን ጦር አንድ ግንባር ሠጥተናቸው ብናገባ ምናልባት በዛ በኩል ሾልከው ይገቡብናል ብለው አያምኑንም ነበረ። ገና አያውቁንም ነበር። ገና አያውቁንም፤ አላወቁንም (ብርጋዲየር ጀኔራል ደስታ ገመዳ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 7፣ ነሐሴ 23፣ 1999 ዓ.ም)።

ይህ ገለጻ የተባበሩት መንግስታትን ጦር የመምራት ሀላፊነት የተሰጣቸው የጦር አዛዦች ለኢትዮጵያውያኑ ወታደሮች ድንበር የማስጠበቅ ሀላፊነት ለመስጠት አለመድፈራቸውን ያስረዳል። በዚህም ምክንያት አዛዦቹ የኢትዮጵያውን ጦር በሰሜን እና ደቡብ ኮሪያ ድንበር ላይ ከሚገኘው የአሜሪካ ክፍለ ጦር በስተጀርባ አሰፈሩት (ቃኘው፣1994፣9)። ድንበር የማስጠበቅ ሀላፊነትን ለመስጠት ወታደራዊ ግዳጅ የመወጣት ብቃታቸውን መፈተሽ ነበረባቸው። ለዚህም ሁለት ግዳጆችን የአቀረቡላቸው ሲሆን የመጀመሪያው ምርኮኛ እንዲያመጡ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የጠላትን አሰፋፈር እንዲሰልሉ ናቸው።



ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

#### 4.2.2.1.1 ምርኮ የማምጣት ግዳጅን መወጣት

በዚህ ክፍል በኮሪያ ዘማቾች ግለተረኮች ውስጥ በጉልህ የሚታየውን የስኬት ጭብጥ ምርኮ የማምጣት ግዳጅን ከመወጣት ጋር በተያያዘ በዝርዝር እንመለከታለን። ቀደም ብለን እንዳየነው የአሜሪካ አዛዦች ለኢትዮጵያውያን ወታደሮች ድንበር የመጠበቅ ሃላፊነትን ለመስጠት አመንትተዋል። ብቃታቸውን ለመፈተንም የጠላት ወታደር ማርኮ የማምጣት ግዳጆ ሰጧቸው። ይህንን ሁነት የሚያሳየውን ረጅም ግለተረክ በስብስብ ቁጥር 6 ላይ አንብቢው እንዲያነብ የሚጋበዝ ሲሆን አሁን ግን ጨምቁ ለማቅረብ እሞክራለሁ።

በኮሪያ ግንባር እስረኛ ለረጅም ጊዜ ባለመያዙ ኢትዮጵያውያን የተካተቱበት የአሜሪካ ጦር ስለጠላት ጦር አሰላለፍ መረጃ ያጣል። በዚህም መሰረት ከነበሩበት የጦር ሰፈር በቅርብ ርቀት ላይ ከሚገኝ የጠላት ሰፈር እስረኛ እንዲያመጡ ለኢትዮጵያውያን ወታደሮች ትዕዛዝ ይሰጣቸዋል። ተራኪዬ ብርጋዲየር ጄኔራል ደስታ ገመዳ ይህንን ተልዕኮ የማስፈጸም ሃላፊነት ይሰጣቸዋል። ምርኮኛ ባያገኙ እንኳ የጠላትን ምሽግ ደብድበው እንዲመለሱ ይነገራቸዋል። አንድ የመቶ ጦር ይይዙና ወደ ጠላት ሰፈር ይሔዳሉ። እዛም ይደርሱና በጠላት ሰፈር መዳረሻ ላይ በሚገኝ ወንዝ አጠገብ አድፍጠው ይጠባበቃሉ። በዚህ መካከል አንድ የቻይና ወታደር ከምሽጉ ወጥቶ ውሃ ለመቅዳት ወደ ወንዙ ይወርዳል። ተራኪዬ ለበታች ወታደሮች ቻይናውን የመያዝ ሃላፊነት ይሰጣሉ። ወታደሮቹም አምጥተው ያስረክባሉ ተራኪዬም የምርኮኛውን መያዝ ለአሜሪካ ጦር ያሳውቃሉ። እስረኛውን በአፋጣኝ ወደ ጠቅላይ ሠፈር እንዲልኩ ይገለጽላቸዋል። ይህንንም ያደርጋሉ። ቀጥለው የጠላት ሰፈር በከባድ መሳሪያ የማስደብደብ ሚና ይጫወታሉ። በዚህ ጊዜ የጠላት ጦር በአቅራቢያቸው መኖራቸውን በመረዳት የከፍተኛ መሳሪያ ተኩስ ያከፍትባቸዋል። ኢትዮጵያውያን ወታደሮች ተልዕኳቸውን ስለፈጸሙ በፍጥነት ወደ ኋላ ይመለሳሉ (ብርጋዲየር ጄኔራል ደስታ ገመዳ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 7-10፣ ነሐሴ 23፣ 1999 ዓ.ም)።

በዚህ መሠረት ተራኪዬ የሚመሩት ጦር ምርኮኛ የማምጣት ግዳጅን ይወጣል። ይህ አጋጣሚ ኢትዮጵያውያን የአሜሪካ ጦር የነበረበትን የመረጃ እጥረት እንዲሸፍን ያስቻለበት ሲሆን ለእነሱም የብቃት ማረጋገጫ ሆኖ ማገልገሉን መገመት ይቻላል። ይህ ተራኪዬ የሚመሩት ጦር የፈጸመው የጠላት ወታደር የመማረክ ተግባር የነበረው ዋጋ ከፍተኛ እንደነበር ይህንን ገጠመኝ ከሌላ አንጻር የተረኩልኝ ሌላ ዘማች «አሜሪካኖች ድንቅ የሆነባቸው ይህ ነው አንዱ። ተአምር የሆነባቸው አንዱ እሱ ነው።» በማለት ገልጸውታል (ኮሎኔል ገብረ አየለ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 29፣ ነሐሴ 10፣1999 ዓ.ም)

ኢትዮጵያውያን ወታደሮች ከሽንት ጀምሮ ጦር ግንባር እስከሰፈሩበት ጊዜ ድረስ ጉዟቸው የጋሬጣ እንደነበር አይተናል። ከላይ የሰፈረው ናሙና ግለተረክ ኢትዮጵያውያን ወታደሮች በኮሪያ ጦርንት ተሳትፏቸው ያስመዘገቡትን የመጀመሪያውን ስኬታማ የግዳጅ

አፈጻጸም የሚያሳይ ነው፡፡ ይሁንና ይህ ምርኮኛ የማምጣት ግዳጅ ስኬታማ አፈጻጸም ለኢትዮጵያውያን ወታደሮች መጀመሪያው እንጂ ብቸኛው አይደለም፡፡ ዘማቾቹ የኮሪያ ተልእኳቸውን አስመልክተው ከተረኩልኝ ግለተረኮች ውስጥ የጠላት ወታደር የማረኩባቸውን የተመለከቱ በርካታ አጋጣሚዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አንደኛው ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

> ሂርት ብሬክ ላይ [በደቡብና ሰሜን ኮሪያ ድንበር ላይ የሚገኝ ተራራማ ቦታ] ፓትሮል ተባለ [ፓትሮል የሚለው ቃል የጠላትን ጦር አሰላለፍ የመሰለል ተግባር የሚገልጽ ነው]፣ ኢንፎርሜሽን ጠፋ፡፡ ለዩናይትድ ኔሽንስ [ለተባበሩት መንግስታት] ኢንፎርሜሽን ሲጠፋ ፓትሮል ተብሎ ይሄዱና ኸ አንድ ወንዝ ጋር ደርሰው ይነጋል፡፡ ሲነጋ አንድ የቻይና ወታደር ልብሱን ሲያጥብ፣ አንቺ ነው የምንላቸው፣ አዎ ልብሷን ልታጥብ ወደ ወንዝ ትመጣለች፡፡ የእኛ ወታደር ለሊቱን ሄዶ ቦታ ተጠግቶ ፓትሮል ለማድረግ፣ እዚያ ይጠጋና አድፍጦ ይጠብቃል፡፡ ያቺ ቻይና ልብስ፣ ልብሷን አውልቃ ማጠብ እንደጀመረች አንድ ዘውዴ፣ ማነው? ከበደ፣ ከበደ ደፋር የሚባል [ዘውዴ ያሉት ከበደ ደፋር ለማለት ፈልገው ነው] እንዴት እንደዘለለ፣ እንዴት እንደሮጠ አይታወቅም ሄዶ ማጅራቷን ይይዛል፡፡ ወንዝ ዳር ማጅራቷን ይይዝና ትትቶ ስትፈራገጥ እንስ ካራቴም ይችላሉ፣ ካራቴም ለመምታት አልቻለችም፡፡ ማጅራቷን ጭምድድ አድርጎ ይዟታል፡፡ አንጠልጥሎ ሲመጣ ከቻይና በኩል መትረየስ፣ መድፍ፣ ምን ሁሉ ነገር ተለቀቀበት፡፡ እና ያቺን ቻይና ከነሕይወቷ ይዞ መጣ፡፡ ከሻለቃችን ወደ ሬጂሜንት [ብርጌድ] ወደ ዲቪዥን [ክፍለ ጦር] አስረከብን፡፡ ያቺ የተማረከችዋ ቻይና ጥሩ ኢንፎርሜሽን ነው የሰጠችው፡፡ ከእኛ ፊት ለፊት ያለው ማን ነው? ኸ ስንተኛ ዲቪዥን ነው? ኸ ምን ልበልህ፡ እና እንደዚህ ያለ ጀግንነት አለ (ኮሎኔል አለማየሁ ካሳ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 17፣ ነሐሴ 21፣ 1999 ዓ.ም)፡፡

ከዚህ ዳሙና ግለተረክ ሁለት ነገሮችን መረዳት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ተራኪዎቹ በኮሪያ ጦር ግንባር አምንቃዊ ሚና ይበልጥ መጫወትን መቀጠላቸው ነው፡፡ ይኸውም በኮሪያ ጦርነት በተቃራኒ ወገን ስለተሰለፈው የጠላት ጦር መረጃ በጠፋ ግዜ ምርኮኛ በማምጣት የመረጃ ክፍተቱ እንዲሞላ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ ይህ ደግሞ በኮሪያ ዘመቻቸው ከፈጸሟቸው ስኬታማ ተግባራት አንዱ መሆኑን ግለተረኩ በጭብጥነት የያዘው ነው፡፡ ሁለተኛው ነጥብ ተራኪው በዳሙና ግለተረኩ መጠናቀቂያ ላይ «እንደዚህ ያለ ጀግንነት አለ» ያሉትን የሚመለከት ነው፡፡ ይህ አባባል የጠላት ወታደርን መማረክ ጀግንነት መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡ ይህ ደግሞ በተራው ማራኪውን ወታደር «ጀግና» ብሎ ለመጥራት የሚያስችል ነው፡፡ ምርኮን በተመለከተ አንድ ተጨማሪ ግለተረክ ስብስብ ቁጥር 8 ላይ ስለሚገኝ አንባቢው እንዲመለከት ተጋብዟል፡፡

ዘማቾቹ ጠላት መማረክን አስመልክቶ ከእላቸው አቋም ጋር በተያያዘ አንድ የተለየ ክብሮኝ አላቸው፡፡ አንድ ኢትዮጵያዊ ወታደር በጦር ግንባር አድፋጭነት ስምሪት ላይ ሳለ

ADDIS ABABA UNIVERSITY I.L.S. LIBRARY

ለእያታ እስቸጋሪ በሆነ ጨለማ ውስጥ ምርኮ ለመጣል በነበረው ቁርጠኝነት የዱር አውሬ ማርኳል፡፡

> ዳባ ደግሞ አድፋጭ ወቶልሀል፡፡ አራተኛ ሻምበል ውስጥ ሲጠብቅ እየተሳበ፣ ቀስ እያለ ወዲህ ይመጣል፡፡ ዳባ ደግሞ ዝም ብሎ አድፍጦ፣ ጉብ ብሎ ይይዘዋል፡፡ ሲይዘው እንር ነው /ማት/፡፡ ቅጭም፣ ጉሮሮውን ይዞ ገደለው፣ ጠላት መስሎት፡፡ በእውነቱ በጦር ግንባር ስንት አስቂኝ ነገር ይገጥምሃል (ሎሌጌል ገብረ ኢየሱስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 2፣ ስክርብ ገጽ 30፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)፡፡

#### 4.2.2.1.2 የስለላ ተልዕኮን መወጣት

ከኮሪያ ዘማቾች ያገኘኋቸው ግለተረኮች የዘመቻቸውን ሂደት በመከተል ከሽኝታቸው ጀምር እስከ ኮሪያ ልምምዳቸው ድረስ በጋሬጣዊ ሁነቶች የተሞሉ እንደነበር አይተናል፡፡ ይህ ገጸታ ግን ቀደም ብለን በተመለከትነው የጠላት ወታደርን ማርኮ የማምጣት አጥጋቢ አፈጻጸም ተከትሎ መቶየርና አምንታዊነት ማሳየት እንደሚጀምር ተጠቁሟል፡፡ ቀጥሎም የስኬት ጭብጥ ያለውን ናሙና ግለተረክ እንመለከታለን፡፡ ይህ ግለተረክ ረጅም በመሆኑ ስላልተጠቀሰ አንባቢው በቅድሚያ ከሰብስቡ ላይ ቁጥር 19 እንዲመለከት ተጋብዟል፡፡

ይህ ግለተረክ የኢትዮጵያውያን ወታደሮች በኮሪያ ጦርነት ተሳትፏቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ከጠላት ጋር ፊት ለፊት ውጊያ የገጠሙበትን አጋጣሚ የሚያሳይ ሲሆን ጨመቁ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡ ከተራኪዎቹ አንደኛው በቻይና ጦር ቁጥጥር ስር የሚገኘን የተራራ ላይ ምሽግ ሰለለው እንዲመጡ ይታዘዛሉ፡፡ የተራራውን ርቀት በማሰብ በዚህ መሀል ጠላት ቢያጋጥማቸው የተሰጣቸውን ሰላሳ ስምንት ያህል ወታደሮች በቂ እንዳልሆኑ ያስባሉ፡፡ ትእዛዝ ነውና ትራታቸውን በውስጣቸው ይዘው ይሄዳሉ፡፡ ተራራውን እንደተጠጉም የተኩስ ናዳ ቀለቀል ያከፈትባቸዋል፡፡ ከሁለቱም ወገን ተኩስ ይፋፋምና በስተመጨረሻ የተራኪዬ ጦር ተራራውን ይቆጣጠራል፡፡ ተራኪዬ ይህንን ለበላዮቻቸው ቢያሳውቁ የሚያምናቸው ይጠፋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ ለስለላ ብቻ የተላኩ ጥቂት ወታደሮች ተራራውን መማረካቸው በአለቆቻቸው ዘንድ አግራሞት መፍጠሩ ነው፡፡ ተራኪው ጦራቸውን ይዘው ይቀመጣሉ፡፡ የተራራውን ምሽግ ማታ ሰስት ሰአት ላይ የነበሩበትን ምሽግ የቻይና ጦር በመድፍ ይቀናረዋል፡፡ እስከ ለሊቱ አስር ሰአት ከፍተኛ ውጊያ ይካሄዳል፡፡ ሲነጋ የቻይና ጦር ያፈገፍጋል፡፡ ተራኪዬ የተቆጣጠሩትን ምሽግም ለአሜሪካውያን አስረክበው ለእረፍት ወደ ካምፕ ይመለሳሉ፡፡ ለሊቱን የቻይና ጦር ምሽጉን ከአሜሪካ ጦር ይነጥቃል፡፡

ይህ ናሙና ግለተረክ የተራኪዬን የኮሪያ ዘመቻ እንድ ስኬታማ ተግባር የሚያሳይ ነው፡፡ የስኬታማነቱ ምንጭ አቀንቃኝ ገጸተረኮች ከሚጠበቅባቸው የበለጠ ተግባር በመፈጸማቸው ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይኸውም የጠላትን እስፋፊር ለማጥናት ተልከው ሳለ



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

የጠላትን ምሽግ ለመግረክ በቅተዋል። በዚህም ወታደሮቹ የማይታመን ተግባር ፈጽመዋል። ይህን የሚያሳየው ደግሞ ተራኪዬ ይህ ተግባር መፈጸሙን ለአዛዦቻቸው ለማስረዳት ከቃላት ያለፈ ተጨባጭ ማስረጃ ለማቅረብ መገደዳቸው ሲሆን ይኸውም «የሽጉጥ መብራት አለኝ እሱን ተኩሼ፣ እውነትም እዛ ላይ መሆኔን [እለቶቼ] ያረጋገጡት» በማለት የገለጹት ነው።

የዚህን ግለተረክ ስኬታማ ጭብጥ የሚያጠናክሩ ሁለት ተጨማሪ ገጽታዎች አሉ። አንደኛው የተራኪው «የኢትዮጵያ ጦር የመጀመሪያ ስም ያገኘበት ቀን እሱ ነው» የሚለው ገለጻ ነው። ከዚህ አባባል ሁለት ነገሮችን መረዳት እንችላለን። አንደኛው የኢትዮጵያ ጦር ከአዲስ አበባ ተነስቶ ወደ ኮሪያ ግንባር እስከ ተንቀሳቀሰበት ጊዜ ድረስ «ስም የለሽ» የነበረ መሆኑን ነው። በሌላ አገላለጽ የኢትዮጵያ ጦር እውቅና የሚያሰጠው ተግባር አልፈጸመም ነበር። ሁለተኛው ገጽታ ደግሞ ኢትዮጵያውያኑ በከፍተኛ መስዋዕትነት ከቻይና ነጥቀው ለአሜሪካ ያስረከቡትን ተራራ ቻይና መልሶ ከአሜሪካውያን እጅ ማስለቀቅ መቻሉን መሰረት ያደረገ ነው። ይህ አጋጣሚ ኢትዮጵያውያኑ በውጊያ ብቃት ከአሜሪካውያን የተሻሉ ነበሩ ለማለት የሚያስደፍር ሲሆን ይኸውም ከአሜሪካውያኑ እጅ ቻያናውያን የነጠቁትን ቦታ ኢትዮጵያውያኑ ወታደሮች ለሁለተኛ ጊዜ ማስመለሳቸው ነው። «እኛ ደግሞ መልሰን ከቻይናዎቹ ነጠቅን» የሚለው አባባል ነው (ኮሎኔል ገብረ ኢያሱስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር ሁለት፣ ስክሪብ ገጽ 9-11፣ ነሐሴ 10 1999 ዓ.ም)። በአጠቃላይ ናሙና ግለተረኩ ኢትዮጵያውያኑ ወታደሮች ጠላትን የመሰለል ግዳጅ ማሳካታቸውን፣ በኮሪያ ጦርነት ተሳትፏቸው ስማቸው ለመጀመሪያ ግዜ የተነሳበትን አጋጣሚና ከአሜሪካውያን ወታደሮች በተሻለ የጠላትን ጦር መጋፈጥ መቻላቸውን የሚያሳይ ነው።

እስካሁን ድረስ ከኮሪያ ዘማቾች የተሰበሰቡትንና የስኬት ጭብጥ ያላቸውን ግለተረኮች አይተናል። የግለተረኮቹ ሁነት ምርኮኛ በማምጣትና የጠላትን አሰላለፍ በመሰለል ላይ ያተኮሩ ናቸው። ቀጥሎ ደግሞ ኢትዮጵያውያን ወታደሮችን ከሌሎች ሃገራት ወታደሮች የሚለያቸውን በጠላት ያለመማረክ ሁነት የሚገልጹ ግለተረኮችን እንመለከታለን።

#### 4.2.2.2 የአለመማረክ ስኬት

ከኮሪያ ዘማች ኢትዮጵያውያን ግለተረኮችና ከህትመት ውጤቶች መረዳት እንደሚቻለው የዘመቻቸው ስኬታማነት መገለጫ የጠላት ወታደርን ከመማረክ፣ የጠላትን እንቅስቃሴ ከመሰለል ወይም የጠላትን ምሽግ ከመንጠቅ አጥጋቢ አፈጻጸም የሰፋ ነው (ቃኘው፣1994፣19)። ዘማቾቹን በኮሪያ ጦርነት ከተሳተፉ የሌላ ሀገር ወታደሮች የሚለያቸው ዓቢይ ገጽታ ምርኮን የተመለከተ ነው (ዳምጤ፣1950፣309)። በኮሪያ ጦርነት ወቅት በውጊያ ላይ ከተሳተፉ የተለያዩ ሀገራት ወታደሮች ውስጥ በጠላት እጅ ያልወደቁ ወይም ጠፍተው ያልቀሩ ኢትዮጵያዊያን ብቻ ናቸው (ቃኘው፣1993፣41)። ይህ ተግባር ኢትዮጵያውያኑን ዘማቾች ከሌላው ሀገር ዘማቾች ልዩ ያደርጋቸዋል።

ይህም ሆኖ ኢትዮጵያውያኑ ይህንን ስኬት በቀላሉ እንዳላገኙት ግለተረኮቻቸው ያስረዳሉ። የጠላት ጦር እንሱን የመማረክ አላማ ስላልነበረው ወይንም በጠላት እጅ ሳይወድቁ ቀርተው አይደለም። ይልቁንም እጅን በጸጋ መስጠት በአሻፈረኝ ግብግብ መካከል ህይወትን ከማጣት ጋር ተወዳድሮ ለኢትዮጵያውያኑ የኋለኛው፡ ለሌሎች ግን የመጀመሪያው ሚዛን ስለሚደፋባቸው መሆኑን አንድ ተራኪ እንዲህ ገልጸውታል።

> የእኛ ወታደር መማረክ አይፈልግም። ኸ አሜሪካኖች ለማምለጥ ካልቻሉ «ኋይ ሹድ አይ ዳይ?» [ለምን እሞታለሁ?] ነው የሚሉት። ስለመኪናቸው፣ ስለቤታቸው፣ ስለሚስታቸው፣ ስለልጆቹ፣ ስለ ምኑ ያስባሉ። ሀገሩ ምቾቱን ሁሉ ያስባል። «ኋይ ሹድ አይ ዳይ? አሁን፣ አሁን ብማረክ አንድ ቀን እመለሳለሁ።» ይላል። /ላቅ/ እዚያ ኮሚኒስት ሀገር ሄደው ግን በተቅማጥ ብዙዎቹ አልቀዋል። እና፣ የእኛ ሰዎች መማረክ አንፈልግም። ከመማረክ መሞትን ነው የምንመርጠው። ምክንያቱም እዚያ ኸ ቶርቸሪንግ [ማሰቃየት] የሚባል አለ፤ ኮሚኒስቱ ጋር። ኮሚኒስቶች ጋር የባንቡ፣ ሹል ባንቡዎች አሉ ቶርቸሮቻቸው። እንትን፣ በጣት፣ ማነው? ይሄ ጥፍር፣ ጥፍርና ጣት መሃከል እየወጉ ያሰቃዩሃል። ጥፍርህን ይነቅሉታል። እንደዚህ እየተባለ ስለሚወራ ኸ ደግሞ ማንኛውም ሰው መማረክ አይፈልግም። ሌሎቹ ግን ግድ የላቸውም። የሚሞቱ ከሆነ እንዳይሞቱ መማረክ ይፈልጋሉ። እኛ ደግሞ ከምንማረክ ብንሞት ይሻላል ብለን ነው እንትን ምንለው። እና፣ በዚህ ሁኔታ የእኛ ወታደር እንኳን በሕይወት ሆኖ ሬሳውም አልተማረከም። አንድ ሰው እንኳን (ኮሎኔል አለማየሁ ካሳ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 22-23፣ ነሐሴ 21፣ 1999 ዓ.ም)።

ኢትዮጵያውያኑ የኮሪያ ዘማቾች ከመማረክ መሞትን የሚመርጡ ብቻ ሳይሆኑ መማረካቸው የአገር ስም የሚያጠፋ ነው የሚል እምነት እንዳላቸው ግለተረኮቻቸው ያስረዳሉ። ኢትዮጵያውያኑ በአካል እያሉ ላለመማረክ ቁርጠኛ አቋም የነበራቸው ሲሆን ይህም መማረክ ያለውን ሀገራዊ እንድምታ ታሳቢ በማድረግ ነው። ለእነሱ መማረክ ያለው ፍቺ በጠላት እጅ መውደቅ ብቻ ሳይሆን የወከሉት ሀገር ሽንፈት እንደሆነ ቀጣዩ ናሙና ግለተረክ ያስረዳል።

> አንዱን ማረኩት። ኋላ «ወሰዱኝ! ወሰዱኝ! የአገርህ ስም ጠፋ! የአገርህ ስም ጠፋ! አለ። ተሰማ የሚባል ፈረሰኛ ነበር ዘሎ ሄደና በሳንጃ ጀርባው ላይ ሰካበት፣ ቻይናው ላይ። በሳንጃ ሲወጋው ያ ሲወድቅ ቢስበው አልወጣ አለ፡ ሳንጃው። ጥሎት ከነጠመንጃው ምርኮኛውን ይዞ ተመለሰ (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 29፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)።

ይህ ናሙና ግለተረክ ኢትዮጵያውያን ወታደሮች ከራሳቸው በጠላት እጅ መውደቅ ይልቅ የወከሏት ሀገራቸው ስም መጥፋት እንደሚጨንቃቸው የሚያሳይ ነው።



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

የአለመግረክ ጭብጥ ከኮሪያ ዘማቾች በተሰበሰቡ ግለተረኮች ውስጥ ጉልህ ስለሆነ ተጨማሪ ማሳያ የሚሆንን አንድ ሪሳ ላለማስማረክ በነበራቸው ቁርጠኛ አቋም የከፈሉትን መስዋዕትነት የሚያሳይ ግለተረክ ነው።

> አንድ ወታደር ተመቶ ሬሳው፣ አሞቲ ይባላል፤ አስተውሳለው ስሙን ጥሩ አርጌ፣ ገደል ቢገባ እሱን ለማውጣት ጥለን አንሄድም ብለው እምቢ አሉ ወታደሮች። እሱን ለማውጣት ገደል ሲገቡ አንደኛው ገደል ገብቶ ተሰ ተሰበረ። እሱን ጎትተን እንደገና ደግሞ ዳመና እስኪሆን ድረስ፡ ጥላ እስኪያጠላ፡ ጥላ ሲሆን ከሩቁ አይታይም፣ ጎትተን አወጣናቸው። የኛ ወታደሮች ሬሳ እንኳን ሬሳ ጥለው ሲሄዱ እ ቁስለኛ ጥለው ሲሄዱ ይቅርና ሬሣ እንኳን ጥለው አይሄዱም ወታደሮች (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ፤ ቃለ መጠይቅ፤ ካሴት ቁጥር 2፤ ስርክብ ገጽ 21፤ ነሐሴ 10፤ 1999 ዓ.ም)።

ተራኪዎቹ የኮሪያን ዘመቻቸውን ስኬታማነት መቼታቸው እዛው ግንባር ላይ የሆኑ ግለተረኮች ማሳያነት ስናዳብር ቆይተናል። ይህ የስኬታማነት ጭብጥ ቀጥሎ በቀረበውና መቼቱ ከኮሪያ ጦርንት ውጪ በሆነ ግለተረክ ይበልጥ የሚዳብር ነው።

> የኮሪያ ታሪክ የኮሪያ ጦርንት የቃኘው ሻለቃ አለምን ያስተዋወቃት ቃኘው ሻለቃ ነው እውነት ልንገርህ በዚህ አጋጣሚ ልናገረው ምፈልገው ለትምህርት አሜሪካን ሃገር በሄድኩበት ጊዜ ኒወርክ አንድ ሆቴል አርፌ አንድ የህግ ተማሪ ያውም ጠበቃ የሆነ ባለዲግሪ «ከየት የመጣቹ ናቹ?» ብሎ ሲጠይቀን «ከኢትዮጵያ» ብንለው «የት ነው ኢትዮጵያ?» አለን። ከዚያ በኋላ ኢትዮጵያ እንደዚ እንደዚ ስለው «የቃኘው አገር ነው?» አለኝ። አየው እይ ሌላ ሳያውቅ ኢትዮጵያን ሳያውቅ ቃኘውን ያውቃል። አለም ያውቃታል። ቃኘው ሻለቃ ኢትዮጵያን ያሳወቀ ቃኘው ሻለቃ ነው (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ፤ ቃለ መጠይቅ፤ ካሴት ቁጥር 2፤ ስክርብ ገጽ 24፤ ነሐሴ 10፤ 1999 ዓ.ም)።

ይህ ግለተረክ ተራኪዬ የተሳተፉበት የኮሪያ ዘመቻ ኢትዮጵያን ለአለም ህዝብ የማሳወቅ ግብ እንደተሟላ የሚያሳይ ነው። በሌላ አንጻርም በግለተረኮች ሲገለጽ የነበረው የስኬት ጭብጥ የአሜሪካዊ አዛዦቻቸውን አቀንቃኝ በአደረገ ተረክ ዳብሮ ይገኛል።

> የክፍለ ጦሩ አዛዥ የነበረ አንድ አሜሪካዊ ሲሰናበተን በመሐል ወደ አገሩ ይመለስ ነበር። ኧኧኧ «እኔ ወደ ሀገሬ ከመመለሴ በፊት እናንተን የወለደች እናት ኢትዮጵያ ሄጄ ሻለቃው አዛዥ «ሁላችሁም መጠየቅ አልችልም። ሻለቃው አዛዥ ጋር ሄጄ እራት እበላለው፣ ከዚያ ኋላ ወደ ሀገሬ እሄዳለው» ብሎ የተናገረውና ከዚያ መጥቶ እዚህ፤ ጄኔራል ወልደ ዮሃንስ ሽታ፤ የሰተኛ ቃኘው አዛዥ የነበሩ ቤተሰብ ጋር ገብቶ እራት በልቶ፤ ክብር ዘበኛም ተቀብሎት፤ ይህን ያደረገ ነው (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ፤ ቃለ መጠይቅ፤ ካሴት ቁጥር 2፤ ስክርብ ገጽ 21፤ ነሐሴ 10፤ 1999 ዓ.ም)።

በዚህ ንኡስ ክፍል ከምርኮ ጋር በተያያዘ የኮሪያ ዘመቻን ስኬታማነት የሚያሳዩ ጭብጦች ያሏቸውን ግለተረኮች የተመለከትን ሲሆን ቀጥለን ደግሞ የጠላትን ጦር በፊጠራ ወሬ ያሸበሩበትን አጋጣሚ እንመለከታለን::

## 4.2.2.3 የበላዒሰብ ፕሮፓጋንዳ ስኬታማነት

ከኮሪያ ዘማቾች ካገኘኋቸው ተረኮች ውስጥ በላዒሰብነታቸውን የተመረኮዙ በርካታ ግለተረኮች ያሉ ሲሆን እነዚህም ቢሆኑ የስኬት ጭብጥ ያዘሉ ናቸው:: የኮሪያ ዘማቾችን የተመለከተ ጥናት እየሰራሁ መሆኔን ያወቁ አንዳንድ ሰዎች አማካሪዬን ጨምሮ የዘማቾቹን በላዒሰብነት የተመለከቱ ተረኮች ተርከውልኛል:: (ሰብስብ ቁጥር 15 ተመልከት) እነዚህ ተረኮቻቸው በኮሪያ ጦርነት ወቅት ኢትዮጵያውያን ወታደሮች የሰው ስጋ የሚበሉ ናቸው የሚል እምነት በጠላቶቻቸው ዘንድ እንዲያድርባቸው ማድረጋቸውን የሚያሳዩ ናቸው:: የዘማቾቹን በላዒሰብነት የተመለከቱ ሞክሼ ግለተረኮች ስላገኘሁና የተረኮቹ ጭብጥ ሲቀርብ ከነበረው ትንተና ጋር ግንኙነት ስላለው ቀጥዬ ጥቂት ነጥቦችን አቀርባለሁ::

በትድማጊያ ሁሉም ተራኪዎቹ የዚህን ተረክ ኪትመጣ (origin) አስመልክቶ የተለያየ ገለጻ ሰጥተዋል:: ከአንደኛው ተራኪ በስተቀር የተረኩ ሁነት ኢትዮጵያውያኑ ወታደሮች ፈጠራ ውጤት በመሆኑ ላይ ይስማማሉ:: የአራቱም ገለጻ የየራሱ መጠነኛ ልዩነት ቢኖረውም አጠቃላይ መንፈሱ ግን ኢትዮጵያውያን ወታደሮች የጠላት ጦር በሚያያቸው ርቀት ላይ ሆነው ከተማረከ እስረኛ ገላ ላይ ልክ የእስረኛውን ስጋ የሚቆርጡ በሚመስል አኳኋን ዳቦ በኮንጻ እየቆረጡ ሲበሉ በመታየታቸው በጠላት ጦር ዘንድ የሰው ስጋ ይበላሉ የሚል ግንዛቤ እንዲፈጠር ማድረጋቸውን የሚገልጽ ነው:: የሁነቱን አፈጣጠር አስመልክቶ ከቀረቡት ትረካዎች ውስጥ አንዱ ቀጥሎ ቀርቧል::

> ኧ የእኛ ወታደር ጨበጣ ሲገባ ይሸልላል፣ ይፎክራል:: «በለው! በለው!» ይላል:: እና ኮሚኒስቶች ይሄ በጣም ይገርማቸው ነበር:: አሜሪካኖች ድምጻቸው አይሰማም:: የእኛ ወታደር ጨበጣ ውጊያ ሲገባ ይፎክራል፣ ይሞግላል:: «እገሌ በርታ» ምናምን ይላል:: በኋላ አንድ ቦታ ላይ ኧ አንድ ትልቅ ተራራ አለ:: ኮሚኒስቶች እዚያ ማዶ ናቸው:: ኧ ምን ያደርጋል አንዱ፣ ኧ የሰው ስጋ የሚበላ አስመስሎ አንድ ቀይ ነገር እንደዚህ እየቆረጠ በሳንጃ ሲበላ፣ ሲጎርስ ያያሉ:: እዚያ በቃ ትልቅ ሽብር ሆነ:: እዚያ የተማረከ ጠላት ነው የሚነገረን:: ትልቅ ሽብር ሆነ:: «ጥቁሮች ሰው የሚበሉ መጡ::» ተባለ:: እና ይሄ አንድ አድቬንቸር ነው አንድ ትልቅ ፕሮፓጋንዳ ነው (ኮሎኔል አለማየሁ ካሳ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 15፣ ነሐሴ 21፣ 1999 ዓ.ም)::

በሌላ በኩል የተረኩ መንስኤ የጠላት ወታደሮች እንጂ ኢትዮጵያውያን ወታደሮች አለመሆናቸውን አንደኛው ተራኪ አስረድተዋል:: እንደሳቸው አገላለጽ ከአፍሪካ ሰው የሚበላ



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

መጣ የሚለው ቻይናዎች ለፕሮፓጋንዳ አላማ የፈጠሩት ነው ይላሉ:: (ስብስብ ቁጥር 7 ተመልከት) የበላኤሰብ ግለተረኩች በዚህ ትንታኔ ለመካተት ምክንያቱ የግለተረኮቹ ነው:: ይህ በኢትዮጵያውያን ወታደሮች የተፈጠረ መሆኑ በአብዛኛው የሚታመንበት የፈጠራ ወሬ ለስኬታማ የፕሮፓጋንዳ ፍጆታ የዋለ ነው (Dereje 1993:27):: ለዚህ ማሳያ የሚሆነው የጠላት ጦር ከኢትዮጵያውያን ጋር ለመዋጋት እስከመፍራት መድረሱን የሚገልጸው ቀጣዩ ግለተረክ ነው::

> በእውነቱ ቻይናዎቹ ይዘውታል ያን ፈረንሳይ ያለቀበት ተራራ:: አሁንም ደግሞ በስተቀኝ ክንፍ የነበረው የኛ ጦር እንዲያጠቃ ተደረገ:: እና እኔና ሁለተኛ መቶ ነን ያጠቃን ያን ጊዜ ደግሞ:: እ ገባን እና በውነቱ ብዙ ጉዳት አልደረሰብንም:: ለምን? ኮሪያኖች ፈሩ አሁን በውነቱ:: ከአፍሪካ ሰው የሚበላ ጦር አምጥተዋል የሚል ጄኔራል አማንን እ የውሻ ጅራት አስመስለው ስለው ስጋ እንደዚህ እየበላ አስመስለው ቻይናዎች ስላወጡ ይባንን ጀመረ:: አይዋጋንም:: ይፈራሉ፡ የተማረኩ እንደሆን እርዶ ይበላኛል እያለ:: ታዲያ ምን ልበልህ እዚህ ላይ ወታደራዊ ሳይኮሎጂካል ምን ይላል? የምታደርገው ፕሮፓጋንዳ ተመልሶ እንዳይጠጋህ ተጠንቀቅ ይላል:: መልሰ ወጋቸው፡ ለራሳቸው (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 12፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)::

ይህ ናሙና ግለተረክ የበላኤሰብ ፕሮፓጋንዳ ከተፈጠረበት አላማ በተቃራኒ እንደዋለ የሚያስረዳ ነው:: በአጠቃላይ በዚህ ንኡስ ክፍል የኢትዮጵያ ወታደሮች የሰው ስጋ ይበላሉ በሚል እምነት የጠላት ጦር ከነሱ ጋር መዋጋት እንደሚፈራ የሚያስረዱ ግለተረኮችን አይተናል:: በሚቀጥለው የትንታኔ ንኡስ ክፍል ደግሞ በኮሪያ ጦርነት መሳተፋቸው ለተረኪዎቹ ያበረከተውን ሙያዊ አስተዋጽኦ እንመለከታለን::

### 4.2.2.4 ሙያዊ ትሩፋት

በኮሪያ ጦርነት ተሳትፎ ለዘማቾቹና ለሀገራቸው ጭምር ፈርጀ ብዙ ትውፊቶች አሉት:: ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግስታትን ውሳኔ ተቀብላ ከደቡብ ኮሪያ ጐን መሠለፏ ያስገኘላትን ኢኮኖሚያዊና ዲፕሎማሲያዊ ጠቀሜታዎች በምዕራፍ ሁለት አይተናል:: ዘማቾቹ በግል ያገኙትን በተመለከተ ቀጥሎ የተወሰኑ ነጥቦች ይቀርባሉ፡

በኮሪያ ጦርነት ተሳትፏቸው ያገኙት የሚሉት ጥቅም ሙያዊ ሲሆን ለወታደራዊ ህይወታቸው ስኬታማነት አስተዋጽኦ ያበረከተ ይመስላል:: ለምሳሌ አንዱ ተራኪ «ኮሪያ ዘማች በመሆን በጣም ደስ የሚል ነው ባጠቃላይ:: እውነትም ጥሩ ልምድ አገኘሁ የወታደርነት... ለወታደርነት ኑሮዬ ለኖርኩበት ላሳለፍኩት እስከ ሙሉ ኮሎኔልነት እስከ የደረስኩበት ድረስ የነበረኝ ኮሪያ ያመጣችልኝ ልምድ ነው በዕውነቱ:: ከካዴት እስኩል ያላነሰ ልምድ አግኝቼበታለሁ...» በማለት በኮሪያ ዘመቻቸውን ሙያዊ ጠቀሜታ ገልጸዋል (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 2፣ ስክርብ ገጽ 26፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)::

በሌላ በኩል የኮሪያ ዘመቻ ተሞክሮ ላይ በቀጥታ ለመመርኮዙ ተጨባጭ መረጃ ባይኖርም ከአምስቱ ተራኪዎቹ ሶስቱ በ1953 ዓ.ም በተባበሩት መንግስታት ሰላም አስከባሪነት ወደ ኮንጎ የተላከው የጠቅል ብርጌድ አባላት ነበሩ:: በኮንጎ ቆይታቸውም እጅግ ስኬታማ ተግባራትን የፈጸሙ ሲሆን ለዚህም ከአስር አመት በፊት በኮሪያ ጦርነት የተጎናጸፉት ሙያዊ ብቃት የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዳበረከተ ማሰብ ስህተት አይሆንም:: ይህ የኮንጎ ዘመቻ ራሱ የኮሪያ ዘመቻ ስኬታማነት ውጤት ሊሆን ይችላል:: ይኸውም የኮሪያ ዘመቻቸውን በስኬት የተወጡት የኢትዮጵያ ወታደሮች ለኮንጎው ሰላም ማስከበር ተልዕኮ አሳጭቷቸው ሊሆን ይችላል:: እዚህ ጋ የኮንጎው ዘማች ጦር ስያሜ ትኩረት የሚስብ ነው:: የኮሪያው ዘማች ጦር ቃኘው ይባል እንደነበር በዚህ ጥናት መግቢያ ላይ አይተናል:: ስያሜው ከንጉሱ አባት የፈረስ ስም መወሰዱንና ለተለያዩ ነገሮች መሰጠቱንም ተመልክተናል:: እንደ ኮሪያው ሁሉ ለኮንጎው ዘማች ጦር የተሰጠው ስያሜም ቢሆን ከፈረስ ስም የተወሰደ ነው (ቃኘው፣1995፣10):: የተራኪዎቹን የኮንጎ ተሞክሮ በተመለከተ ስብስብ ላይ የሚገኙትን ስብስብ ቁጥር 10 እና 11 አንባቢው እንዲመለከት ተጋብዟል::

በአጠቃላይ ከኮሪያ ዘማቾች የተገኙ ግለተረኮችን በመተንተን ሂደት ሁለት ዓቢይ ጭብጦችን አይተናል:: የመጀመሪያው ከአዲስ አበባ ከተሸኙበት ቅጽበት ጀምሮ ኮሪያ ጦር ግንባር እስኪደርሱ ድረስ ባሳለፏቸው ሂደቶች ውስጥ ተደጋጋሚ ጋሬጣዎች ሲደነቀሩባቸው ታይቷል:: ሁለተኛው ተራኪዎቹ ኮሪያ ጦር ግንባር ከገቡበት ቅጽበት ጀምሮ የነበራቸውን ቆይታ ስኬታማ አድርገው እንደሚያዩት በግለተረኮቻቸው ጭብጥ አማካይነት ለማየት ተችሏል::

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

## 5. ማጠቃለያ

በዚህ ክፍል በኮሪያ ጦርነት በተሳተፉ የአንደኛ ቃኘው ሻለቃ አባላት ግለተረኮች ላይ የተካሄደውን ጥናት የተመለከቱ ማጠቃለያ ሃሳቦች ይቀርባሉ።

ኢትዮጵያ በነጮች የአፓርታይድ አገዛዝ ስር ከነበረችው ደቡብ አፍሪካ ውጭ በኮሪያ ጦርነት ላይ የተሳተፈች ብቸኛዋ አፍሪካዊት ሀገር ናት። የተሳትፎዋ ምክንያትም እንደተባበሩት መንግስታት አባልነቷ ድርጅቱ በሰሜን ኮሪያና በደቡብ ኮሪያ መንግስታት መካከል በተፈጠረው ጦርነት ደቡቧን ለመርዳት ያሳለፈውን ውሳኔ በማክበር ነው። ከኮሪያ ጦርነት በኋላም ቢሆን በበርካታ የድርጅቱ ሰላም የማስከበር ተልዕኮዎች ላይ ተሳትፋለች። ነገር ግን በአጠቃላይ የሀገሪቱ የመከላከያ ሰራዊትና በተለይም በሰላም ማስከበር ተልእኮዎች ላይ የተሳተፉ ወታደሮች አካዳሚያዊ ትኩረት የሳቡበት አጋጣሚ እጅግ አናሳ ነው። በኮሪያ ጦርነት ዘማቾች ላይ ያተኮረው ይህ ጥናት በዚህ ክፍተት መነሻነት የተሰራ ሲሆን ክፍተቱን በመጠቆምና በመሙላት ረገድ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዳበረከተ ይታመናል።

የጥናቱን መረጃ አሰባሰብ በተመለከተ የመረጃ አቀባዮቹ ከ77 እስከ 89 እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ የአንደኛ ቃኘው ሻለቃ ዘማቾች ናቸው። ዘማቾቹ የኮሪያ ጦርነት ትዝታዎቻቸውን ለመተረክ እጅግ ተባባሪ ሆነው ተገኝተዋል። ተባባሪነቱ በእድሜ መግፋትና የሚኮሩበትን ታሪክ ለተተኪው ትውልድ አቆይቶ ለማለፍ ካላቸው ከፍተኛ ፍላጎት የመነጨ ይመስላል። ይህም "drive to story" seems particularly strong when one is confronted with death, loss, and grief." [Gilbert 2002:224] ከሚለው የተረክ አጥኚ ምሁር እይታ ጋር የሚጣጣም ነው። በአጠቃላይ የዘማቾቹ ተባባሪነት የመስክ ስራዬን በእጅጉ አቅልሎታል።

ምእራፍ ሁለት የጥናቱ የመረጃ ምንጭ የሆኑት ግለሰቦች የተሳተፉበትን የኮሪያ ጦርነት ከአነሳሱ ጀምሮ እስከ ፍጻሜው ድረስ የሚያስተዋውቅ መረጃ ቀርቧል። ተከትሎም የወታደሮቹን ምልመላ፣ ልምምድ፣ ሽኝትና የኮሪያ ጦርነት መሳተፍ ከተባበሩት መንግስታትና ከሌሎች ሀገራት ጋር የጠበቀ ዲፕሎማሲያዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስር ለመፍጠር ምክንያት እንደሆነች ተገልጿል። የዘመቻውን ባህላዊ አሻራዎች በተመለከተም ለሙዚቃና ለድርሰት ውጤቶች መሰረት በመሆን ማገልገሉን የሚያሳዩ አጋጣሚዎች መኖራቸው ተጠቅሷል። በተቀማጭ ጥናቶች ቅኝት ስር ደግሞ ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸውን ጥናቶችና ጽሁፎች ለመዳሰስ ጥረት የተደረገ ሲሆን የግለተረክ ጥናት በአለም ተቀፍ ደረጃ ከተቋሞቹ ጀምሮ ከፍተኛ ትኩረት እየሳበ መምጣቱንና በሀገራችን ግን ምንም አይነት አካዳሚያዊ ትኩረት አለመሳቡን አይተናል። ይህም ሆኖ በተለያዩ የትግል መድረኮች የተሳተፉ ግለሰቦች የግል ተሞክሮ በመጽሃፍና በቃለ መጠይቅ የማቅረብ ጥረቶች መኖራቸው የተገለጸ ሲሆን ከኮሪያ ዘማቾች ጋር በተያያዘ የተጻፉ ጥቂት ታሪክ ነክ ጽሁፎችን ለማስተዋወቅ ተሞክሯል።

ምእራፍ ሶስት በግለተረክ ላይ ያተኮረ ትውራዊ ዳራ የቀረበበት ሲሆን በግለተረክ ድፍየና፣ መዋቅር፣ ጭብጥ፣ ተተራኪነትና ክልሰፋ ላይ ያተኮረ ነው። በቅድሚያ የግለተረክን ድፍየና በተመለከተ በበርካታ የዘውጉ አጥኚዎች ተቀባይነት ያለውን ቅደም ተከተላዊ ትስስርሽ ያላቸው በእውንታው አለም የተከሰቱ የግል ገጠመኝ ሁነቶች ዘገባ ነው የሚለው በጥናቱ ውስጥ ለግለተረክ የቀረበ ድፍየና መሆኑ ተገልጿል። ቀጥሎም በስነተረክ አጥኚዎች በአንድ ግለተረክ ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡትንና አጠቃሎ፣ እውቅያ፣ ሴራ፣ ልቀት፣ ምዘናና ኮዳ የሚባሉትን ስድስት ያህል የግለተረክ መዋቅሮች ለማስተዋወቅ ጥረት ተደርጓል። እነዚህ መዋቅሮች በጥናቱ የትንታኔ ክፍል በስፋት የሚያጋጥሙ በመሆናቸው ምንነታቸውን ለማስተዋወቅ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። በማስከተል በግለተረክ ላይ የሚካሄዱ ጥናቶች አንደኛው የትኩረት አቅጣጫ በተረኮቹ ውስጥ የሚገኙትን ጭብጦች አውጥቶ ማሳየት በመሆኑና በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ትንታኔ የሚተኮርበት በመሆኑ ጥቂት ነጥቦችን ለማንሳት ተሞክሯል። ይኸውም ጭብጥን በተመለከተ ግልጽና አማራጭ ድፍየናዎች አለመኖራቸውን በመጠቆም በጥናቱ ውስጥ ታሳቢ የሚደረገው ድፍየና ቀርቧል። ከአንድ ለበለጠም ሆነ ግለተረክ ውስጥ ጭብጥን ለማውጣት ብቸኛ ወይንም ተመራጭ ተብሎ የሚገለጽ ስልት አለመኖሩን መሰረት በማድረግ የግለተረኮችን ጭብጥ ለማውጣት የሚደረገው ጥረት አስቸጋሪ መሆኑ ተገልጿል።

በምእራፍ ሶስት የተነሳው ሌላው ጉዳይ ግለተረክን ለመከወን የሚጋብዙ የተረክ ርእስ ነጥቦችን በተመለከተ በርካታ የተረክ ምሁራን አስደናቂ፣ አስገራሚ ወይንም ያልተለመዱ ሁነቶች ግለተረክን የማስከወን የተሻለ ብቃት እንዳላቸው መግለጻቸውን ተመልክተናል። በዚህም መሰረት ከኡሪያ ዘማቾች የተሰበሰቡት አብዛኞቹ ግለተረኮች አግራሞትን የሚያጭሩ ሁነቶች የሚያነተቱ መሆናቸው በጥናቱ ውስጥ ለተለያየ አላማ በናሙናነት የቀረቡና በስብስብ ላይ በወጣት የቀረቡ ግለተኮችን በማንበብ መረዳት እንደሚቻል ተጠቁሟል። የግለተረኮቻቸው ርእስ ጉዳዮች በገጸተረኮችን ሞተና ህይወትን አደጋ ላይ በጣሉ ሁነቶች ዙሪያ የሚሽከረከሩ ናቸው። ይህንንም ሁኔታ የጥናቱን የትንታኔ ክፍልና ስብስብ ግለተረኮችን በማየት ማረጋገጥ ይቻላል። በዚህ ምእራፍ መጨረሻ ላይ ግለረክን ለመከልሰፍ የማያመቹ ሆነው ተገኝተዋል።

ምእራፍ አራት የጥናታዊ ጽሁፉ ትንታኔ የቀረበበት ሲሆን ይኸውም መዋቅራዊና ጭብጣዊ አቅጣጫዎች ላይ ያተኮረ ነው። በዚህም መሰረት በቅድሚያ የቀረበው በምእራፍ ሶስት ውስጥ ለማስተዋወቅ የተሞከሩትና በአንድ ግለተረክ ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡት መዋቅሮች ከኡሪያ ዘማቾች በተሰበሰቡ ግለተረኮች ውስጥ ምን አይነት ገጽታ እንዳላቸው በናሙና ግለተረኮች አማካይነት ለማሳየት ተሞክሯል። በዚህም ሂደት በናሙናነት የቀረቡት ግለተረኮች አብዛኞቹን መዋቅሮች ያሟሉ ሆነው ተገኝተዋል። እግረመንገድም ለመዋቅራዊ ትንታኔ ያገለገሉት ናሙና ግለተረኮች ርእስ ጉዳያቸው ሞትና የሞት አደጋ የተደነቀረባቸው ሁነቶች መሆናቸውን አንባቢው እንዳስተዋለ ይታመናል። ይህ ደግሞ ጥናታዊ



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ጽሁፉ መሰረት ያደረጋቸው ግለተረኮች ሞትና የሞት አደጋን የተመለከቱ ተተራኪ ሁነቶችን በስፋት ያቀፉ በመሆናቸው ለተረክ ክዋኔ ከፍተኛ ተገቢነት እንዳላቸው የሚያሳይ ነው፡፡

የትንታኔው ሁለተኛ ክፍል ከኮሪያ ዘማች ኢትዮጵያን የተገኙት ግለተረኮች ሁለት ዓቢይ ጭብጦች እንዳላቸው አሳይቷል፡፡ የመጀመሪያው ዓቢይ ጭብጥ የዘመቻው ጋሬጣማነት ወይም ፈታኝነት ሲሆን ይህም ዘማቾቹ በአዲስ አበባ ከተደረገላቸው ሽኝት ጀምሮ ግንባር እስኪገቡ ድረስ ያለፉባቸውን ሂደቶች መሰረት አድርገው በከወኗቸው ግለተረኮች ውስጥ ጎልቶ ታይቷል፡፡ ዘማቾቹ በሚያሸብር ህዝባዊ ሽኝት የኮሪያ ጉዟቸውን ጀመሩ፡፡ ጅቡቲ ወደብ ደርሰው የተመለከቱት በተንጣለለ ውቅያኖስ ላይ የቆመው መርከብ አግራሞትን አጫረባቸው፡፡ ጉዟቸውንም በሀንድ ውቅያኖስ ላይ ወደ ሩቅ ምስራቅ አደረጉ፡፡ በዚህ ሃያ አንድ ቀን በፈጀ የመርከብ ላይ ቆይታቸው ሁለት ፈታኝ ሁኔታዎችን ተጋፈጡ፡፡ የመጀመሪያው በመርከብ ላይ ቆይታቸው ሙሉ የተፈታተናቸው የተመገቡት ነገር ሆድ ውስጥ አለመርጋት ሲሆን ይህም ለመርከብ ጉዞ አዲስ ከመሆናቸው የመነጨ ነው፡፡

ሁለተኛው ደግሞ ወደ ኮሪያ ለመዝመት አብሯቸው ከሀገሩ የወጣ ባልደረባቸውን በመርከብ ላይ ሳሉ አጡት፡፡ ይበልጥ ስሜታቸውን ለጎዳው ግን በተባበሩት መንግስታት ጥላ ስር ለአንድ ዓላማ የተሰለፉት የመርከቡ አዛዦች የሟች ባልደረባቸውን ሬሳ ለባህር አሳ ለመስጠት የተዘጋጁበት አጋጣሚ ነው፡፡ ይህ እቅድ ዘማቾቹ በተቀላቀሉት ዓለም አቀፋዊ ጦር የካምፕ ላይ ሕግ ተፈጻሚነት ያለው ሲሆን ኢትዮጵያውያኑን ግን በእጅጉ ለመቆጣትና የመርከብ ላይ ዓመጽ ለመቀስቀስ አስገድዷቸዋል፡፡ በዚህ ጥረታቸውም የሕጉን ተፈጻሚነት በመከላከል የባልደረባቸው ሬሳ አፈር እንዲቀምስ አድርገዋል፡፡ ወታደሮቹ ኮሪያ ወደብ ደርሰው በሀገሩ መሬ አቀባበል የተደረገላቸው ሲሆን ከአቀባበሉ ቀደም ብሎ ግን የቃል ኪዳን ሀገር ወታደሮች ያካሄዱት የነበረ የወደብ ላይ ጦር ልምምድ ጦርነት የተከፈተባቸው ያክል አስደንግጧቸዋል፡፡

የኢትዮጵያውያኑን ወታደሮች የኮሪያ ዘመቻ ጋሬጣማነት በጭብጦቻቸው አማካይነት የሚያሳዩት ግለተረኮቻቸው የኮሪያን ምድር ከረገጡ በኋላ የተጓዙባቸውን ሂደቶች በሚተርኩት ውስጥም ቀጣይነት ነበራቸው፡፡ ዘመናዊና አዲስ የጦር መሳሪያዎችን ተረክበው በሚለማመዱበት ወቅት የጥቂት ወታደሮችን ህይወት በቀጠፈ አሳዛኝ ሁነት ውስጥ አልፈዋል፡፡ ይኸውም በልምምድ ላይ ከወገን ጦር በስህተት በተተኮሰ መድፍ ሁለት ወታደሮች ህይወታቸውን ሲያጡ ከሰላሳ በላይ ደግሞ የመቁሰል አደጋ አጋጥሟቸዋል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በልምምድ ላይ ሳሉ በተፈጠረ ስህተት ጠላት በሌለበት ሁኔታ ውጊያ እስከመክፈት ደርሰዋል፡፡ ይህንን በመጨረሻም ከልምምድ በኋላ ኢትዮጵያውያኑ ወደ ዓውደ ግንባር ይላካሉ፡፡ ይህንን የዘመቻቸውን ሂደት ተከትሎም የግለተረኮቻቸው ጭብጥ የዘመቻቸውን ጋሬጣማነት ከማሳየት ወደ ስኬታማነት ይለወጣል፡፡

ኢትዮጵያውያኑ ወታደሮች ግንባር ላይ ከሰፈሩ በኋላ ብቁነታቸው ስላጠራጠረ ሁነኛ ተልዕኮ አልተሰጣቸውም ነበር። ይህም ብቃታቸውን ለማሳየት እንዲቋምጡ ሳያደርጋቸው አልቀረም። ብዙም ሳይቆይ በኮሪያ ዘመቻ ታሪክ የመጀመሪያው ተልዕኮ ተሰጣቸው። የተቀላቀሉት የአሜሪካ ጦር በጠላት መረጃ እጥረት ተቸግሮ ኖሮ ኢትዮጵያውያኑ ምርኮ እንዲያቀርቡ ይታዘዛሉ። ይህንንም በብቃት ይፈጽማሉ። ቀጥሎ የጠላትን አሰላለፍ ሰልለው እንዲመጡ ተልዕኮ ይሰጣቸዋል። ይህንንም ከሚጠበቅባቸው በላይ ይፈጽማሉ። አሰላለፍን ለመስለል ተልከው ምሽግ ይማርኩና ለአሜሪካ ጦር ያስረክባሉ። ለዚህ ስኬታቸው የኒሻን ሽልማት ያገኛሉ።

ከእነዚህ ሁለት አጥጋቢ የተልዕኮ አፈጻጸሞች በኋላ ኢትዮጵያውያኑ ወታደሮች የተለያዩ የውጊያ ተልዕኮዎችን ተቀብለው በመወጣት ስማቸው በኮሪያ ዓውደ ግንባር ይናኛል። በተለይ በኮሪያ ዘመቻቸው ጠላት በመማረክ አሃዱ ብለው የጀመሩትን ተግባር ገፉበት። ለአሜሪካውያኑ አስቸጋሪ የነበረውን ምርኮ የማምጣት ተግባር አጣደፉት። የጠላት ጦርም በሁሉ ማረኪ እንጂ አይማረኬ የሆኑትን ኢትዮጵያውያን በእጁ ለማስገባት ቢጥር ያተተዋል። እየቆየ ሲሄድማ በሰኀስብ ናቸው ብሎ በማመን ይዋጋቸው ዘንድ ድፍረት ያጣል። በመጨረሻም ኢትዮጵያውያኑ ምርኮ የማምጣት፣ ግዳይ የመጣልና ምሽግ የመንጠቅ ውጤቶችን በጠላት ላይ ሲያስመዘግቡ ጠላት በበኩሉ ግዳይ ከመጣል ያለፈ ነገር መፈጸም ይሳነዋል። በጦርነት መሀል የጠፋ፣ በጠላት እጅ የወደቀ ወታደርም ሆነ ሬሳ አለመኖር በኮሪያ ጦርነት ከተሳተፉ የበርካታ ሃገራት ወታደሮች ውስጥ ልዩ ያደርጋቸዋል። በዚህም የተነሳ በኮሪያ ዘመቻቸውን ለወከሏት ሀገራቸው መልካም ስም፣ ለራሳቸውም ልምድ የቀሰሙበት አጋጣሚ አድርገው ያስቡታል።

ከኮሪያ ዘማቾች የተገኙት ግለተረኮች የዘመቻውን ጋሬጣማነት በማሳየት ይጀምሩና ...ን ስለገጽ» በአስከፊ ስኬታማ አጨራረስ መቋጨቱን ያውጃሉ። ዘማቾቹ «የአለምን ደህንነት» የመታደግ ዓላማ አንግበው የተሳተፉበት አለም አቀፋዊ ተልእኮ፣ በፈታኝ አነሳስ ተጀምሮ በስኬት መጠናቀቁን ስናስተውል ኢትዮጵያውያኑ የተጋዱለት ገብ /hero journey/ ያካኼዱ መስለው ይታያሉ። እነዚህን የግለተረኮቻቸው አቢይ ጭብጥ የሆኑትን በፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ አልፎ ለስኬት የመብቃት ሂደቶች በሁለት ስንኞች በቁጥቡ እንዲህ ተገልጸዋል።

> የጠቅል፡ አሽከር፡ የጦር፡ መምህሩ፡
> ሲሄድ፣ ኮሳ፣ ሲመለስ፣ ክሩ (ዳምጤ፣1950፣217)።

በመጨረሻም ይህ ከኮሪያ ዘማች ኢትዮጵያን በተሰበሰቡ ግለተረኮች ላይ የተመሰረተ ጥናት የግለተረክ ዘውግንና የኮሪያ ዘመቻን የተመለከቱ በርካታ በግንዛቤዎችን እንዳስጨበጠ ይታመናል።

## 6. ይሁንታ

በዚህ ክፍል በኮሪያ ጦርነት የተሳተፉትን የአንደኛ ቃኘው ሻለቃ አባላት ግለተረኮች ስብስቦ በማጥናት ሂደት የተስተዋሉና ለወደፊቱ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል የሚባሉ ነጥቦች ለተለያዩ አካላትና ለግለተረክ አጥኚዎችም አንዳንድ የአቅጣጫ ጥቆማዎች ይቀርባሉ፡፡

ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግስታት ጥላ ስር ሰላም የማስከበር ሚናዋን አሃዱ ብላ የጀመረችው በኮሪያ ስለነበር ለኮሪያ ዘማቾች ቅድሚያ ተሰጥቶ የአምስቱንም ቃኘው ሻለቃ አባላት ግለተረክ በምልዓተ መስነድ ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ፡፡ የኮሪያ ዘማቾችን ተከትሎም ወደ ኮንጎ፣ ቡሩንዲ፣ ላይቤሪያና ሱዳን ዳርፉር የዘመቱትን ወታደሮች ግለተክ ከዘማቾቹ አንደበት መሰብሰብ ተገቢ ነው፡፡ እነዚህ ዘመቻዎች የሃገሪቱን ወታደራዊ ኃይል ድንበር ተሻጋሪ ተልዕኮዎች የእስከ አሁን ሂደቶች በቅደም ተከተል ስለሚያሳዩ ከተለያዩ የሶሻል ሳይንስ ዘርፎች ፍላጎት አንጻር ተናጠላዊ ወይም ንጽጽራዊ /comparative/ ጥናቶች ሊካሄዱባቸው ይችላሉ፡፡

የሀገራችን ሰላም አስከባሪነት ተልዕኮ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ይገኛል፡፡ በቀዳሚዎቹ ተልእኮዎች ላይ የተሳተፉ ዘማቾች ተሞክሮ ለቀጣዮቹ ስኬት አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይችላል፡፡ ለምሳሌ የሚሄዱበትን ሀገርና አብረዋቸው የሚሰለፉትን የሌላ ሀገር ወታደሮች ባህል፣ ቋንቋ፣ መልከዓ ምድር ወዘተ አስቀድሞ ማወቅ ያለውን ጠቀሜታ ከበፊቶቹ ልምድ መማር ለቀጣዮቹ ተልእኮ ስኬታማነት እገዛ ይኖረዋል፡፡

በሌላ በኩል ግለተረክን መተረክ ስነልቦናዊ ጠቀሜታ የሚሰጥበት ሁኔታ አለ፡፡ በግጭቶች ላይ በተለይም ከሃገራቸው ውጪ በሚካሄዱ ዘመቻዎች ላይ የሚሳተፉ ወታደሮች አሉታዊ ገጠመኞቻቸውን እንዲተርኩ ማድረግ ካጋጠማቸው አደጋ ወይንም ጉዳት ፈጥኖ ለማገገም እንደሚያግዛቸው በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ግለተረኮች ላይ የተካሄዱ ጥናቶች አመልክተዋል፡፡ በተለይ በጦርነት ላይ የተሳተፉና ጉዳት የደረሰባቸው ወታደሮች ሳይዘገዩ ገጠመኞቻቸውን ቢተርኩ ይበልጥ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ተደርሶበታል፡፡ "Veterans who developed accounts of their experience felt they coped better, overall, if they began to tell their story early after the loss." (Gilbert 2002:224) ከዚህም በመነሳት ኢትዮጵያውያን ወታደሮችን ለሰላም ማስከበር ተልዕኮ የሚያሰማራው የመከላከያ ሚኒስቴር ይህንን የተረክ ስነልቦናዊ ፋይዳ ከግምት አስገብቶ የዘማቾቹን ግለተረክ ለመሰብሰብ ተገቢ ትኩረት መስጠት ይኖርበታል፡፡

በግለተረክ አቀባይነት ካገለገሉኝ ዘማች አረጋውያን ያስተዋልኩት ጉዳይ ከእድሜያቸው መግፋትና ፖለቲካዊ ንቃት አንጻር በሶስት የአገዛዝ ስርዓቶች ወይንም በግማሽ ክፍለ ዘመን ውስጥ በሃገሪቷ የታዩ ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦችን አስመልክቶ ከግል ተሞክሮ የመነጨ ሰፊ መረጃ ሊሰጡ እንደሚችሉ ነው፡፡ ስለዚህም ለአረጋዊያን አካዳሚያዊ ትኩረት ተሰጥቶ በግለሰባዊም ሆነ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸው ምልከታ በቃለ



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

መጠይቅ አማካይነት ተሰብስቦ ቢሰነድና ቢጠና መልካም ነው። በአጠቃላይ አረጋዊያንን ቃለ መጠይቅ ማድረግ ጠቃሚ መረጃዎችን ከመቅረስ ባሻገር የእነሱንም ስነልቦና ለማጠንከር የሚረዳ ነው።

በአጠቃላይ ከሃገራችን የቀድሞና የአሁኑ የመከላከያ ሰራዊት አባላት ቁጥር፣ ከሰራዊቱ ነባር ተቋምነትና ተልእኮ ብዛት አንጻር ፈርጀ ብዙ አካዳሚያዊ ጥናቶችን የሚጋብዙ ናቸው። የኢትዮጵያ ቋንቋና ስነጽሁፍ በተለይም የፎክሎር ክፍል ትምህርት ተማሪዎች የመከላከያ ሰራዊት አባላት ስነቃላዊ ሃብት አማላይ ሊባል የሚችል በመሆኑ ትኩረታቸው ወደ እነሱ ቢሳብ መልካም ነው። በግለተረክ ላይ የተመሰረተ ጥናት የሚያካሂዱ አጥኚዎችም ግለተረኮችን በቅድሚያ በመሰብሰብና በመቅረስ ቀጥሎም ከክልሰሳ፣ ከመዋቅር፣ ከጭብጥ፣ ከአተራረክ ስልት፣ ከቋንቋ አጠቃቀም፣ ከዘዌ፣ ከዘዌ አውድና ከታዳሚ አንጻር ጥናቶችን እንዲያካሂዱ ለመጠቆም እወዳለሁ።

## አባሪ አንድ

### 1. የተረክ አቀባዮች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ስም | እድሜ | ጾታ | አድራሻ | ስራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የአስር አለቃ አስፋ አስፋው | 89 | ወንድ | አዲስ አበባ | ጡረተኛ |
| 2 | የመቶ አለቃ ታደሰ ገ/ክርስቶስ | 80 | ወንድ | አዲስ አበባ | ጡረተኛ |
| 3 | ኮሎኔል ገ/ኢየሱስ ሚካኤል | 82 | ወንድ | አዲስ አበባ | ጡረተኛ |
| 4 | ብርጋዲየር ጀኔራል ደስታ ገመዳ | 79 | ወንድ | አዲስ አበባ | ጡረተኛ |
| 5 | ኮሎኔል አለማየሁ ካሳ | 77 | ወንድ | አዲስ አበባ | ጡረተኛ |
| 6 | የአምሳ አለቃ ተስፋዬ ሳህሉ | 85 | ወንድ | አዲስ አበባ | ጡረተኛ |

ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

## አባሪ ሁለት

## ለኮሪያ ዘማች ኢትዮጵያውያን ቃለ መጠይቅ የተዘጋጁ ጥያቄዎች

ሀ. ከጉዞ በፊት

1. ሙሉ ስምዎ ማን ይባላል?
2. መቼና የት እንደተወለዱ አስተዳደግዎን ጨምረው ቢገልጹልኝ?
3. ወደ ውትድርና ሙያ እንዴት ሊገቡ ቻሉ?
4. ወታደራዊ ትምህርቶችን በየትኛው የጦር ትምህርት ቤት ተከታተሉ?
5. ወደ ኮሪያ ከመዝመትዎ በፊት የነበሩበት የጦር ክፍልና የስራ ድርሻ ምን ነበር?
6. ለኮሪያ ዘማችነት እንዴት እንደተመለመሉ ቢነግሩኝ?
7. ወደ ኮሪያ ለመዝመት ከተመለመሉት ውስጥ አንዱ መሆንዎ የተገለጸልዎት ቀን የተሰማዎት ስሜት ምን ነበር?
8. ወደ ኮሪያ ከመሄድዎ በፊት ስለኮሪያ ጦርነት የነበርዎት አስተያየት ምን ነበር? በህዝቡ ዘንድስ ምን አይነት ወሬዎች ነበሩ?
9. ከእዛ በፊት ኮሪያ የሚባል ሀገር መኖሩን ያውቁ ነበር?
10. ወደ ኮሪያ ለመዝመት መመረጥዎን ቤተሰቦችዎ ሲያውቁ ምን ተሰማቸው?
11. ለኮሪያ ዘመቻ ያደረጋችኋቸው ቅድመ ዝግጅቶች ምን ዓይነት ነበሩ?
12. ወደ ኮሪያ የተሸኛችሁበትን ቀን እንዴት ያስታውሱታል? ሥነስርዓቱ ምን ይመስል ነበር? የመሸኛ ንግግር ነበር? የንግግሩ ይዘትስ ትዝ ይልዎታል?
13. «ቃኘው ሻለቃ» የሚለው ስያሜ ለምን ተሰጣችሁ? ትርጉሙስ ምንድነው?

ለ. በጉዞ ላይ

14. ከአዲስ አበባ እስከ ጅቡቲ ያደረጋችሁትን ጉዞ በተመለከተ ባቡር ሲሳፈሩ የመጀመሪያዎ ነበር?
15. ከአዲስ አበባ ጀምሮ ወደ ምስራቃዊው የሃገራችን አቅጣጫ ስትጓዙ መልክዓ ምድሩን፣ አየሩንና ህዝቡን በተመለከተ ምን አዲስ ነገር አስተዋሉ?
16. በባቡር በጉዞዎ ላይ ያስተዋሉትና ዛሬም ድረስ የማይረሳዎት አጋጣሚ ካለ ይጥቀሱልኝ?
17. ከሃገርዎ ሲወጡስ የመጀመሪያዎ ነበር? ምን ተሰማዎት?
18. ከጅቡቲ ወደብ ወደ ኮሪያ ለመሄድ መርከብ ስትሳፈሩ የነበረውን አጋጣሚ ያጫውቱኝ:: መርከቡ ውስጥ ሲገቡ ምን ተሰማዎት?
19. በመርከብ ላይ ለቀናት ያህል ስትቆዩ አዲስ የሆነብዎትና የገረምዎት ምንድነው?
20. የመኝታ፣ የምግብ ሁኔታና የመርከቡ ሰራተኞች አቀባበል ምን ይመስል ነበር?
21. መርከቡ ላይ እንደናንተው ወደ ኮሪያ ከሚዘምቱ ወታደሮች ጋር እንደተገናኛችሁ አንብቤአለሁኝ:: እስቲ ስለእነዚህ ወታደሮች በወቅቱ የተሰማችሁን ያጫውቱኝ::
22. ዛሬም ድረስ የማይረሳዎት የመርከብ ላይ አስቂኝ አጋጣሚ ያጫውቱኝ::

ሐ. አቀባበል፣ ትውውቅና ውህደት

23. ኮሪያ ስትደርሱ የተደረገላችሁ አቀባበል እንዴት ያለ ነበር?
24. ለመጀመሪያ ጊዜ የኮሪያውያን ሲቪሎችን ሲያዩ ምን ተሰማዎት?
25. የአየር ጠባዩና መልክዓ ምድሩን እንዴት አገኛችሁት?
26. ከአቀባበል በኋላ በነበረው ሂደት ይግለጹልኝ።
27. የአንደኛው ቃኘው ሻለቃ አባላትን አብረዋችሁ ከነበሩት ከአሜሪካውያን ወታደሮች የሚለያችሁ ምንድነው?
28. ምን አይነት የጦር መሳሪያዎችን እንድትታጠቁ ተሰጣችሁ? ከኢትዮጵያ ስትነሱ የታጠቃችኋቸውስ?

መ. ግንባር ላይ

29. ኮሪያ ሳሉ የነበሩበት ግንባር መጠሪያ፣ የሥራ ምድብዎ፣ ቦታው፣ ማዕረግዎና አዛዥዎን ይግለጹልኝ?
30. ግንባር ሳላችሁ የሚቀርብላችሁ ምግቦችና መጠጦችን በተመለከተ ምን ያስታውሳሉ?
31. እርስዎን ያልተስማማዎት መጠጥ ወይም ምግብ ነበር?
32. ከአሜሪካውያኑ ወታደሮች ጋር ቋንቋን በተመለከተ እንዴት ነበር የምትግባቡት?
33. ግንባር ላይ የተጋፈጣችሁት ጦር የየት ሃገር ሰራዊት ነበር?
34. ከጠላት ወታደር ጋር ፊት ለፊት የተጋፈጡበት አጋጣሚ ከነበረ ይግለጹልኝ?
35. የጦሩን አሰላለፍና የውጊያ ብቃት እንዴት ይገመግሙታል?
36. እርሶ የነበሩበት ክፍል በጦርነቱ ወቅት ፈጸመ የሚሉት ትልቅ ጀብዱ ወይም ተግባር ምንድነው?
37. እርስዎስ በግልዎ በጦርነቱ ላይ የፈጸሙት ልዩ ተግባር ነበር?
38. በኮሪያ ለፈጸሙት ተግባር ያገኙት ሽልማት ወይም ሜዳልያ ነበር?
39. የቆሰሉበት አጋጣሚስ ነበር?
40. በአቅራቢያችሁ የነበሩ የሌሎች ሀገራት ወታደሮችና ኮሪያውያን ስለእናንተ ምን ዓይነት አስተያየት ነበራቸው?
41. ኮሪያ ሳላችሁ ራሳችሁን እንዴት ነበር የምታዝናኑት?
42. በኮሪያ ቆይታ ወቅት የቡና ቤት፣ የመሸታና የፍቅር ጉዳይ እንዴት ነበር?

ሠ. ከኮሪያ መልስ

43. ከኮሪያ የተሸኛችሁበትን አጋጣሚ እንዴት ያስታውሱታል?
    - ሽልማቶች፣ የመሸኛ ንግግሮች ወዘተ
44. ከኮሪያ ወደ ሃገር ቤት በምን ተመለሳችሁ?
    - የመርከብ ጉዟችሁ መጀመሪያ ስትሄዱ ከነበረው በምን ይለያል?
    - ሃገር ቤት መቼ ደረሳችሁ?

- የተደረገላችሁስ አቀባበል እንዴት ነበር?

45. ለበርካታ ግዜ ደጋግሜ አውርቼዎለሁ የሚሉት የኮሪያ ገጠመኝዎ የትኛው ነው?
46. ከኮሪያ ምን ይዘው መጡ? (ማስታወሻዎች፣ ቁሳቁሶችና ፎቶ ግራፎች)

ረ. ቀጣይ ሕይወት

47. የኮሪያ ዘማች በመሆንዎ ከዚህ ቀደም ያገኟቸውና ዛሬም ድረስ የሚያገኟቸው ጥቅማ ጥቅሞች አሉ?
48. ከእናንተ የኮሪያ ዘመቻ በኋላ የኢትዮጵያ ወታደሮች በሠላም አስከባሪነት ወደ ኮንጎ፣ ርዋንዳ፣ ብሩንዲና ላይቤሪያ ዘምተዋል። ስለዚህ ጉዳይ ምን ይላሉ።
49. የኮሪያ ዘመቻችሁን በተመለከተ የአሁኑም ሆነ መጪው ትውልድ ማወቅ ይኖርበታል የሚሉት ጉዳይ አለ?
50. ሳልጠይቆት የቀረሁት ነገር ግን መግለጽ የሚፈልጉት ጉዳይ ካለ ዕድሉን ልስጥዎት?
51. በዚህ በማካሂደው ጥናት ላይ ምን አስተያየት አለዎት?

አመሰግናለሁ፣ እግዚአብሔር እድሜና ጤናውን ያብዛልዎት!

## አባሪ ሶስት

## የግለተረኮች ስብስብ

1. ሸንቁጥ መቼ የኢትዮጵያ ህዝብ ያስኬዳል? እኔ አሁን በሰቃ ነው የተሳፈርኩት፣ በሰቃ ነው እንደኛ ሻምበል ብቻ ነው እዚህ የተሳፈረው:: ግማሹ በሰቃ ነው፣ ግማሹ እዚህ ነው የተሳፈረው:: ህዝቡ አላሳፍር አለ:: በመንገድ ላይ ሰላ ነው:: ድሬደዋ እስከምንገባ ድረስ ህዝብ እንደዚሁ ነው፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ከተማው ጠትሳላ:: ይሄ ጋሪ የሚባል ሁሉ መንገዱን ዘጋ:: በቃ እሪታ ነው፤ ጩኸት ነው (አስር አለቃ አሰፋ አስፋው፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 3-4፣ ሐምሌ 30፣ 1999 ዓ.ም)::

2. በጦር እንትን ነው የተሸኘነው:: ብዙ ሰዎች ይላቀሳሉ:: አሁን ለምሣሌ ትዝ የሚለኝ እህቴ ነበረች:: ታናሽ እህቴ ነች:: እሷ ቄስ ትምህርት ቤት ነው የምትማረው:: ይቺ አሁን ከነአባቴ ጋር አብረው ይማሩ ነበር:: ነርስ እስኩል እና ያን ጊዜ እኔ እዚያ ውስጥ እነሱ ጋ ውጪም ቅርብ ስለነበርኩ እና እሷ እህቴ ልትሸኘኝ መጥታ እዛ መጥታ ታለቅሳለች:: ያገሩ አንድ ሌላ እኔን የሚያውቁ ቤተሰቦች ነበሩ:: እነሱም ያለቅሳሉ:: «ማን ነው ለምንድነው የምታለቅሺ?» ብለው ይጠይቋታል:: ለደስታ ደስታ እኮ መሄዱ ነው:: እህ እኔም የማለቅሰው እኮ ለሱ ነው እነሱ ግን በእንትንነት አይተዋወቁም:: እስከዚህ ድረስ ነው መስዋት የቻልነው:: እንደዚህ ያለ ነገር ነበር ለማለት ነው (ብርጋዴየር ጀኔራል ደስታ ነመራ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 4፣ ነሐሴ 23፣ 1999 ዓ.ም)::

3. እና ከዚህ ተነስተን ጫኑ የቆመው ናዝሬት ነው:: ያው ለቅሶ ነው:: ምን ልበልህ መተቀርነው [መረጃ አቀባዩ ከአዲስ አበባ እስከ ጅቡቲ የተዘረጋበት በባቡር የሚጎተት ተሳፍረን ነው] የሚወረወረው ምግብ [እሳላቸው]፣ የሚወረወረው ጠላ፣ ጠጅ ሳይቀር:: ህዝቡ እያለቀሰ ነው የሸኘን:: ጠቅላላ ማለት ይቻላል:: ከዛ ተነስተን ከናዝሬት ተነስተን አዋሽ ቀምን እንደገና:: ከአዋሽ ድሬደዋ ነው የቆምነው:: እና እንግዲህ ህዝቡ እያለቀሰ ነው:: ለቅሶ ነው በሚደንበት:: ሽበር ነበረ (ሎሌኔል ገብረ ኢየሱስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 4፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)::

4. ከደረስበኝ እኔ አስቂኝ የምለው፣ አንድ በጣም የምወዳት ሾርባ ነበረች:: ጧት ጧት እሷን ነው ማገኘው በምግብ ሰዓት በምሳ ሰዓት ያቺን ሾርባ እወዳታለሁ:: ኋላ አንድ ቀን፣ አንድ ጎደኛዬ ከጎኔ ቁጭ ብሏል:: ጆሮዬ ሲነበብ «ምንድናት ይቺ ነገር እባክህ ትጣፍጣለች?» አልኩት:: «ትንበርስ እኮ ነው!» አለኝ [ሳቁ]:: «የባህር ትንበርስ ነው» አለ:: ደነገጥኩ:: ሊያስቀውከኝም ፈለገ:: እና አንድ ይሄ ነው

(ኮሎኔል ገበረ ኢየሱስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 4፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)።

5. አንድ ጊዜ ፑሳን እንደገባን ኧ ትልልቅ ድንኳን አለ። ኮርት ሴንተር የሚባል የዛ ዓይነት ትርም ኮርሻቶ [የጨዋታ ዓይነት] ሲጫወቱበት የነበረው የእሱ ዓይነት ትላልቅ ድንኳኖች አሉ። ለየሻምበሉ አንዳንድ ትልልቅ ድንኳን ተሰጥቷል። እዚያ ድንኳን ውስጥ ኧ ሚንስ ነው - ምግብ ቤት ነው። እዚያም ቤት ውስጥ አንድ የአንድ ካምፓኒ ሚንስ [ለአንድ ሻንበል የተዘጋጀ መመገቢያ ቦታ]። እንትን አለ፣ ቪኒገር ቆምጣጤ። ምግባቸው ላይ ከፈለጉ ብዙ ዓይነት ምግብ ይቀርባል። ከቸኮላት ጀምሮ ደንበኛ ምግብ ሁሉ ይቀርባል። ቸኮላት አለ፣ ሲጃራ አለ፣ ኧ ቺዊንግ ገም አለ፣ ኮልጌት አለ፣ ምንም የሌለ ምግብ የለም። እዚያ ኧ አንድ በራሽን ነው የሚሰጡን። እና እዚያ ገበታ ላይ ቆምጣጤዎች አልፎ አልፎ ተቀምጠዋል። መልካቸው ዊስኪ ነው የሚመስለው። የፈለገ ሰው ምግቡ ላይ እየጨመረ ከጎመን ከሰላጣ ጋር እንዲበላ ነበር። በኋላ ተረኛ የነበረው አንድ በመጨረሻ ላይ ሻለቃ ሆኖ የሞተው ምን ይላል ሲያይ፣ ያ ቆምጣጤ በነጭ ጠርሙስ በየገበታው ላይ አለ። «ጎበዝ እንዳትሰክሩ ብቻ ይኼ ይኼ ደንበኛ የአሜሪካን ዊስኪ ነው። እ እንዳትሰክሩ እንጂ መጠጣት ትችላላችሁ።» ይላል። «እሺ» ይሉና ወታደሮች ስለዊስኪ ምንም አያውቁም ይጠጣሉ። እሱም ይቀምስና «አይ ትንሽ ይጎመዝዛል እንጂ ጥሩ ዊስኪ ነው።» ይላል። እና ወታደሩን ይጋብዛል። ወታደሩ ያንን ቆምጣጤ ጠጥቶ ጠጥቶ አሳላፊዎቹ ወጥ ቤቱ ምን ምን አሜሪካኖች ናቸው የተመደቡልን፣ ሲያዩ ጠርሙሱ ባዶ ነው። «ኡይ ቦይ ዊር ዛት ዊር ዲድ ዩ ፑት ኢት?» በቃ ምንድነው ይጠይቃሉ። ጥቁሮች ናቸው። በቃ ትልልቅ ናቸው። መጨረሻ ላይ እራት በልተው ይወጣሉ። ያ ሻምበል እራቱን በልቶ ይወጣል፣ ትንሽ እንደቆየ እንግዲህ ሽንት ቤት አለ - ሽንት ቤቱ ደግሞ ጎን ለጎን ነው። ይኼ መደባበቅ የለም። አንተ ፊክሽን ታነባለህ፣ አንዱ ኖቭል ያነባል፣ አንዱ ምናምን ያነባል፣ ቁጭ ብለው ጋዜጣ ያነባሉ፣ መፅሐፍ እያነበቡ ቁጭ ብለው ተጠቅመው ነው ተነስተው ተጠቅመው የሚወጡት። እና አሜሪካኖቹም ይመጣሉ። ያው አንድ ላይ ነው ኧ «ጋይስ ጋስ» ይላሉ፣ ፈሳቸውን ይፈሳሉ። ከዚያ ሌሊቱን ሙሉ ተቅማጥ በተቅማጥ። የጠጣው «እኔ ቀድሜያለሁ ሽንት ቤት፣ እኔ ቀድሜያለሁ» ግፊያው፣ ሩጫው፣ ጭቅጭቁ ሻምበሉ በሙሉ እንደዚህ ሲሆን ሲጫወ «ምን ዓይነት በሽታ ገባ? ይኼ ሁሉ ሰው እንዴት ተቅማጥ ያዘው? ምን በሊታችኋል? ምን በልተው ነው እንደዚህ ተቅማጥ የመጣባቸው?» በኋላ ቪኒገር መሆኑን አውቆ ይሰማል። ጥግሽ ማነው ያክተሩ ይስቃል፣ ይራገማል ምን ይላል፣ በለሊት ነዋ የተቀሰቀሰው። እንዲህ ሲሉ ነጋ። ያ ቆምጣጤ ሲያልቅ ተቅማጡም አለቀ። እንደዚህ ያለ ፈኒ የሆነ ኢንሲደንት አለ ለማለት ነው (ኮሎኔል አለማየሁ ካሳ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 9፣ ነሐሴ 21፣ 1999 ዓ.ም)።

ADDIS ABABA UNIVERSITY 'S LIBRARY

ሬ ትሬኒንግ አለቀ። ትሬኒንግ ካለቀ በኋላ አሁን ተራ በተራ ምንድነው የኮሪያ ግንባር እንደመቀነት ነው። ከምስራቅ እስከ ምእራብ ድረስ:: እንዲህ እንዲህ መቀነት፡ ጎኑ ልክ የኮሪያ ሲፐ አለው። ወገቡ ላይ ያለው እንዲህ ነው:: ዩናይትድ ኔሽን የያዘው ግንባሩን ክፍት የለም። ክፍት የለም። እንደ እንትን ነው ቦታ:: እዛ ላይ ሁሉ ዝግ ነው:: አንድ ክፍት እዚህ መሐከል በጭራሽ አይኖርም። ምክንያቱም ኸ በመጀመሪያ ጊዜ እኛ ከመድረሳችን በፊት ኸ የተባበሩት መንግስታት የአሜሪካንም ጦር እንደዚሁ አልፎ አልፎ ነው ሚይዘው:: በኋላ ግን ጊዳ ጊዳ ነው እነሱ ሲይዙ የነበረ። አሁን ቻይናዎችና ሰሜን ኮሪያዎች እንትኖች እሄንን አጥንተው ወደ ተራራ እየወጡ እና እንትን እያረጉ መሐል መሐል እየገቡ ብዙ ጊዜ ጉዳት እያደረሱ እስከ ፑሳን ድረስ ገፍተዋቸው ነበር እኛ ከመድረሳችን በፊት ከዚያ:: በኋላ እሄ ጥናት ተወሥዶና ዝግ ነው። በምንም መንገድ ማንም አይሾልክም:: እና ሁለተኛ ደግሞ ተራራ ላይ አልነበሩም። አሁን በኋላ ላይ ወደ መጨረሻ ከፍተኛ ቦታዎች ይያዝ ነበር:: ምክንያቱም ከፍተኛ ቦታ ምንም ጊዜም ብትይዝ አንተ የበላይ ነህ:: ወደታች ታያለህ:: አንዱ ለማጥቃት ሲመጣ ከታች ወደ አንተ ነው እንጂ የሚመጣ እንትን ነው እሄ ጠቃሚ ስለሆነ ከፍተኛ ቦታዎችን በሙሉ ይያዙ ነበር። በዚያን ጊዜ እና አሁን ይሄንን እንግዲህ ምናልባት እኛን የኢትዮጵያን ጦር አንድ ግንባር ሠጥተናቸው ብናገባ ምናልባት በዛ በኩል ሾልከው ይከብቡናል ብሎ አያምኑንም ነበረ። ገና አያውቁንም ነበር:: ገና አያውቁንም አላወቁንም:: እና በመጀመሪያ በምን ጀመሩ አንድ ሻምበል ጦር ከመግባቱ በፊት አንድ የመቶ ጦር ቢፐትሮል (ቅኝት) መልክ ሚሽን (ግዳጅ) እየተሠጠው እንዲሄድ ይደረጋል:: ይሄ እንትን እያለ ይደረግ ነበርና እንደዚህ ሆነን በግንባር በሻምበል ከመግባታችን በፊት በኮሪያ ግንባር እንትን ጠፋ። እስረኛ አልተያዘም። ለብዙ ጊዜ መረጃም በጣም ምታገኘው ከነሱ ነው:: ይናገራሉ። ምን ጦር እዛ አንዳለ፤ እንዴት እንደሆነ ይናገራል:: እና ትዛዝ ተሠጠን:: ማንም እና በግንባሩ እስረኛ ስላልተገኘ በተቻለ መጠን እስረኛ ይዛችሁ አምጡ ተባለ:: አሁን እኔ ከኔ ሻምበል አታችድ ሆኜ (ተካትቼ) ወደ አንድ ሻምበል የአሜሪካን ጦር እግረኛ ሻምበል አለ በእኛ ካለንበት በጣም እሩቅ ነው። እዛ አታችድ ሆንኩና መቶዎችን ይገፍ ሄድኩ:: የሄድኩት ቦታ በጣርታ ነው። ሄጄ ሪፖርት አደረኩለት:: እዛ ስደርስ እንግዲህ ሚሽን ሠጠኝ እሱ:: ገዜው ዝናብ ነበረ። ኸ ጭጋግ ነበረ። ተራራ ነው:: እዛ ስሄድ እኔ ወደ አስር ሰዓት ገደማ ነው እሱ ጋ የደረስኩት። ሄጄ ለሻምበሉ ሪፖርት አደረኩ እና ያሉኝ ወታደሮች ምናምን አሉኮ ቦታ የሱ ምክትል አለ። ቦታ ሠጠን:: እንደዚህ ምሽግ የምንይዝበት ቦታ ይዛችሁ እዛ ተጠብቁ ትዛዝ እስኪሠጣችሁ ድረስ። እሱና ከዚያ ተመልሼ እኔ ወታደሮቹን ቦታ አስይዤ ምሽግ ቤታችን እንትን አድርገን ቆየን:: ከዛ እንደገና ወደ አስራ ሁለት ሰዓት አካባቢ ጠራኝ:: ሄድኩና በጣርታ ቦታውን ያለንበት እያንበብኩ አውቃለሁ:: «አሁን ነገ በአስራ ሁለት ሰዓት ወታደሮችን ይዘህ ከኛ ጋር አንድ ኸ መግሪያ የመቶ ጓድ አታችድ ተጨማሪ የአሜሪካኖች

ናቸው አሉምግለሁ:: እነሱን ይዘህ በዚህ በኩል አድርገህ ይዢ የጠላት ምሽግ ነው:: ይሄ ምሽግ ነው እና እዚያ ውስጥ እስረኞችን ከዚህ ቦታ አንደኛ ሚሽን ይዘህ እንድታመጣ:: እስረኛ ሁለተኛ እስረኛ ከተገኘ በኋላ ባይገኝም ይሄ የጠላት ባንከር ምሽግ እንድትደበድብ::» የሚል ሚሽን ሠጠኝ እና «እዛ ሁነህ የምታደርገው ነገር ሁሉ ምንድ ነው በሬድዮ ሪፖርት እንድታደርግልኝ::» አለኝ:: ይሄንን ሚሽን ተቀበልኩና መጣሁ ጥዋት ለሊት ተነሳሁና ወታደሮቼን ብሪፍ አደረኳቸው የምንሄድበትን እና ያው ካርታ እኔ ነኝ የማነበው:: ጥቂት ወታደሮቼም የሚችሉም አሉ:: እንግዲህ እዚያ ሀገር ካርታ ማንበብ ቬሪ ቬሪ ኢንፖርታንት በጣም ጠቃሚ ነው፤ ምክንያቱም ተራራማ ነው:: እዎ እና ካርታ በጣም አስፈላጊ ስለሆነ በዚያ ካርታ መጠቀም ነው እና ይሄንን ጠዋት ተነሳሁና ወታደሮችን ብሪፍ አደረኳቸው የት እንደምንሄድ እና መንገዱ ያው በአንድ ተራ ነው ምትሄደው:: እንትን አድርገህ ነው የምትሄደው:: ሪቾ ነው ተራራ ነው:: እሱ ላይ እንደዚህ ብለህ ነው የምትሄደው እና እሱ ያው ካርታ ላይ ይታያል ግን መንገድ የለውም:: ሜካ ነው እና ይሄንን ብሪፍ አደረኳቸውና መጀመሪያ የሚሄደውን ጎድ ቀጥለው የሚሄደውን እኔ የት ቦታ እንዳለሁ በሬዲዮም በሬዲዮ እንዴት እንደምንገናኝ አሁን ኢታችድ የሆነው ኧ ጎድ ሃምሳ አለቃ የአሜሪካ ቀለብ መሣሪያ የያዘው እሱ መጥቶ ጠዋት ለኔ ሪፖርት አደረገኝ:: እኔም እሱን እንግዲህ ያለማመን ነው እንደፈለኩት እንትን አያደርገኝም:: ምናልባት ይፈራ ይሆናል |ግት| የሚል ነገር ስለነበረ እነሱ ነም ያው አደለሉቼ ሚሽን እነሱን ብሪፍ አድርጌ ሠጠኋቸሁ:: እነሱንም ሄድን ገና ከሠፈራችን ከነበርንበት ተነስተን አንድ መቶ ሜትር ምናምን ከሄድን ምንም አይታይም:: ጉም ሸፍኖታል:: ማንበብ አልተቻለኝም ምንም አይታይም ከፊቴ እንዴት አድርገን እንሄዳለን ትንሽ በኋ እንግዲህ በአስር ሜትር ላይ ነው እደዚህ የምታየው እንጂ ከዛ ውጭ ምንም የምታየው ነገር የለም:: በኋላ ትንሽ ከሄድኩ በኋላ አንድ ሁለት መቶ ሦስት መቶ ሜትር ሞከርኩ… ምንም አልታይ አለኝ በኋላ ጠራሁት ሻምበል አዛዡን የኛ አለቃን እና እዚህ እዚህ ደርሻለው በካርታ እንኳን ቅርብ ነው ቦታው እና ማየት አልቻልኩም አልኩት:: «ቆይ» አለኝ… «እዛው ባለህበት ቆይ አትንቀሳቀስ እና በተወሰነ ጊዜ ላይ ይለቃል ያን ጊዜ ትሄዳለህ…» አለኝ:: እውነትም ቦታችንን ይዘን እዳለ እዛ ቁጭ አልን:: ስንቆይ ስንቆይ ቀስ አለና አሁን እየለቀቀ ሄደ:: ዝናብ ነበር:: ጭምልትልታችን ወጥቷል እና እየለቀቀ ሲሄድ ተራራው ምናምን ይታያል:: አሁን ያለንበት ቦታ የት እንደሆነ በካርታ ላይ እያየው እንተርሴፕት እንትን እያደረኩ ኧ እንትን እያደረኩ እያየሁ እያየሁ ተነሳንና አሁን ግልፅ ብሎ የተባለው ቦታ ይታየኛል:: ሜካ ነው:: ግን ዝምብለን ስንሄድ ስንሄድ ስንሄድ በተራ በእንትን አድርገን ነው የምንሄደው ሄድን:: አሁን ከፊት ለፊታችን ወደ አንድ አራት መቶ አምስት መቶ ሜትር ርቀት ላይ ይሄ ምሽግ አለ ይታያል አሁን ተጠጋንና ከዚህ ከምሽጉ ታች ወንዝ አለ:: ቀጥን ወንዝ ነች:: በጣም ገደላማ አይደለም:: እዛ ደረስንና መቶ መቶዎቼን ማለው ወታደሮቼን ቦታ ቦታ የት የት ቦታ አስያዝኳቸውና አሁን በመነፅር



ILS LIBRARY ADDIS ... UNIVERSITY

እያየሁ ሳጠና፣ ሳጠና፣ ሳጠና፣ ላይ አሁን እንግዲህ ያየተሠጠኝ ሁለት ምሽን ነው:: አንደኛ እስረኛ ይዤ መመለስ አለብኝ:: ደግሞ እስረኛም ያዙ ስለተባለ ግማሽም ፎጣም የያዘ ምንም እንትን ያለ ማፈኛም ነገር ምናምን ነገር እንግዲህ በትምርታችን አፍነን ነው እንግዲ አዳያሩሙህ የሚባልም ነገር አለ:: ከዛ እዛ ቦታ ደረስንና እንትን ስንል አንድ ከሁለት ከተሰጡኝ ሁለት ሚሽኖች አንዱ እንግዲህ ባንከር አለ:: አሁን ሰዎቹ እዛ ውስጥ ጉድጓድ ሲቆፍሩ ሲንቀሳቀሱ ምናምን ይታዩናል:: አሁን ደግሞ ሁለተኛው እስረኛ ነው እንደዚህ በደንበ አድርገን ከሁለት አንዱ እስረኛ ከተገኘ ተገኘ:: ካልተገኘ ያንን ባንከር ልናፈርስ ነው:: እና ከኔ ጋር ያሉትም አሚሪዎች እንትን መግረያ እንትን የያዙ የማይራገጥ መግረያ እኔም አለኝ… ሁለቱን ቦታ ሠጠኋቸውና ወደ እዚያ አልመው እንትን ባንከር ላይ በትዕዛዝ እንዲተኩሱ አዘጋጀኋቸው ሳለ አንድ ቻይና ከጉድጓድ ውስጥ ከዛ ትወጣና ውሃ ለመቅዳት ተመጣለች:: እንትን ነው እንደው ውሃ ሲቀዱ ይሄ እንትናቸው ላይ ግራና ቀኝ የተንጠለጠለ እንትን ነው ከዛ ውስጥ ወጥቶ ወደ ወንዙ ይመጣል:: ከኛ በታች ነው እንግዲህ ወንዙ ያለው… እነሱ እዚህ አፋፍ እንትን ላይ ነው ያሉት:: እና ስትወርድ አየሁ አሁን ጥሩ አጋጣሚ ነው እንግዲህ አንድ እስረኛ ለማግኘት እድል አለን:: ከበደ ደፋር የሚባል አንድ አስተዳደር ሦስተኛ ጓድ አዛዥ ነው:: ጎበዝ ልጅ ነው:: ከበደ አልኩት:: ይታይሀል? አልኩት… «አዎ አይቻለሁ» አለ:: የሱ ጓድ በንደዚህ ያለ በቀኝ በኩል ነበር ቦታ የያዘው:: አንድ ቀላል መግረያና አራት ወታደሮች ያዝና ውረድ እና ልቀም እዛ እንትን እንዳትጮህ ተጠንቀቅና አፍናችሁ ያዙ አልኩትና ላኩት:: ሄደ እሱም:: ተሽሎከለከና ጫካ ለጫካ ወንዙ ጋ ሄደ… ከዚያ በኋላ እሷ መጣች:: እዛ ወንዝ ውሃ ለመቅዳት እንትን ሲል ያፍኑታል ይዘሉና እንደፈራነው እንዳያሩሙህ ለመሙህ ሞከረ:: ተንፈራገጠ:: እንደው መያዝ አቃታቸው:: ከዚያ በኋላ ቂጡን በግንጀ ሎት አደረገና |ግቅ| ወጉና አፍነዋት ይዘው ጎትተው መጡ:: ከዚያ በኋላ ልክ እሱ እንደ ደረሰ በሬዲዮ ነገርኩት ለሻምበል አዛዥ:: አንድ እስረኛ አግኝተናል ይዘናል አልኩት:: «እና እሱን ባፋጣኝ ወደ ላይ ላኩት» አለ:: እንግዲህ እኛ ከነሱ ትንሽ አልሞስት ወደ ሁለት ኪሎሜትር ርቀት በላይ ነው ያለነው:: አሁን ተራራ ነው እኛ በጣም ወርደናል:: ታች ነው ያለነው:: እና ከዛ በጥቂት ወታደሮች አስያዝኩና እንግዲህ መንገድ ላይ እንዲጠበቁና እንትን እንዲሉ እሱን ላኩ:: አሁን እንግዲህ ሁለተኛ ሚሽን ነው የቀረኝ:: ደግሞ እዛው እያየን ደግሞ አንድ ትንሽ ቤት ደግሞ ሰዎች አሉ:: ይሦሉ… ይወጣሉ:: ኧ ኮሪያኖች ሊሆኑ ይችላሉ:: እና ይሄንን ሪፖርት ሳደርግ ምን አለ ከተቻለህ እዚያ ውስጥም እስረኛ ይኖራል እና ትንሽ ከኛ ይርቃሉ:: አሁን እንግዲህ ኧ እዛም ሲመላክ ጥናት እንትን እያስጠኩ እያለው አሁን ምሽግ ውስጥ ሚተራመሱትን ሰዎች ሪፖርት ሳደርግ ለማስመታት እችላለሁ አለ:: እምን አልኩት:: ቦታውን በካርታ ቁጥር ሠጠሁትና መድፍ አዘዝኩ:: መድፍ እኔ እንትን ከመተኮሱ በፊት መድፍ አዘዝኩ:: ሰራውንድ እንትን የሚባል አለ እና ከዚያ በኋላ ጠብቅ አለኝ:: ጠበኩ:: ከዚያ በኋላ መንገድ

ላይ ነው አለኝ፡፡ ያን ነው ቃሌን የሠጠሁ፡፡ መጀመሪያ ጢስ ተኮስኩ፡፡ ጢሱ፡፡ ማስተካከያ ነው ተተኮሰ፡፡ አንደኛው መጀመሪያው የመጀመሪያው ከኛ ፊትለፊት ሁለተኛው ሲተኩስ ከነስ ደርግ አሁን በነዚህ በሁለቱ መሐል ነው አስተካክሎ የሚሠደው፡፡ እና አስተካክሎ መንገድ ላይ ነው ያለው አለ፡፡ ሹኩ...ሹኩ...ሹኩ እያለ መጣ፡፡ ከው...ከው...ከው... ያቺን ቦታ አመድ አደረግንና ከዚያ እንዴት ነው አሁን አለ ልድገም ወይ አለ፡፡ ይበቃል ጠብቅ እንደገና አልኩት... እና ቀኖን እዛ ውስጥ እንግዲህ አሁን እንደገና ጉድጓድ እንትን ለማለት እንትን ያለ የሞተ ሰው ይኖራል አሁን ምን አለኝ ሂድና ያን እዚያ አሁን የተደበደበ ቦታ ቼክ አድርግ አለኝ፡፡ ይሄንን እንግዲህ እሺ አልኩና አሁን እኔ ከመግባቴ በፊት ደግሞ የግድ በፊት መግቢያ እነዚያን የሚታዩት ባንከሮች ምኖች እንግዲህ መምታት አለብኝ እነሱን አፈራርሼኩና መግቢያ ስመጣ ሰዓቱ አሁን እየሄደ እንትን አለ፡፡ ገና እኛ ከዛ እስክንመለስ ድረስ ሊጨልምም ይችላል፡፡ እና ጊዜው ጥሩ አይደለም፡፡ እኛ መሀል ላይ ነው እኮ ያለነው፡፡ አሁን እንግዲህ አውቀ፡፡ እኛ እዚያ አካባቢ መኖራችን እና በአዳፍኔ ከኋላችን ከው...ከው...ከው... እየለቀቁ እየተኮሱ እንትን አለ፡፡ እንግዲህ አሁን አለ ተመለስ አለ ተመለስን እኔ እነዚያ አሚራሆኖች ከኔ ጋር ያሉት ትንሽ እንትን ሆኑ እና ተመለሱ አለ፡፡ ቅድም በመጣነው መንገድ እንደገና መቶዎቹን አለዋወጥኩና አንዱ ሲሄድ አንዱ ደግሞ ሊለውጥ አንዱ ሲሄድ እንደዚህ ተራ በተራ አደረግንና ያቺን ቤት በዚህ በጢስ አለን የሚያቃጥል በማይፈነዳ መግቢያ አለን እምሳ ሰባት መግቢያ እንትን አለን፡፡ በሱ አቃጠልኩት፡፡ እሱን ቤቱን ከነ እንትን እዚያ ውስጥ ያለው ሁሉ ተቃጥሎ ሊሆን ይችላል፡፡ እና እሱን አደረግንና እንደዚህ እያደረግን ተመልሰን እስረኞችንን ይዘን እሱ አረዳ ወሰዱት ወዲያውኑ ተቀባብሎት ለመረጃ ወደ ጠቅላይ ሠፈር ወሰዱት፡፡ እኛ በዚህ ዓይነት ተመልሰን ሠፈር ገባን፡፡ ከዚያ አንድ ቀን አደርኩና ከዚያ በኋላ እንደገና ሚሽኔን ጨርሻለሁ ወደ ሻምበሌ ተመለስኩ፡፡ እንደዚህ ነበር (ብርጋዲየር ጀኔራል ደስታ ገመዳ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክሪብ ገጽ 7-10፣ ነሐሴ 23፣ 1999 ዓ.ም)፡፡

7 ከበደ ደፋርና አያሌው ካሣ የሚባሉ ሁለት ወታደሮች፣ በጦር ግንባር ምርኮኛ ጠፉ፡፡ አሚራሆኖች ምርኮኛ እንደናመጣ አዘዙን፡፡ እንዱም ትልቁ ስማችን ያስነሳው እውነቱን ነው አሉ፡፡ እነዚህ ወታደሮች ሄዱ በፍቃደኝነት ምርኮኛ ሊያመጡ፡፡ ሄዱና ቻይና ምሽግ ውስጥ ገቡ፡፡ እዚያ ስራቸው ምንጭ አለች፡፡ እዚያ ጫካ አለ፡፡ ጫካው ውስጥ ተደብቆ ውሃ ሊቀዳ መጥቶ ወታደሩ ነገበስ ሲል በብርድ ልብስ ጠቅለል አድርገው ተሸክመው ወሰዱት፡፡ አሚራሆኖች ድንቅ የሆነባቸው ይህ ነው፡፡ እንዱ ተዓምር የሆነባቸው እንዱ እሱ ነው (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 2፣ ስክሪብ ገጽ 29፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)፡፡



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

8. አዛ ምሽግ ላይ አንድ ታሪክ የማስታውሰው ቻይናዎች ለካስ ይራቡ ኖረዋል፡፡ አሁን ምግብ ለመስረቅ እየተሳበ መጥቷል፡፡ አንድ ወታደር ይህንን ከበደ ያልኩህ ወታደር ሲመለከት እየተሳበ ይመጣል፡፡ ምሽጉን ትቶ ወጥቶ እሱ ላዩ ላይ ኧ ቁጭ ይላል ከምሽጉ ወጥቶ፡፡ ያ ቢሉ በመታኮሻ ዘሉ ውስጥ ሲገባ ሽቦ አለ፤ ቦምብ እንዳይጣልብን ከላይ የምናደርገው፡፡ ያን ሮጭን ያደረግና «ብይ እስቲ ውጪ» ይላታል፡፡ «ማርኪያስሁ!» ይላል፡፡ እኔ በዕውነቱ አላመንኩም፡፡ ስሄድ «እዚህ ውስጥ ነው ያለ፡፡» አለኝ፡፡ ኋላ ቁጭ ብሎ ሲጋራውን ያጨሳል፤ ከዛ አንስቶ የወታደሩን ሲጋራ፡፡ ከፍቶ ይበላል፡፡ ያንን ምርኮኛ ይዘን ላክነዋ! አስረከብን [ሳቅ]፡፡ እንደዚያ ያለ ነበረ (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ፤ ቃለ መጠይቅ፤ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 14፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)፡፡

9. በሦስተኛው ቀን ፈረንሳዮች ይደመሰሳሉ፤ ግንባር፡፡ ኢትዮጵያ ጦር በአስቸኳይ ጦር ግንባር እንዲገባ ይባላል፡፡ ያን ፈረንሳይ የያዘውን ቦታ ለመያዝ ሲባል ሌሊት ከተኛንበት ብቻ እየተሰቀሰ እንዘልጥሉ ወደ ኮሪያ፤ የጦር አዛዥ የለማ፡፡ ደረስን፡፡ ስንደርስ ጦር ተዘጋጅቶ ጠብቶን... ነን ይገባሉ ተብሎ ነው፡፡ እኛ ሌሊቱን በቃ በአውሮፕላን አገዘው ኮሪያ ደረስን፡፡ ነጋ ትናንትና ማታ ዳንስ ቤት መብራት ያመሸ ሰውዬ ዛሬ ማታ ጨለማ ውስጥ ወደ ተደገፈ ገባው [ሳቅ]፡፡ ኋላ አጥቅተን ገባን፡፡ በዕውነቱ ቻይናዎቹ ይዘውታል ያን ፈረንሳይ የለቀበት ተፈራ፡፡ አሁንም ደግሞ በስተቀኝ ክንፍ የነበረው የኛ ጦር እንዲያጠቃ ተደረገ፡፡ እኔ እኔና ሁለተኛ መቶ ነን ያጠቃነው ያን ጊዜ ደግሞ ኧ ገባን እና በውነቱ ብዙ ጉዳት አልደረሰብንም፡፡ ለምን ቢባል? ኮሪያኖች ፈሩ አሁን በዕውነቱ፡፡ ከአፍሪካ ሰው የሚበላ ጦር አምጥተዋል የሚል፡፡ ጀነራል አማንን ኧ የውሻ ጅራት አስመስለው ስለው፤ ሥጋ እንደዚህ እየበላ [ተፈሊጠው ሥጋ የመጋጥ ዓይነት የሰውነት እንቅስቃሴ አደረጉ] አስመስለው ቻይናዎች ስላጠጡ ይህንን ጀመረ፡፡ አይዋጋንም፡፡ ይፈራሉ፤ የተማረኩ እንደሆን አርዶ ይበላናል እያሉ፡፡ ከአፍሪካ ሰው የሚበሉ እመጡ አሉ፡፡ ሰው የሚበሉ ሰዎች ናቸው ብለው ፈጠሩ ፊላቸው፡፡ ፊላቸው የፈጠሩት እንጂ ምንም፡፡ ታዲያ ምን ልበልህ እዚህ ላይ ወታደራዊ ሳይኮሎጂካል ምን ይላል? የምታደረገው ፕሮፓጋንዳ ተመልሶ እንዳይወጋህ ተጠንቀቅ ይላል፡፡ መልሶ ወጋቸው ለፊላቸው (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ፤ ቃለ መጠይቅ፤ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 13-14፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)፡፡

10. ቀድሞ እንደዚሁ የነበርከው ጥሩ ሥራ ሠራሁ ያልኩት ምንድነው፡፡ እዛ እስታንድቪል ሁለት ሻለቃ ጦር ነበረ፤ ከበር ዘበኛ [እስታንድቪል ማለት ኮንጎ ውስጥ የሚገኝ የቦታ ስያሜ ነው] እኔ አንደኛው ነኝ፡፡ እና ኪንዱ የሚባል ቦታ ኪንዱ ያለበት ቦታ ኧ ድሮ የዩናይትድ ነሽን ወታደሮች ነበሩ [ኪንዱ ማለት ኮንጎ ውስጥ የሚገኝ የቦታ ስያሜ ነው]፡፡ አንድ



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

አውራጃ ነው፣ ሩቅ ነው ከስታንድቪል። እና እዛ ምን ይሆናል ኧ ወታደሮቹን ሕዝቡ እዛ እንትን አደረገና ሸሹና ወጡና ሄዱ። ታይላንዶች ነው ምንድነው እንደዚህ ያሉ ነገር ናቸው የዩናይትድ ኔሽን እንትን ነበር፣ ሻምበል። እና እነሱ ሸሽተው ሄዱ። አንድ አውሮፕላን ስንቅ ይዞ ከስታንድ ቪል እዛ ይሄዳል፣ ኪንዱ። ጣልያኖች፣ የጣልያን አውሮፕላን ነው፣ ለእርዳታ የሄደ የዩናይትድ ኔሽን እንትን ውስጥ። አስራ ሦስት ጣሊያኖች ነበሩ። በልዩ ልዩ ቴክኒሻኖች ምናምኖች ናቸው። ሄዶ እዚያ አውሮፕላን ማረፊያ እንዳረፉ ኮንጎሊ ወታደሮች ሄደው ያዟቸው። ያዙና አውሮፕላኑን አስጠፍተው ምን ብሎ እንትን አደረጉና እነዛ አሥራ ሦስቱን ረሸኗቸው፣ ገደሏቸው። በኋላ ዩናይትድ ኔሽን እዛ ተደናገጠ በጣም። እና እንዴት እንደዚህ ተደረገ? ተባለ። እና አንድ ጦር በአስቸኳይ እዚያ ቦታ መሄድ አለበት ተባለ። እንግዲህ በአውሮፕላን ነው እንጂ በመኪና መሄድ አይቻልም ሩቅ ነው። ከዛ የኔ ሻለቃ ታዘዘ። እና እኔ በፊት እንደምነግርህ ነው አሁን አንድ ኃላፊ አደረጉኝና እዛ ቦታ እኔ አናውቅም። ኤሪያውን፣ አካባቢውን በጭራሽ አናውቅም። እና በካርታ ነው። ኪንዱ ነው ከተማው። አንድ አውሮፕላን ማረፊያ ምና ምን አለ። እና አሁን ያንተ ጦር ይሄዳል አለ። እና ከሶስት ቀን በኋላ ተንቀሳቀስ ስትባል ትንቀሳቀሳለህ ተባለ። ጦሬን አዘጋጀሁ። ከዛ በኋላ ኧ የአሜሪካና የዩናይትድ ኔሽን አውሮፕላኖች መጡ። የመጀመሪያው ስልሣ ወታደሮች አንድ የመቶ የሚሆን ያዙና እስታፎችን ይዤ ወደዛ፣ ከኃይሌቶቹ ጋራ። እንግዲህ አሁን እኛ ማንም የለም። ሊመቱንም ይችላሉ ስንወርድ። እና እርግጥ ኃይሌቶቹ ያውቃሉ ቦታውን። እና እንዴት አርገን ነው ምንወርደው። ማን ኮኔክሽን ምንም የለም። እና አደጋ ይደረጋል ተብሎ ተሰጋ በጣም። እውነትም ነው። እኔም በድፍረት እምቢ ማለት አልችልም። ሦልሳ ወታደሮቼን አንድ አውሮፕላን ውስጥ ጫንኩና ኃይሌቱ ጋር ተነጋገርኩ። «ስትሄድ ዝም ብለህ ቀስ ብለህ ወረድ ወረድ እያልክ ድምፅ በጣም እንትን ማታደርግ በጸጥታ ብቻ ውረድልኝ» አልኩት። «አደርጋለሁ» አለ። እንግዲህ ኮንጎ ጫካ ነው በየቦታው። ከከተማው ደግሞ ይቺ ሁለት ኪሎ ሜትር ትርቃለች፣ አውሮፕላን ማረፊያው። ቀስ ብለን ሄዶ ሸርተተተት አለና ጠብ አደረገን። እዛ ታወሩ አጠገብ አወረደን። ቶሎ እኛ ወረድንና እንተ ጥፋ አልነው። ከዛ እኛ ያቺን አካባቢ በስልሣ ወታደሮች ቦታዎችን ከበብንና ያዝንና ጭጭ አልን። አንድ አውሮፕላን በተጨማሪ ተከትሎ ነበር። እሱም እንደዚሁ ቀስ ብሎ ወረደ። አሁን አንድ ወደ መቶ ስልሳ ነው መቶ አርባ የምንሆን ያቺን ቆፋፈርንና ምሽግ መሸገን ቀጭ አልን። ምንም ምንም ግንኙነት የለንም። ከዛ አሁን በማግስቱ እንግዲህ ጦር ይመጣል ቀጭ አልን። ከከተማ የሚመጣ የለም። ሰው አያየንም። እኛም አናይም። እዚያች መሸገን ደረቅ ራሽናችንን እየበላን ጭጭ ብለን ምሽጋችንን አጠናከረን ጠበቅን ዝም ብለን። እንግዲህ ማታ መጥቶ ያጠቁናል ብለን ስንጠብቅ ስንጠብቅ እንግዲህ ምንም አልመጣም። ከዚያ በኋላ በሁለተኛ ጊዜ ወደ አራት ሰዓት አምስት ሰዓት አውሮፕላን መምጣት ሲጀምር ምንድነው እዚያ ያለ? ብለው አንድ የመቶ አለቃ እንትን አለች መጣ።

በአንድ ጂፕ መጣ። ምንድናችሁ እናንተ? አለ። ኧ እንትን እንገናኝ ተባባልን። እናም መሸገናል እዛ ወታደሮች ቆም ቆም ብለው እንትን አሉ። ደነገጠ። እሱ መጣ። አነጋገርነው፣ ተግባባን በቃ። እኛ ኧ ጥቁሮች ነን ቀለማችን እንደ ነው። ፈረንጎዮች አስተርጓሚዎች አሉን። እነሱ ፈረንሳይ ነው የሚነጋገሩት። አስተርጓሚዎች ልጆች ነበሩን። እና ተግባባንና ምን አልንና ቀስ በቀስ ወታደር እየገባ እየገባ እየገባ መጣ። ተጠናከርን። ከዛ በኋላ ሄዶ እሱ ለቀሩት ነገረ። መጡ። ምንድናቸው? እንዴት እንደዚህ ሆነ? እንዴት ተደረገ? እንደዚህ እንደዚህ አልን። ወታደሮች አላግባብ አደጋ አድርሰው ነው። ስህተት ተደረገ ምናምን አሉን። ተግባባንና ከዚያ በኋላ ቀስ በቀስ ለነሱ መጠጥ ኧ ይወዳሉ። አልኮል ምናምን ሁሉ ሠጠናቸውና ከዚያ በኋላ ከተማ ገባን። መኪና የለንም። እዛ ደግሞ ሚሲዮኖች፣ ሌሎች፣ ሌሉች ነበሩ። ተዘረፍን ተብሎ ሁሉም በር ዘግቶ ጭጭ ብሎ ቁጭ ብሏል። በኋላ በአንድ አውሮፕላን አስመጣን፤ አንድ ሃያ በርሜል ቤንዚል። ከዛ በኋላ መኪና ተከራየን። እየጨመርን በሱ እየነዳልን እኛም ሹፌሮች ነበሩን የኛ ደግሞ ሌላ መኪና ደግሞ እንደገና የሚመጣ አለ በኮንጎሌ ወንዝ ላይ ነው የሚመጣው፤ በጀልባ። እነሱ እስኪመጡ ብለን ተከራየን ቀስ በቀስ ገባን። እዛ ከተማ ያዝን። ከተማዋን ያዝን። ትምህርት ሚኒስቴር ነበረ። እዛ ውስጥ ሻምበሎችን አስቀመጥን። አውሮፕላን ማረፊያውን ሲኪውርድ አደረግን። ከተማዋን ሲኪውርድ ያዝንና ከነሱ ጋር በመግባባት እንትን በማለት በደንብ አድርገን ተቆጣጠርን። ከዚያ አውሮፕላን ማረፊያ፤ ማነው እነዚህ የተገደሉትን ኢጣሊያኖችን የት እንዳሉ ኢንፎርሜሽን ነገሩን። እነሱን ሪፖርት አደረግን። ከእስታንድ ቪልም [ኮንጎ ውስጥ የሚገኝ የቦታ ስያሜ] የዩኤን ተጠሪዎችም ምኖች መጡ። ቦታው ተገኘ። አስቆፈርን። አስራ ሦስቱንም ኢጣሊያኖች አወጣን። ከዛ ግጥን ምናምን አምጥቶ እዛ አሽገን ምን ብለን ከዛ በስርዓቱ ተሠልፈን ሰላምታ ሰጠን። ወሰድናቸው። ከዛ ኪንዱን [ኮንጎ ውስጥ የሚገኝ የቦታ ስያሜ] እስከ አራት መቶና ሦስት መቶ ኪሎ ሜትር ከከተማ ውጪ እየተቆጣጠረ ህዝቡን ሁሉ [አልተሰማኝም] አደርገን፤ እንትን ሲኩርድ አደርገን፤ ጥሩ ሥራ ሠርተን፤ ሕዝቡንም አረጋግተን ኧ ሥራቸውንም እንዲሠሩ አደርገን፤ እዛ ጥሩ ሥራ ሠርተን ከሕዝቡ ጋር በሰላም ለመገናኘት መከራ በምናደርግበት ጊዜ እቴጌ ሞቱ። ይሄ እኛ ልንደንስ፣ ጭፈራ ምናምን ልናደርግ ነበረ። ሞቱ አሉን። ከበር ዘበኞችንም ጥቁር ጨርቅ አሰርንና በቃ ቁጭ አልን። ምንም እንትን መሠራት አልተቻለም። በእንደዚህ ያለ እዛ ዘጠኝ ወር ነው የቆየነው። አልሞላት አንድ ዓመት ቆየን። ሕዝቡን በደንብ እንትን አድርገን ምን ካልን በኋላ ከዛ መጣን (ብርጋዲየር ጀኔራል ደስታ ገመዳ፤ ቃለ መጠይቅ፤ ካሴት ቁጥር 2፤ ስክርብ ገጽ 14-16፤ ነሐሴ 23፤ 1999 ዓ.ም)።

11 የኮንጎውን የሠራሁት ስራ እኔ በወታደርነት በነበርኩበት ሕይወቴ እንደዛች ቀን የማስታውሰው ነገር የለም። እዩ፤ ጦሩን በትንን በትንን በየአቅጣጫው እንግዲህ ሠላም



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

እስከባሬ ነው የሄድነው። ጦርነት አይደለም የሄድነው። ሁለት ሻምበል ብቻ ነው ያለው። ሞስኮቦች፣ ፈሻዎች አስር አውሮፕላን ይዘው መጡና ሄዱ። በአንድ ቀን ሲሊት ኤር ኮንጎ [የኮንጎ አየር መንገድ] የሚል ጻፉባቸው። ከዚያ አምስት ሺህ የሚያህል ጦር ይመጣልህና ወደ ኪታንጋ እየተንጠለ ነበረ፤ ይሄ አንድ ቾምቤ የሚባል እሱን ለመውጋት። አምስት ሺህ ጦር አውሮፕላን ማረፊያ እየደሰፈረ የተባበሩት መንግሥታት አውሮፕላን ማረፊያ እንዲዘጋ እንዲደነስ አለ። አሁን ትዕዛዝ መጣ። ተደብቀው ሻለቃ አዛገና ምክትል አዛገች፣ የሳቸው ምክትል ነበሩ ጄኔራል ግዛው፣ የዮሐንስ ሺታ። ኮንጎ፤ ኮሪያም አዛገቹ ነበሩ እሳቸው፣ ይማከራሉ። «ምን ሆነው ነው ዛሬ ተዘግተው የተቀመጡ እነዚህ ሰዎች?» እላለሁ። አሁን ኃይለ ስላሴ በላይነህ የሚባል ኮድ እየዛፈ የሚያስተላልፍ፡ አዲስ አበባ «ኧረ እስቲ ገብረ የሱስን ብታማክሩት ምን ቸገራችሁ? እሱ አንድ መላ አያጣም» ይላቸዋል፣ እሱ። ጠሩኝ «ገብረ የሱስ» ብለው። አሁን ምን የሚል የመጨረሻ ቴሌግራም ይመጣል፡ ጃንሆይ ምን ያላሉ «እኛ ለተባበሩት መንግስታት አግልፈን ከሠጠናቸው የሚሏችሁን ፈጽሙ» የሚል ቀርጥ ያለ ትእዛዝ መጣ። «እኛ ሰው የለንም እንዴት እናድርግ ብንዋጋ ማለታችን ነው» የሚል ነው የሚያስተላልፉት። ኧኧኧ «አውሮፕላን ማረፊያ እንዲዘጋ ታዟል። እና አንተ የውጊያ ትእዛዝ አዘጋጅ።» «ምን? ከኮንጎሌዎች ጋር ልንዋጋ? እሺ! ጥሩ አድርጌ አዘጋጃለሁ። ቁጭ በሉ እናንተ» አልኩና «ጠብቁኝ፤ አሁኑኑ አርቅቄ አመጣለሁ» አልኩና እየበረርኩኝ መሀላቸው ሄጄ ጥልቅ አልኩ!

ምናቸው መጣል? [ልጃቸው ጠየቀ]

ሄድኩና አዛዡን [ተራኪው]

ማን ጋር ነው የሄድከው? [ልጃቸው ጠየቀ]

አስተርጓሚ ይዤ፤ አንድ አስተርጓሚ። [ተራኪው]

ኮንጎሎቹ ጋር? [ልጃቸው ጠየቀ]

ኮንጎሎቹ ጋር። «እየውና መጣትያ ነው ያደረጉን፤ እኛን አፍሪካውያንን ለማዋጋት እርስ በርሳችን።» ጨለመር እረከባት፣ የለለ። ቤልጅግ ይፈራሉ በጣም። «የቤልጅግ አውሮፕላን ላየርፍ አይቀርም። በአውሮፕላኖቹ፣ እንዲደነስ ዝገባቸው። ጦሩም እንዲደነግ ብለው አዘዋል። እርስ በእርስ ያፋጁናል። መጣትያ ሊያደርጉን ነው። ነገ ታዲያ፣ ይቺ ናት አሁን፣ ነገ እሱ የአፍሪካ አንድነት ይመሠረታል። ኮንጎሌና ኢትዮጵያ ተዋጉ ተብለን መጣትያ እንሆን እንዴ?» አዛዡ አሰበ፣ መኮላ ይባላል፣ አሰብ አደረገና «ለኔ ተውልኝ» አለ። መኮንኖቹን ነው ሰብስቤ ያነጋገርኳቸው። «ዝም በል አንተ፣ ተከተለኝ ብቻ» በመኪና ጫነና ወሰደ ብቻ አውሮፕላን ማረፊያ በርሜል ቁጭ አደረገበት። አሁን «ታዘዝን፣ እኛ ምን እናድርግ? ቀንሱ» አሏቸው ወታደሮቹን።

ይህን አድርጌ ስመጣ እነሱ ተጨንቀዋል ሁሉም [የኢትዮጵያ ጦር አዛዦች]። «አዚጋሁት አውሮፕላን ማረፊያ፣ አውሮፕላን ማረፊያው ተዘግቷል። «ምን? መዚጋት ምን ማለት ነው? አውቀሃል?» አሉኝ አለቃዬ። «ሄዳችሁ እዩት ብትፈልጉ በርሜል ማስቀመጥ እኮ ነው።» መስኮቶች ከየአውሮፕላናቸው ሳይቀሩ ዕቃቸውን እየጠቀለሉ ወደ ሆቴላቸው። ከዛ በኋላ «ሻምበል ገብረ የሱስ ሚካኤል የተባለ ከዛገሬው ጦር ጋር በመስማማት አውሮፕላን ማረፊያውን በሰላም አዘግቶታል።» ብሎ ለጃንሆይ ቴሌግራም «ፈተን ለማየት እግዚአብሔር ያብቃን» ሲሉ መልስ ሰጡ፤ ጃንሆይ (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 2፣ ስክርብ ገጽ 34-35፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)።

12. በስታርስ ኤንድ ስትራይፕስ ጋዜጣም ደግሞ መጨረሻ ሲወጣ፣ ጦርነቱ ሲያልቅ «ነን ስኪንድ ኢን ኮሪያ» የሚል ነው ያወጡት [ስታርስ ኤንድ ስትራይፕስ ጋዜጣ በኮሪያ ጦርነት ወቅት ከደቡብ ኮሪያ ጎን የተሰለፉ የተባበሩት መንግስታት ጦር ልሳን ነው]። ተወዳዳሪ የሌለው በኮሪያ ጦርነት የሚል ነው ያወጣው። ተወዳዳሪ የሌለው በሚል፣ ጋዜጣ እስታር ኤንድ ስትራይፕስ በሚል የጦርነቱ ጋዜጣ ነበረ፣ በሱ ላይ አውጥቶታል። ስለዚህ አለም ያደነቀበት ማነው እና እ የኢትዮጵያ ጦር የሰራው ስራ በኮሪያ እ. በውነቱ በዚህ ለስት አመቱ ውስጥ ቻይናዎቹ ራሳቸው መስክረውለታል። እና ይሄን ትውልዱ እንዲያውቀው ያስፈልጋል፣ እ ትንሽ ስላልሆን። አለም በሙሉ ነው ያደነቀን። አብሮን የነበሩ የቃል ኪዳን ሃገሮች በሙሉ እንኳን አድንቀውልናል። በጣም ነው የተደነቀልን (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 2፣ ስክርብ ገጽ 20-21፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)።

13. እረ በውነቱ ኧ አሁን እንዳልኩህ ከመጀመሪያው ስላስደነገጠን ህዝቡ ኧ በጣም አያዘን፣ እያዘንን ነው የሄድነው። እና ያው ጅቡቲ ደረስን። ጅቡቲ እንደደረስን የጅቡቲ ኮሚዩኒቲ የኢትዮጵያ ህዝብ እዛ የነበረው ተገልብጦ መጥቶ ሸኘን። እና በእውነቱ እያዘንን ነው። የንጓዝ ነበር (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 4፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)።

14. የፈረንጅ ምግብ ነው፤ ግማ ነው። እ ምን በቶሎ አለ። ልዩ ልዩ ነገሮች አሉ። እነዛን የመኳኳሉ ነገር ያቀርባሉ። ብሉ አሉን። እኛም ዳቦ ቶሎም ይዘን ነበር። እ ዳቦም፣ ቆሎም የዘን ነበርን ያንን አልበላንም። ያንን ለመድን ለመድን። ማርመራታ አለ፣ ወተት አለ። አንድ ለስላሳ ሰስ የምትባል መጠጥ አለች። ቢንጉ ይሏታል። በቃ እሷን እንጠጣለን ጥሩ



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ነው:: በቃ ሌሎች ታመሙ:: እኔ ምን በሽታ የሚባል ነገር አላየሁም (አስር አለቃ አሰፋ አስፋው፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 5፣ ሐምሌ 30፣ 1999 ዓ.ም)::

15. መርከቡ ውስጥ የተማሬርነው የኢትዮጵያ ጦር፣ የግሪክም አንድ ሻለቃ ጦር ነው፤ እና የታይላንድም:: ኋላ በመንገድ ላይ፣ ኋላ እንሳዋለሁ፣ ኸ በእውነቱ ምግቡ እጅግ በጣም በጣም ቆንጆ ነው:: ነገር ግን አያስበላህም ማዓበሉ:: ሲሲክነስ ባህሩ፣ እሄ ማዕበሉ መገለባበጥ ማስታወክ፣ ማስታወክ ነው:: እና ሰብዙዎቹ አልተስማማቸውም:: እኔ ግን አንድ ቀን ሳልታመም ነው የደረስኩት:: እግዚአብሔር ይመስገን፣ እግዚአብሔር ረድቶኝ ምንም አንድ ነገር፣ አንድ ቀን:: መርከቡ እንዲህ ሳህኑ እላዬ ላይ እየተደፋብኝ ምግቡን እየዋጥኩ ነው የደረስኩት (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 5፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)::

16. ጥያቄ፡- የመርከብ ላይ ህይወትን እንዴት አገኙት?

መልስ፡- እእእ! እንዲያውም ጥሩ ጥያቄ ነው ያመጣኸው:: ወታደሮቹ የማዕበሉ መገለባበጥ በጣም ኸ ታመሙ:: ኋላ አንድ ወታደር ሞተብን፣ መርከብ ላይ:: በአሜሪካኖች ህግ መርከብ ላይ የሞተ ወታደር ወይንም ሰው ባህር ይጣላል እንጂ ሬሳ ተገቦ አይሄድም፤ በህጋቸው:: ከዛ ኋላ የእኛ ወታደር ገንዘው ኸኸኸ ባህር ሰመጣል ኸ እኔ ተጠርቼ እንደ አጋጣሚ ሻምበል አባገርና ጀነራል መርዕድ ግዛው ይባላሉ:: አምና ሞቱ:: እሳቸው ኸ ጥሩ ምክር መከሩኝ:: «ክየሻምበሉ አንድ አንድ ጓድ ይመጣልሀልና ወታደሮቹ እንዲያድሙ አርጋቸው:: እንዴት! የወንድማችን ሬሣ አናስጥልም:: ዓይናችን እያየ ባህር አይጣልም:: ወታደር ወንድማችን::» ብለው «እንዲያድሙ አድርግ::» አሉኝ:: /ፒፕሲና የገብስ ቆሎ እየቀረበልኝ ስለነበረ ቀርቦልኝ እስኪያልቅ ዝም አለ/ አድርግ አሉኝ:: ከዛ በኋላ ኸ ወታደሮቹ ተሰበሰቡና ለወታደሮቹ ይኸን ነገርኳቸው:: ኸ በእውነቱ የሚደንቅህ ነገር ኸ ውስጥ ለውስጥ ይሄ ነገር ለአንድ ሀምሳ አለቃ የኔ የነበረው ለሱ ነገርኩትና እሱ እንዲያሳድማቸው አድርጌ ወደሚጣልበት ዴክ እንሱን ታች ትቼ ላይ ዴክ ነው እኔ የተዘጋጀው ሬሳው ወጥቼ ኸ ወታደሮቹ እምቢ አሉኝ አልኳቸው:: ነገርኳቸው ለሻለቃ አባገሮ:: ሻለቃ አባገሮ በቀጥታ «እኔ ምን ላድርግ? ወታደሮቹ ሬሳው እንዳይጣል ብለውኛል::» ብለው ተናገሩ:: እና ሬሳው በዚህ አስጣልነው:: እና የመጀመሪያ በረዶ ውስጥ ገብቶ በሳጥን ላይ ኮሪያ ደረሠ:: መጀመሪያ አፈር ውስጥ የገባ ኮሪያ የኢትዮጵያ ወታደር መርከብ ውስጥ የሞተው ነው (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 5-6፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)::

17. በኋላ ደግሞ በሌላ ቀን ድል አድርገን አንድ ምርኮኛ አገኘን:: ሁለት አገኘንና አንዷን አርቀን አቆምን:: ርቃ ቆመች:: ያቺን፣ አንድ አምሳ አለቃ ነበረ፣ ሱሪ ፈታና ዳቦ ተኪሱ አወጣና

ያንን እንዲህ እያደረገ ሲበላ ያቺ ታያለች። ሲበላ ታያለች። ታይና ሆዷን ያማታል። «ልሂድ ትላለች፣ ሆዱን አሞኛል» «ሂጂ» አላት። እኛ እንድትጠፋ ነው እንግዲህ፣ ሄደች፣ አልፈለግንም። እኛ እናያታለን፣ ሄዳ ተቀላቀለች። ማዶ ለማዶ ነው እንግዲህ ያለነው፣ ተቀላቀለች። ያቺን ብድግ አረግንና ሴሬዋን ታጠቀች፣ ወደ ምርኮኛ ቦታ። ይህንን ስራ ሰርታ «ሰው በላ መጣ» አለች። እኛ ሰው አንበላም። «ሰው በላ መጣ» አለች። በዚህ ስማችን ወጣ። አንድም ሰው ላይ ሳይማረክ፣ አለም በሙሉ ሲማረክ ኢትዮጵያ ምንም። እንኳን ሰው ቀርቶ ሽመል እንኳን አልተማረከም። አንዲት ምርኮኛ የለችም፣ ድል ተማድረግ በስተቀር (አስር አለቃ አሰፋ አስፋው፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 9፣ ሐምሌ 30፣ 1999 ዓ.ም)።

18. ተኩሳችንም ሃይለኛ ነው። ውጊያችንም ሃይለኛ ነው። የፈለገ ሰው ይለቅ እኛ በቆራጥነት አንድ ጊዜ ወጥተናል ለሃገራችን በቃ ለመሞት። እእእ ደግሞ አንድ ሰው ቢቆስልብን ወይንም አንድ ሰው (ፋታ)፣ አንድ ቁስለኛ (ፋታ)፣ አንድ ጅፋር ፍታል እሚባል አለ። አንድ አሽኔ እሚባል ሀኪም ነበረ። ይገርማችኋል ለካ እሱ ኢም ዋኑን ሰቅሏል፣ ተክሏል። ስንቆጣጠር የለም። እንዲህ ስናይ ማዶ ላይ አለች። ትንሽ ተራራ ነች። ተራራ ሥር ወድቋል «አሽኔ ሂድ» አለ። «ደክመኝ እኔ አልሄድም» አለ። «እኔ ልሂድ» አለ ጅፋር ፍታል። ሄደ። በከባድ መሳሪያ እንደበድብ ጀመር ዙሪያውን። ሄደ፣ አልቻለም ወደቀ። ይሄ ሎሚ እንዲህ ጥምዝዝ አለ። አየር ወዲያው። በጀግንነት ተጻፈ። እንደጀግና የሚቆጠር ነው።

እንዴት?

ብድግ አደርጋለው፣ እሸከማለው ሲል ከነመሳሪያው፣ በቃ አልቻለም። ይህን ጊዜ እግሩ ወለም አለች፣ ሎሚዋ። ሁለቱም ተዋደቁ። ከዛን በኋላ ጠሩ ሄደ፣ አነሳቸው ሁለቱንም። እና የዝያን ያህል ነው። እኛ ምርኮኛ የሚባል ነገር የለም። ምርኮኛ የሚባል ነገር የለም። እና አንድ ሰው ወታደር አላማውን ስለሆነ ጉዳይ ዓላማውን የፈለገ ነገር ይምጣ። ይሄ ነው የማቀው። እኔም ከዛም በኋላ በአስራ አንደኛ ወሬ ተመታው (አስር አለቃ አሰፋ አስፋው፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 9-10፣ ሐምሌ 30፣ 1999 ዓ.ም)።

19. ጥያቄ፡- ግንባር ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ተኩስ ጠላት ላይ የከፈታችሁበት አጋጣሚ ትዝ ይልዎታል?

መልስ፡- እንዴ! በጣም እንጂ። እንደ ዛሬ አስር ሰባ ሶስት ተራራ ያዘን። በበነጋው ጠዋት ወደ ጠቅላይ ሰፈር ተጠራሁ። እኔ ነኝ መጀመሪያ ጦር ግንባር የገባሁት ውጊያ የገጠምኩት። የኔ የመቶ ነው። ከዚያ በኋላ ኸ «ያንን የምታየው ተራራ ሂደህ ኸ.. በተኩስ ሀይል እንድትሰልል ዛሬውኑ አሁኑኑ ትሄዳለህ» አሉኝ። «የት?» ስል ተራራ አሳዩኝ።



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

«እንዴ ጠላት የለበትም እንዴ አገሩ?» አልኩ ርቀቱን ሳይ፡፡ «ያንን ሁሉ አንድ የመቶ ብቻዬን ይገፍ ሰላሳ ስድስት ወታደር ሂጄ ድንግጥ አልኩ፡፡ «እውነትም ጠላት የለበትም እንዴ እዚህ አገር?» አልኩ፡፡ አሁን ትዝዜን ተቀበልኩ፡፡ ልክ እኛ የያዝነው ያለነው አስር ሰባ ሶስት የተባለ ተራራ ነው፡፡ ያ ተራራ እኔ እምሄድበት እንዲህ ስታየው ከዚህ እንደ፣ በትንሹ ልበልህ ኽ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን ይሆናል |መረጃ አቀባዩ ቃለ መጠይቁን የሰጡኝ መንን አካባቢ በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ በመሆኑ ከመነን እስከ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን ድረስ ያለውን ርቀት ከግምት ውስጥ በማስገባት ሊገልጹ የፈለጉትን ርቀት መገንዘብ ይቻላል|፡፡ አሁን ቁልቁለት ነው፡፡ እንዲህ ወንዝ ወርጄ እንደገና ዳገት ወጥቼ ነው የምደርሰው፡፡ አሁን ሰላሳ ስድስቱ የኔ ወታደሮችና ሁለት በፍቃደኝነት እንሄዳለን ያሉ ወታደሮች ሰላሳ ስምንት ወታደር ይገፍ ሄድኩኝ፡፡ እና አስራ ሁለት ሰዓት ተኩል ገደማ ደረስን ዳገቱን እስክንወጣ ምን ስል፡፡ አስራ ሁለት ሰዓት አይመሽም ነበር፤ ምክኒያቱም የፀሀይ ጊዜ ነው፡፡ አልመሸም ገና ነበረ፡፡ ከዛ በኋላ፣ በተኩስ ሀይል ሞክር ነው የተባልኩት፤ እኔ አልተኩስም እነሱ ካልተኮሱ፡፡ ይሄን ጊዜ ሳየው በመነጽር እንዲህ አድርጌ ሳይ አንድ እንቅስቃሴ የለም፡፡ ምናልባት ከዚህ እንደ ምን ልበልህ ግፋ ቢል ግፋ ቢል የዩኒቨርሲቲው በር ያህል ደርሻለው |መረጃ አቀባዩ ቃለ መጠይቁን የሰጡኝ መነን ትምህርት ቤት ፊት ለፊት በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ በመሆኑ ከመነን እስከ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስድስት ኪሎ ካምፓስ በር ድረስ ያለውን ርቀት ከግምት ውስጥ በማስገባት ሊገልጹ የፈለጉትን ርቀት መገንዘብ ይቻላል|፡፡

አሁን እዛ ላይ በመነጽር ስመለከት ምንም የለም፡፡ ይሄን ጊዜ አንደኛ ጓድን በጓዶች አሰልፌ ይሄን ጊዜ የሀምሳ አለቃውን አንድ ቦታ አለች ጉብታ ነበረች፤ እዚህ ሁነህ ያችን ምሽግ አፏን ከፍታ የምትታየውን ምሽግ ሰባ አምስት መትረየስ አዕፌህ አነጣጥርባትና ከተኮሱ ምታት አልኩና ሰሱ ትዛዝ ሰጥቼ ሁለቱን ጓዶች ያዝኩና ወደ ፊት ስገስግስ ልክ ተራራው፤ ይች ምን ልበልህ የዚህችን መንገድ ያህል ነው ስፋቷ ተረተሯ |ፊት ለፊታቸው የተቀመጠን ጠረጴዛ በማመልከት|፡፡ እና በዛ በአንድ ተራ ነው ያረኳቸው፡፡ ልክ መሃከሉ ስንደርስ መትረየስ ተኮሱ፡፡ አሁን ወታደሩ በሃምሳ ሰባት ብትን እረጋት ወታደሩ ያችን ምሽግ፡፡ ሩጠን ደረስን እዛ፡፡ እና ቅርብ ነበረች፡፡ እንዳልኩ ከዚህ እንደ ዩኒቨርሲቲው ገደማ ናት |መረጃ አቀባዩ ቃለ መጠይቁን የሰጡኝ መነን ትምህርት ቤት ፊት ለፊት በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ በመሆኑ ከመነን እስከ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስድስት ኪሎ ካምፓስ በር ድረስ ያለውን ርቀት ከግምት ውስጥ በማስገባት ሊገልጹ የፈለጉትን ርቀት መገንዘብ ይቻላል|፡፡

እዛ ገባን፡፡ ለካ እነሱስ እራት ሊበሉ ወደ ኋላ ሄደውልሀል፡፡ ሰው የለም እዛ፡፡ ሌሊት አጥቅቷቸው የሚያውቅ ሰው የለም፡፡ አይፈሩም ሌሊት ተኝተው ነው የሚያድሩት፡፡ እኛ የመጀመሪያ ነን ሌሊት ስናጠቃ፡፡ ይሄን ጊዜ እእእ ያንን ምሽግ ስንይዝ



ILS LIBRARY ADDIS

እንኛ ሸሽተው አምልጠዋል፣ እዛ የነበሩ፣ ደረስንባቸው። ያዘንና ቁጭ አልን። አሁን «ቦታውን ይገፍለሁ» ብል አላመኑም፤ ከላይ። ይሄን ጊዜ የሽጉጥ መብራት ሽጉጥ ጥይት አለኝ እሱን ተኩሼ ይሄው መያዜን ያው እውነትም እዛ ላይ መሆኔን ያረጋገጡ። ልክ አራት ሰአት ሲሆን ኮሽታ ተሰማ ግራና ቀኝ። ከምሽቱ ወደ ሶስት ሰዓት ገደማ መሰለኝ። ኮሽታ ይሰማል። አፈር ሲፈርስ ምን ሲል ጋራ ነው። እንግዲህ መውጫዋ አንድ ናት። መግቢዋም አንድ ናት። በዚህ በኩል አሁን ፊት ለፊታችን ያለው ተረተር ነው እሱም። ሰብዙ ሰው አያስልፍም። ግን ከገባንበት ይሻላል ያ ክፍት ነው። ልክ አራት ሰዓት ገደማ ሲሆን በመድፍ ቆፈሩት፤ ያንን ተራራ። ግን እነሱ ያዘጋጁት ምሽግ ነው፤ አቶሚክ ቦንብ ቢፈነዳ አይገነጥለውም። ራሳቸው የሰሩት ምሽግ ነው። ስንጨፋጨፍ ስንጨፋጨፍ ጦሩ አለቀ በቃ። ብዙ ቆሰለብኝ። እንዲህ እስከ አስር ሰዓት ከለሊቱ ተከላከልን። ታገለ ወታደሩ። ከዛ በኋላ እ በተለይ መጀመሪያ መትረየስ ተኳሹ ገደሉብኝ። እና ከፍተኛ ትግል አደረግን።

ኋላ ነጋ። አፈገፈጉ እነሱ። ለሊቱ ግን የመድፍ ተኩስ እንዲህ ከበበን፤ የወገን። በውነቱ ከፍተኛ እርዳታ ነው ያደረጉልኝ። አደርን። በውነቱ እኔ ሰው ይተርፋል ብዬ አላሰብኩም። ቀላጭ የሚወርደው የመድፍ ብዛት ተራራዋን እንዲህ ዙሪያዋን ቆፈሯት። እና በውነቱ አደርን። ጠዋት ያው የቆሰለውም ሌላውም አሜሪካኖች መጥተው ቦታውን ተረከቡ። እኔም ወደ ሰፈር ተመለስኩ። እና የኢትዮጵያ ጦር የመጀመሪያ ስም ያገኘበት ቀን እሱ ነው። አንድም ሳንማረክ አንድም ሳናስደፍር ምሽጉንም አድረን ለአሜሪካኖች አስረክበን መጣን። ያን ዕለቱን ማታ አጥቅተው ቻይናዎች እንደገና ያዙት። አሜሪካኖች ሸሹ (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 9-10፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)።

20. አንድ ወታደር ከማስታውሰው ታሪክ ከእኔ የመቶ ተደርቦ የሄደ ነበር አስፋ ይባላል። በውነቱ ሊነጋጋ ሲል እኔ ሻምበል አዛገፎን አስፈትጄ ወረድኩ ወደነሱ፤ ከኔ ፊት ለፊት ናቸው። እዚያ ስደርስ «አስፋ ሞቷል» አሉኝ። እና አንድ ድንጋይ ስር ቁጭ ብሏል፤ ተኝቷል። በደረቱ እንዲህ አስተኝተውታል። ሳየው ገልበጥ አድርጊ፣ እንዲህ ሳይ ትኩሳት አለው ልቡ ላይ። አፌ ውስጥ ሲጋራ ያገባሁት ያን ለት ነው። ከዛን በኋላ እንደ ክሮኒክ ሆኖ ሰላሳ ዓመት አጨስኩኝ። ሲጋራ አፌ ውስጥ የገባችው ያን ለት ነው። ሲጋራ ያጨሳል እሱ። «ሲጋራ ስጡኝ ሲጋራ ያለው» አልኩና ስቢ ገልብጬ አፍ ስልበት ዓይነ ሞራው ግልጥ አለ። ከዛም ወደ ሆስፒታል በህይወት ደረሰ። ግን ለረጅም ሰዓት እንዲህ ስለወደቀ ሸባ ሆነ። ደሙም ፈሰሰበት። እና ይሄ መጀመሪያ ሲጋራ ያጨስኩበት በመሆኑ ላስታውስ የምፈልገው ይሄን ነው (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 11፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)።

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

21. አንድ ወታደር ደግሞ እንዲህ አድፍጦ ሲጠብቅ፣ ጊንጪ እንለዋለን ወታደሩን፡፡ የጊንጪ ሰው ነው፡፡ እንትልፍ ይዞት ብንን ሲል ባርኔጣው ይንከባለልበታል፡፡ በጥይት አነጣጥሮ ትጥል ያደርገዋል ያን ባርኔጣውን፣ የሚሸሽ መስሎት፡፡ ከዚያ በኋላ «ገደየዋለው» አለ፡፡ «አልሄደም፣ አላመለጠም"፡፡» ሲንጋ ሲታይ ባርኔጣው /ግት/ (ኮሎኔል ገብረ ኢያሱስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 2፣ ስክርብ ገጽ 29፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)፡፡

22. አንድ ጊዜ ሳይታወቅ ጦር ሜዳ የተቀበረ ፈንጅ ላይ አንድ ወታደር ይረግጥና ብትንትኑ ይወጣል፡፡ ቀን በቀን ነው፡፡ ትልቅ ጦርነት ነበር፡፡ የአውሮኘላን ጦርነት ነበር፡፡ የመድፍ ነበር፡፡ የእግረኛ ነበር፡፡ ይሄ ሁሉ እያለ ያንን የተበጣጠሰ ወታደር አስከሬን ምናምኑን ሁሉ ሰብስቦ ወደ ኋላ ወስዶ ጉዛን ሄዶ እንዲቀበር ተደርጎ ነበር (ኮሎኔል አለማየሁ ካሳ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 2፣ ስክርብ ገጽ 22፣ ነሐሴ 21፣ 1999 ዓ.ም)፡፡

24. አንዱ ወታደር ከእኛ ጋር ዕረፍት ሄዶ አንድ ጌሻ ቤት ይገባል፡፡ [ጌሻ ማለት በልምድ ንጹህ የሆኑ የባለባት ወይም የሀብታም ልጆች ሆኖ ሴት አዳሪዎች ናቸው]፡፡ ይሄ እንደ ሀንድ እዚህ ላይ የሚለብሱት አለ፡፡ ጌሻ ነው፣ የጌሻ ልብስ ነው፡፡ እነርሱ ናቸው፡፡ እና አንዱ እንግዲህ ሃላፊዋ ማመሳን ነው የምትባለው፡፡ እዚያ ይገባና ማምሳን ትጠራለታለች «ምረጥ» ትለዋለች፡፡ ከብዙዎቹ አንድዋን መረጠና እግሩን ታጥባለች፣ ጥፍር ትቆርጣለች፣ ትዘፍንለታለች፡፡ ተንበርክካ ነው ይሄ ሁሉ የሚደረገው፡፡ በኋላ ያንን ፍላጎታቸውን ከፈፀሙ በኋላ «ለመሆኑ እናንተ ሀገር ዘፈን ምን ይመስላል? እስቲ ዝፈንልኝ?» ትለዋለች፡፡ ዘፈን «ገንዘቤ፣ ገንዘቤ፣ ገንዘቤ....» እያለ ይዘፍናል፡፡
መጨረሻ ላይ «ምን ማለት ነው ትርጉሙ?» ትለዋለች፡፡ እ... «ማይ መኒ፣ ማይ መኒ፣ ማይ መኒ...» ማለት ነው ይላታል፡፡ «ሄይ ዩ መኒ? ዩ ፔይ ሚ መኒ?» ታመጣና እፍንጫው ላይ ትወረውርለታለች፡፡ ትወረውርለትና «በቃ ከእኔ ጋር ግንኙነት አቋርጠሃል፡፡» ትለዋለች፣ ገንዘቡን ትመልስለትና፡፡ ሰውየው ይደነግጥና «እና መልሺ እኮ ማለቴ አይደለም» አላት፡፡ አስተርጓሚዋ ደግሞ ማመሳን ናት፡፡ እና እንደዚህ ሆኖ ገንዘቡን መለሰች፡፡ እሱም ሳይከፍል ጉዳዩን ተጠቅሞ ወጥቶ ሄደ አልሃለሁ፡፡ እስከዚህ ያለ የሚያስቅ ነገር ነው (ኮሎኔል አለማየሁ ካሳ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 2፣ ስክርብ ገጽ 17፣ ነሐሴ 21፣ 1999 ዓ.ም)፡፡

25. አንድ ጊዜ የግሪክ ወታደሮች ሰዓት የማይሰራ ሰዓት፣ ትንሽዬ እየሠሩ ለእኛ ወታደሮች ይሸጣሉ፡፡ በኋላ የእኛ ወታደር ይገዛና በቃ መገናኘት ጀምረዋል በተለይ ግሪክ ተቀራርበናል /ላት/፡፡ በኋላ ሰዓቱ ትንሽ ይቆይና ይቆማል፡፡ ትንሽ ቆይቶ ሲቆም ያ የገዛው ሰውዬ



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

ይሄድና ያንን ግሪክ እንግቱን ያንቀዋል። እና የአሜሪካን ሚሊተሪ ፖሊስ አለ። ይሄድና ያስጥለዋል። «ምንድነው ታሪኩ? ሁኔታው?» «እንደዚህ አታሎኝ ነው የገባሁት» «ማነው የሼጠልህ» ይለዋል። በኋላ እንጃ ተካሰው ገንዘቡን እንዲመልስለት ተደረገ። ሰዓቱን መልሶ ወሰደ ያ ግሪኩ (ኮሎኔል አለማየሁ ካሳ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 7-8፣ ነሐሴ 21፣ 1999 ዓ.ም)።

26. መርከብ ላይ እያለን ሁል ጊዜ ምግብ ቤት ሁል ጊዜ ምግብ ቤት የሚቀርበው ምንድነው እንትን አለ፣ ኦትሶስ ኦትሶስ፣ ይሄ ተባስኩ። ሻይ ወይም ቡና ስንጠጣ ስኳር አለ፣ ወተት አለ፣ ዳቦ አለ። ምንድነው ደግሞ ይሄ የአሣማ ሥጋ የሚባል አለ። ልዩ ልዩ ምግብ አለን። እዛ ምግብ ቤት ስንገባ ሁሉም እንደ የሀገሩ ባህል የሚወደው ምግብ አለ። የሁሉም ሀገር እንግዲህ ባህል አለው። ለምሳሌ ግሪክ ዳቦ ፋርኖ ምንለውን በኃይል ነው የሚበሉት። በኃይል ነው የሚወዱት፤ የሚፈልጉትም። ምን በቃ እዚያ ገበታ ላይ ስንገባ አይበቃቸውም። ዳቾች [የሆላንድ ወታደሮች] ደግሞ ምንድነው ድንች ድንች በጣም ይወዳሉ። በጣም ይወዳሉ። ፊሊፒንስና ታይላንድ ደግሞ ምንድነው የሚወዱት፣ ሩዝ ነው። ተርኪም እንደዚሁ ሩዝ ነው የሚበላው። ተርኪም እንደኛው፣ እንደኛው ወታደር የአሣማ ሥጋ አይወድም። በሃይማኖታቸው እንትን ነው። ስለዚህ እነሱም ሩዝ ነው የሚበሉት። ሩዝና ይሄ ቅመማ ቅመም። ህንዶችም ነበሩ ግን ህንዶች አልተዋጉም። ኸ የመርከብ ላይ ሬድ ክሮስ [የቀይ መስቀል] አገልግሎት ይሰጡ ነበረ። እና እነሱም እንደዚሁ ሩዝ ይበላሉ። የእኛ ወታደር ደግሞ ምን መሰለህ የምን የምንፈልገው ኦትሶስ፣ ይሄ ተባስኩ፤ እሱንና ስኳር። እዛ መርከብ ላይ ምን ብለው ይቀልዱብን ነበር ወይም ደግሞ ያሾፉብን ነበር «ዘ ኢትዮጵያንስ ዱ ኖት ድሪንክ ኮፊ ዚይ ዱ ኖት ድሪንክ ዚይር ኮፊ አንትል ዘ ስፑን ስታንድስ እስቲል» ይላሉ። ማንኪያው ቀጥ ብሎ ሻይ ስኒው ውስጥ እስከ ሚቆም ድረስ ስኳር ይጨምራሉ ማለታቸው ነው። እና እንደዚህ ያለ ስም ለየ ለየ ለየዘሩ በየባህላችን ተጠቅመናል (ኮሎኔል አለማየሁ ካሳ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 8-9፣ ነሐሴ 21፣ 1999 ዓ.ም)።

27. አንድ ጥቁር አሜሪካን እንዳባቴ፣ ወጥ ቤት ነው፣ እንዳባቴ አርገው እዛ መርከብ ላይ፣ በጣም በውነቱ እንደ ልጁ ያየኛል። ወጥ ቤት፣ የመርከቡ ወጥ ቤት ነው። ከሱ ጋር ቁጭ ብዬ ስጫወት አንድ ጥቁር አሜሪካዊ አምጥቶ አሜሪካ የሚባል የዝንብ፣ የትንኝ መግደያ አፍንጫዬ ላይ ስነዛብኝ። አዙሮኝ ወደኩ። እና ታመምኩ፣ ራስ ምታት። መቼ ነበር (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 6፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)።



ILS LIBRARY ADDIS ABABA UNIVERSITY

28. መርከቦች፣ መርከበኞች ቀን ቀን ዶሴን እየፋቱ ቀለም ይቀባሉ:: ጨዉ ይበላዋል ብረቱን:: እና ሌሊት ተነስተው አምጥተው ውሀ ይረጩብናል:: ሶስት ነን እዛ መርከብ እንደ ዱርዬ ሆነን የቀረነው፣ መኘታ የለለን፣ ደረጃ ላይ የምናድረው:: ኋላ አንድ ቀን በጎማ አድርጎ ማጠቢያ አለ:: እዚህ ፊቴ ቢለቀልቀኝ ትዝታዬ የወረረው፣ ከባህር የወጣ ውሃ ነው ልጦ ለቀቀኝ:: እና ይሄ ይሄ ነው የገጠመኝ በመርከብ ላይ (ኮሎኔል ገብረ ኢየሱስ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 6፣ ነሐሴ 10፣ 1999 ዓ.ም)::

29. ኧ እንግዲህ በትሬኒንግ ላይ ሞርታር፣ ሞርታር የሚባል ሀይ ትራጀክተሪ ያለው ኧ እሱን በምንጠቀምበት ጊዜ ያለካልኩሌሽን እንደ ሞርታር ይተኮሳል:: ሲተኮስ ምን ሆነ ከፊት ለፊታችን ሄዶ ማረፍ በሚገ ሲገባው ፊንጁን በትክክል ካልኩሌት ባለማድረግ ሲተኮስ ከሠራዊቱ ጀርባ ከኋላው ወረደ:: ሲወርድ ከኋላ ያሉት ወታደሮች ጩኸት በጩኸት ሆኑ:: «ምንድነው?» ሲባል «እንዴ ፊንጁ እኮ እኛ ላይ ነው፣ እኛ ላይ ነው ያረፈው::» ምናምን አሉ:: ግን እንደአጋጣሚ ምንም የቆሰለ ነገር የለም:: (ኮሎኔል አለማየሁ ካሳ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 11-12፣ ነሐሴ 21፣ 1999 ዓ.ም)::

30. ኧ በምሽግ ውስጥ ሆነን ደግሞ አንዳንድ ጊዜ፣ ካሳ ሞላ የሚባል ሬዲዮ ኦኘሬተር ነበር:: ካሳ ሞላ «ኪም» ወይም ደግሞ አንድ የነሱን ስም ይጠራና «አፈር ብላ፣ አፈር ብላ፣ የት አባክ!» ምናምን እያለ በሬድዮ ይሳደባል:: እነኛም ደግሞ «ካሳ ሞላ አፈር ብላ፣ አፈር ብላ» ይላሉ /ሳቅ/:: እንደዚህ የሚል ጭውውት ነበረ (ኮሎኔል አለማየሁ ካሳ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ካሴት ቁጥር 1፣ ስክርብ ገጽ 15፣ ነሐሴ 21፣ 1999 ዓ.ም)

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

## ዋቢ መጻህፍት

### በአማርኛ ቋንቋ የተጻፉ ስራዎች


ሁሳዊ ዮሴፍና ሌሎች፣ 1989፣ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ፣ ቅጽ አንድ፣ አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

ሳህሉ ኪዳኔና ሌሎች፣ 1993፣ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ፣ ቅጽ አምስት፣ አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

ስለሺ ቱጂና ሌሎች፣ 1991፣ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ፣ ቅጽ ሶስት፣ አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

ታኘው፣ 1987፣ የኢትዮጵያ ኮሪያ ዘማቾች ማህበር መጽሔት፣ አዲስ አበባ።

_________፣ 1993፣ የኢትዮጵያ ኮሪያ ዘማቾች ማህበር መጽሔት፣ አዲስ አበባ።

_________፣ 1996፣ የኢትዮጵያ ኮሪያ ዘማቾች ማህበር መጽሔት፣ አዲስ አበባ።

_________፣ 1997፣ የኢትዮጵያ ኮሪያ ዘማቾች ማህበር መጽሔት፣ አዲስ አበባ።

_________፣ 1998፣ የኢትዮጵያ ኮሪያ ዘማቾች ማህበር መጽሔት፣ አዲስ አበባ።

ቢያዝን መኮንን፣ 1944፣ ቃኘው ሻለቃ፣ የእሳቱ ላንቃ፣ አዲስ አበባ፣ መርሐ ጥበብ ማተሚያ ቤት።

ተስፋዬ ገብረ አብና ሌሎች፣ 1990፣ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ፣ ቅጽ ሁለት፣ አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

ተስፋዬ ገብረ አብና ሌሎች፣ 1992፣ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ፣ ቅጽ አራት፣ አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

ታገል ሰይፉ፣ 1990፣ አምሳ አለቃ ገብሩ ቢሆንም ቢሆንም፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

አዲስ ዘመን፣ ቁጥር 10፣ ሚያዝያ 6፣ 1943።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣ 1993፣ አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ዳምጤ አስማኸኝ፣ 1950፣ ጠቅልና ስራዊቱ፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ፣ 1998፣ ክህደት በደም መሬት፣ ፍሬድሪክስበርግ፣ አዞፕ አሳታሚና አከፋፋይ።

ፈቃደ አዘዘ፣ 1991፣ የስነ-ቃል መምሪያ፣ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መጻህፍት ማዕከል።

## በውጪ ቋንቋ የተጻፉ ስራዎች


A Handbook of Korea.1978. Seoul Oversea Information Service.

Agar, Michael.1980. "Analysis of themes in life history narrative," *American Ethnologist*, 7:211-223.

Babcock, Barabara A.1977. "The story in the story: Metannaration in Folk Narrative" in Verbal art as Performance. Bauman, Richard. (ed). Waveland Press, inc.Long Grove, IL.

Bascom, William.1965. "Four Functions of Folklore," In The Study of Folklore. Dundes, Alan (ed). Prentice Hall, Englewood Cliffs, N.J.

Bauman, Richard.1977. Verbal Art as Performance. Waveland Press, Inc.

__________.1983. "The Field Study of Folklore in Context," in Handbook of American Folklore. Dorson, Richard (ed). Bloomington: Indiana University Press.

__________.1986. Story, Performance and Event. Cambridge: Cambridge University Press.

Ben-Amos, Dan.1993. "'Context' in Context," *Western Folklore*, Vol.52, no.214, pp 209-226.

Braid, Donald.1996. "Personal Narrative and Experiential Meaning," *The Journal of American Folklore*, Vol.109, No. 431. pp. 5 -30.

Burke, Carol.2002. "Phantom Soldiers, Angel Helpers, and *Barbarella*" *FOAFTALE NEWS*.No.53, December.

Chul-In, Yoo.1991. "Storytelling among Korean Immigrants: The Interplay of Reality, Experience and Expression." *Korea Journal*, Vol.31.no 2, pp.93-100.

Clements, William.1980. "Personal Narrative, the Interview Context and the Question of Tradition," *Western Folklore*, Vol. 39, no. 2, pp.106- 112.

Cleveland, Les.1987. "Military Folklore and the Underwood collection," New York Folklore, Vol. 13 no. 3-4, pp 87-103.

Cornell, George.1981. "G.I. Slang in Vietnam," *Journal of American Culture*, pp 195-200.


ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

Degh, Linda.1970. "Is There a Folk in the City?" *The Journal of American Folklore*, Vol. 83, No. 328, pp. 217-224

Dereje Tekle.1993. "The History of Qagnew Battalions in Korea." Unpublished BA Thesis Submitted to the Department of History. Addis Ababa University.

Dijk, Teun Van. 1975 "Action, Action Description, and Narrative," *New Literary History*, 6, 273-294.

__________.1976a. "Narrative Macro-structures: Logical and Cognitive Foundation," *A Journl of Descriptive Poetics and Theory of Literature* 1:547-568.

__________.1976b "Philosophy of Action and Theory of Narrative," *Poetics*, 5:287-338.

Doorn, Jacques Van.1968. Armed Forces and Society. Mouton & Co.N.V., Publishers, The Hague.

Dorson, Richard.1972. Folklore and Folklife An Introduction. Chicago: University of Chicago Press.

Dundes, Alan.1965. The Study of Folklore. Prentice Hall, Englewood Cliffs, N.J.

Fekade Azeze.2001. "The State of Oral Literature Research in Ethiopia: Retrospect and Prospect," *Journal of Ethiopian Studies*.Vol XXXIV, No.1. Institute of Ethiopian studies. Addis Ababa University.

Freeman, M.2006. 'Life "on holiday" : In defense of big stories,' *Narrative Inquiry*,16.

Ferris, William.1976. "The Enlisted Man: Army Folklore," *New York Folklore*, Vol. 2, pp 229-234.

Fish, Lydia.1989. "General Edward G. Lansdale and the Folksongs of Americans in the Vietnam War," *Journal of American Folklore*, Vol.102, no.406, pp 390-411.

Gilbert, Kathleen R. 2002. "Taking Narrative Approach to Grief Research: Finding Meaning in Stories," *Death Studies*, 26:223-239.

Han-gyu, Lee. 2006. "A New Infrastructure for Korea's African Diplomacy," *Korea focus*, vol.14, no. 4, pp. 36-37.

History of UN Forces in Korean War. 1972. Vol.I .Seoul. Ministry of National Defence.

Labov, W. and Fanshel, D.1977.Therapeutic Discourse: Psychotherapy as Conversation.New York: Academic Press.

Labov, W.1997. "Some Further Steps in Narrative Analysis," *Journal of Narrative and Life History* 7(1-4): 395-415.

__________.2006. "Narrative Preconstruction," *Narrative Inquiry* 16:37-45.

__________.2007.Oral Narratives of Personal Experience. [Internet]

Jones, Michael Owen (ed.).1994. Putting Folklore to Use. The University Press of Kentucky.

Jun-yop, Kim.1995. "Fiftieth Anniversary of Liberation: A Review for Future," *Korea Focus*, Vol. 3, no.1 pp 5-11.

Kaushik, R.P.1972. The Crucial Years of Non-alignment: USA Korean War India. New Delhi, Kumar Brothers.

Koch, Edwin E.1953. "G.I. Lore of the Fifteenth Air Force," *New York Folklore Quarterly*, Vol, 9, pp 59-70.

Marcus, Harold.1982. "American Security and Ethiopia, 1948-1953." Proceedings of the Seventh International Conference of Ethiopian Studies. University of Lund. 26-29 April 1982.

Margaret' K. Brady.1980. "Narrative Competence: a Navajo Example of Peer Group Evaluation," *Journal of American folklore*, Vol, 93, pp 158-181.

May, Vanessa. (2004, December) Public and Private Narrative.Conference Report: Conference on Narrative, Ideology Myth-Second Tempera Conference on Narrative [50 paragraphs]. Forum Qualitative Social Research [online Journal].5(1) Art.19, Available at: http://www.dqualitative-research.net/fqstexte/1-04/1-04 tangung-may-e.htm [Date of Access 5/1/2007]



ILS LIBRARY

Mullen, Patrick.1992. Studying the Elderly. Chicago, University of Illinois Press.

Nusbaum, Philip.1991. "Traditionalizing Experience: The Case of Vietnam Veterans," *New York Folklore*, 17, no 1 and 2, pp 45-62.

O' Ballance, Edgar.1969. Korea 1950-1953. Hamden, Archon Books.

Oring, Elliot (ed.).1986. Folk Groups and Folklore Genres. Utah, Utah State University Press.

Polanyi, Livia.1979. "So what's the point?" *Semiotica*, 25. 207-241.

Ratner, Carl. (2001, September). Analyzing Cultural-Psychological Forum Themes in Narrative Statements [13 paragraphs]. Sozialfors cung/Forum: Qualitative Social Research [On-line Journal], 2(3). Available at: http://www.qualitative-research.net/fqs/ fqs-eng.htm [Date of access: September 4, 2007]

Riessman, C.2002. "Analysis of Personal Narratives," in J.Gubrium and J.Holstein [eds] Handbook of Interview Research.Thousand Oaks: Sage.

Sandra, Stahl 1979. "Style in Oral and Written Narratives." *Southern Folklore Quarterly*.

__________.1977. "The Personal Narrative as Foklore." *Journal of the Folklore Institute* 14:9-30)

Skordiles, Kimon.1954. KAGNEW: The Story of the Ethiopian Fighters in Korea. Tokyo.

Slim, Hugo. and Thompson, Paul.1993. Listening for Change: Oral Testimony and Development.Panos Publications Limited.

Squire, Corinne .2007. "Reading Narratives." *Group analysis*. Vol 38 (1):91-107.

Stowe, Peter .1986. The Origins of The Korean War. New York, Longman Inc.

Steuck, William.1995. THE KOREAN WAR: An International History. Princeton: Princeton University Press.



ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

The History of United Nations Forces in the Korean War. 1972. Vol I. Seoul Ministry of National Defense.

The History of United Nations Forces in the Korean War. 1973. Vol II. Seoul Ministry of National Defense.

The History of United Nations Forces in the Korean War. 1974. Vol III. Seoul Ministry of National Defense.

Titon, Jeff. 1980. "Life story," *Journal of American Folklore*, Vol.93, no.369, pp 276-292.

Vansina, Jan. 1965. Oral Tradition. Routledge and Kegan Paul.

________ 1985. Oral Tradition as History. Nairobi, Heinemann.

Wilson, William A. 1998. "The Deeper Necessity Folklore and the Humanities," *Journal of American Folklore*, Vol .101, no.400, pp 156-167.

Wolfson, Nessa. 1978. "A Feature of Performed Narrative: The Conversational Historical Present." *Language in Society*, 7:215-237 www.teacherslounge.editme.com/files/emartinsories /Short% 20Story%20 Literary%20Terms.doc